ጅማ ዩኒቨርሲቲ ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል

የድህረምረቃ መርሀግብር

# በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂልን ለመማር ያላቸው ፍላጎትና የውጤት ተዛምዶ በጂማ ዞን በጢሮ አፈታ ወረዳ በዲምቱ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት

በ

እታጉ ጌታቸው

አማርኛን በማስተማር ለሁለተኛ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት

ሐምሌ 2013 ዓ.ም

ጅማ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል

የድህረምረቃ መርሀግብር

# በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂልን ለመማር ያላቸው ፍላጎትና የውጤት ተዛምዶ በጂማ ዞን በጢሮ አፈታ ወረዳ በዲምቱ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት

በ

እታገ ጌታቸው

ዋና አማካሪ፡- ጥበቡ ሽቴ (ዶ/ር)

ረዳት አማካሪ፡- ለማ ንጋቱ (ዶ/ር)

አማርኛን በማስተማር ለሁለተኛ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት

ሐምሌ 2013 ዓ.ም

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## *ምስጋና*

*በቅድሚያ መንገዴንና ጥረቴን ሁሉ ያቃናልኝን አላህን አመሰግናለሁ፡፡*

*ይህን ጥናት ከመጀመሪያው ጀምሮ እስከማጠናቀቂያው ድረስ በየጊዜው ስህተቶቼን እያረሙ አቅጣጫ በማሳየት ላገዙኝ የጥናቱ ዋና አማካሪዬ ዶ/ር ጥበቡ ሽቴ እና ረዳት አማካሪዬ ዶ/ር ለማ ንጋቱ ከፍ ያለ ልባዊ ምስጋና ላቀርብላቸው እወዳለሁ፡፡*

*ጅማ ዩኒቨርሲቲ ይህን ጥናት ለማካሄድ የሚያስፈልገኝን የጥናት ወጪ በመሸፈን ላደረገልኝ ድጋፍ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡*

*ባለቤቴ አቶ ፈቆ አማን ገዳ፣ እናቴ፣ ወንድሞቼና እህቶቼ በጥናቱ ወቅት እና ከዚያም በፊት በነበሩት የትምህርት ጊዜያት ላደረጉልኝ ከፍተኛ የሞራልና የማቴሪያል ድጋፍ ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡*

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት አላማ ያደረገው በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ በጂማ ዞን በጢሮ አፈታ ወረዳ የዲምቱ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ለመማር ያላቸው ፍላጎትና የውጤት ተዛምዶን መፈተሽ ላይ ነው፡፡ የተማሪዎቹን የማንበብ ክሂል ወጤታማነት ለመፈተሽ በዚህ ጥናት አንብቦ የመረዳት ክሂልን በመውሰድ በቅድመ እና ድህረ-ትምህርት ፈተና ላይ የተመረኮዘ መረጃ ትንተና ላይ ያተኮረ በመሆኑ ከፊል ፍትነታዊ የጥናት ንድፍን ተከትሏል፡፡ ጥናቱ በልማዳዊ ማስተማሪያ ዘዴና በፍላጎት ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዘዴ የሚማሩ የቁጥጥርና የሙከራ ቡድኖችን በመውሰድ በቅድመ-ትምህርትና ድህረ-ትምህርት ላይ ያተኮረ መረጃ በመሰብሰብ መተንተንን ያለመ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ዕድል ሰጭ የንሞና ዘዴን በመጠቀም የተመረጡት ሁለት መማሪያ ክፍሎች 9B እና 9E መማሪያ ክፍሎች ሲሆኑ፤ ቀጥሎ በተማሪዎቹ መካከል ሊኖር የሚችለው የተለያየ የመረዳት ባህሪ ተላውጦ በጥናቱ ውጤት ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ተጽእኖ ለመቆጣጠር ሲባል አንጻራዊ ተመሳሳይ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች የጥናቱ ተሳታፊ ማድረግ በማስፈለጉ በ9B እና 9E ክፍሎች ከሚገኙ አርባ አርባ ተማሪዎች መካከል 25 25 ተማሪዎችን በቅድመ-ትምህርት ፈተና በማጣራት በእጣ መሰረት የሙከራና የቁጥጥር ቡድን ሆነዋል፡፡ ለሙከራና ቁጥጥር ቡድኑ የቀረቡ የቅድመ-ትምህርትና ድህረ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተናዎችና ከሙከራ ቡድኑ በቅድመ እና ድህረ-ትምህርት የተሰበሰቡ የፍላጎት መለኪያ የጽሁፍ መጠይቅ ምላሾች በመረጃ መሰብሰቢያነት አገልግለዋል፡፡ የጥናቱ ውጤት እንዳመለከተው ፍላጎት ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ ልዩ ልዩ ብልሃቶች በአግባቡ በሚተገበሩበት አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ ክፍል  ተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ውጤታቸው መሻሻል እንዲያሳይ ጉልህ ጠቀሜታ እንዳለው የዚህ ተግባራዊ ጥናት ግኝት አመላክቷል፡፡ የፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ (Pearson Correlation coefficient) ተሰልቶ ($P = 0.204$, $\alpha = 0.05$) ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም በተጠኚዎቹ የአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤትና በፍላጎት የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ አማካይ ውጤት መካከል በስታቲስተካዊ መገመቻ ጉልህ እንዲሁም ቀጥተኛ አዎንታዊ ተዛምዶ መኖሩን ያሳያል፡፡ በዚሁ መሰረት የኦሮምኛ ቋንቋ አፈ-ፈት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል ያላቸው ፍላጎት ከአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤታቸው ጋር ጠንካራ አዎንታዊ ተዛምዶ ያለው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

**የማረጋገጫና የጥናቱ አጽዳቂዎች ውሳኔ መስጫ ፎርም**

**የጥናቱ ርዕስ፡-** በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂልን ለመማር ያላቸው ፍላጎትና የውጤት ተዛምዶ

**ማረጋገጫ፡-**

እኔ ከዚህ በታች የፈረምኩ ይህ በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር የሁለተኛ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ ግዴታዎች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት የራሴ የጥናት ውጤት የሆነ፣ ከዚህ ቀደም በየትኛውም ዩኒቨርሲቲ ለመመረቂያ ጽሁፍነት ያልቀረበ፣ በጥናቱ ውስጥ የተካተቱ ምንጮች ሁሉ በተገቢው መንገድ እውቅና ተሰጥቷቸው የቀረቡ መሆናቸውን አረጋግጣለሁ፡፡

እታገኑ ጌታቸው ____________________ ____________________

**የጥናቱ አጽዳቂዎች ውሳኔ**

**የጥናቱ አማካሪዎች**

ጥበቡ ሽቴ (ዶ/ር) ____________________ ____________________

ለማ ንጋቱ (ዶ/ር) ____________________ ____________________

ስም ፊርማ ቀን

**የጥናቱ ገምጋሚዎች**

------------------------------- ---------------- -----------------

የዉስጥ ገምጋሚ ስም ፊርማ ቀን

---------------------------- ----------------- --------------

የዉጭ ገምጋሚ ስም ፊርማ ቀን

# ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**

ምስጋና......iii
አጠቃሎ......iv
የማረጋገጫና የጥናቱ አጽዳቂዎች ውሳኔ መስጫ ፎርም......v
ማውጫ......vi
የሰንጠረዥ ማውጫ...... ix

**ምዕራፍ አንድ፤ መግቢያ**......1
1.1 የጥናቱ ዳራ......1
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት......4
1.3 የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች......7
1.4 የጥናቱ አላማዎች......7
1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ......8
1.6 የጥናቱ ወሰን......8
1.7 የቁልፍ ቃላት ተግባራዊ ብያኔ......9

**ምዕራፍ ሁለት፤**ክለሳ ድርሳናት......10
2.1 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት......10
2.1.1 የፍላጎት ምንነትና ጽንሰ ኃሳባዊ መሰረቶች......10
2.1.2 የፍላጎት ተኮር ትምህርት አስፈላጊነት......14
2.1.3 ፍላጎት ተኮር ትምህርትን ለመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የማቅረብ ጠቀሜታ......16
2.1.4 የፍላጎት አይነቶች......18
2.1.5 የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ለመጠበቅ የሚረዱ ብልሃቶች......19
2.1.6 የመማር ፍላጎትና ውጤታማነት ግንኙነት...... 22
2.1.7 በቋንቋ መማሪያ አውድ ፍላጎትን በተማሪዎቹ ዘንድ ለማስረጽ የቋንቋ መምህራንሚና.... 25
2.1.7.1 ተማሪዎቹ የቋንቋ መማር አስተሳሰብ እንዲያዳብሩ ማድረግ......26
2.1.7.2 ተማሪዎች በእውቀትና ክህሎት ሊደርሱበት የሚገባ ፍላጎትን በውስጣቸው ማስረጽ......26
2.1.7.3 ተማሪዎች የሚደረስባቸው የቋንቋ መማር ግቦችን እንዲያስቀምጡ ማበረታታት......27
2.1.7.4 ተማሪዎች በራስ የመተማመን ስሜት እንዲገነቡ ማበረታታት......27

2.1.7.5 በመምህሩና በተማሪዎች መካከል አዎንታዊ ግንኙነት መፍጠር……………..28
2.1.7.6 የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ለማንሰራራት የሚረዱ አዳዲስ የማስተማሪያ ብልሃቶችን መተግበር……………………………………………...............................28
2.1.7.7 የተለያዩ ቋንቋ ነክ ተግባራትን መገልገል……………………………………...31
2.1.7.8 ለተማሪዎች እውቅና መስጠትና መሸለም………………………………………31
2.1.8 ማበረታቻን ለቋንቋ መማር ፍላጎት ግብአት የማድረግ ጠቀሜታ…………………31
2.2 የፍላጎት ንድፈ-ሀሳባዊ መሰረቶች........................................................................33
2.3 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት………………………………………..............................36

**ምዕራፍ ሦስት፤** የጥናቱ ንድፍ እና የአጠናን ዘዴ……………………………………39
3.1 የጥናቱ ንድፍ…………………………………………………………………………….39
3.2 የጥናቱ አካላይ……………………………………………………........................39
3.3 የናሙና አመራረጥ ዘዴ…………………………………………………….............39
3.3.1 የወረዳ አመራረጥ…………………………………………………………...............39
3.3.2 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ……………………………………………………40
3.3.3 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ……………………………………………………….40
3.3.4 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ…………………………………………………………40
3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች………………………………………………………41
3.4.1 የችሎታ መለኪያ ፈተና…………………………………………………………….....41
3.4.2 የጽሑፍ መጠይቅ……………………………………………………………..............43
3.5 የትምህርቱ አቀራረብና የማስተማሪያ መሳሪያ ዝግጅት.........................................44
3.5.1 የትምህርቱ አቀራረብ.........................................................................................44
3.5.2 የማስተማሪያ መሳሪያ ዝግጅት.............................................................................44
3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ…………………………………………………………………….45

**ምዕራፍ አራት፤** የመረጃ ትንተና እና የውጤት ማብራሪያ………………………………47
4.1 የጥናቱ ውጤት…………………………………………........................................48
4.2 የትንተናው ውጤት ትርጎማ……………………………………..........................63

**ምዕራፍ አምስት፤** ማጠቃለያና የመፍትሄ ሐሳቦች አስተያየት.......................................68

5.1 የጥናቱ ማጠቃለያ.......................................................................68
5.2 የመፍትሄ ሐሳቦች ጥቆማ................................................................69

ዋቢዎች..........................................................................................71
አባሪዎች........................................................................................76

## የሰንጠረዥ ማውጫ

**የሰንጠረዥ ርእስ** **ገጽ**

ሰንጠረዥ 1፡- የሙከራው እና የቁጥጥሩ ቡድኖች የቅድመ-ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና አማካይ ውጤቶች የገላጭ ስታትስቲክስ ንጽጽር......................................48

ሰንጠረዥ 2፡- የሙከራው እና የቁጥጥሩ ቡድኖች የቅድመ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና አማካይ ውጤቶች የነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ንጽጽር...............................49

ሰንጠረዥ 3፡- የሙከራው እና የቁጥጥሩ ቡድኖች ድህረ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና አማካይ ውጤቶች የገላጭ ስታትስቲክስ ንጽጽር .....................................50

ሰንጠረዥ 4፡- የሙከራው እና የቁጥጥሩ ቡድኖች የድህረ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና አማካይ ውጤቶች የነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ንጽጽር .............................52

ሰንጠረዥ 5:- የሙከራው ቡድን የቅድመ-ትምህርትና ድህረ-ትምህርት አንብቦ መረዳት ፈተና አማካይ ውጤቶች የገላጭ ስታትስቲክስ ንጽጽር......................................53

ሠንጠረዥ 6፡- የሙከራው ቡድን ቅድመ-ትምህርትና ድህረ-ትምህርት አንብቦ መረዳት ፈተና አማካይ ውጤቶች የዳግም ልኬት ናሙናዎች ቲ-ቴስት ንጽጽር ................54

ሰንጠረዥ 7:- የቁጥጥር ቡድኑ የቅድመ-ትምህርትና ድህረ-ትምህርት አንብቦ መረዳት ፈተና አማካይ ውጤቶች የገላጭ ስታትስቲክስ ንጽጽር.......................................55

ሰንጠረዥ 8፡- የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ-ትምህርትና ድህረ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና አማካይ ውጤቶች የዳግም ልኬታ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ንጽጽር ...............56

ሰንጠረዥ 9፡- የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በፍላጎት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ ላይ ያላቸው ፍላጎት ቅድመ እና ድህረ-ትምህርት የጽሑፍ መጠይቅ አጠቃላይና አማካይ ውጤት የገላጭ ስታትስቲክስ ንጽጽር ......................................................................57

ሰንጠረዥ 10፡- የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በፍላጎት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ ላይ ያላቸው ፍላጎት ቅድመ እና ድህረ-ትምህርት የጽሑፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት ልዩነት በዳግም ልኬት ናሙናዎች ቲ-ቴስት.................................................................58

ሰንጠረዥ 11፡- የሙከራ ቡድኑ ተጠኚዎች የቅድመ እና ድህረ-ትምህርት ለፍላጎት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴው ተላውጦዎች የሰጧቸው የጽሁፍ መጠይቅ ምላሾች የገላጭ ስታቲስቲክስ ንጽጽር.........................................................................................60

ሰንጠረዥ 12፡- የሙከራ ቡድኑ ተጠኚዎች የቅድመ እና ድህረ-ትምህርት ለፍላጎት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴው ተላውጦዎች የሰጧቸው የጽሁፍ መጠይቅ ምላሾች የዳግም ልኬት ናሙናዎች ቲ-ቴስት ንጽጽር..........62
ሰንጠረዥ 13፡- የፒርሰን የተዛምዶ ልኬት..........63

# ምዕራፍ አንድ፤መግቢያ

## 1.1 የጥናት ዳራ

የቋንቋ ትምህርት በተለይም የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት በብዙ ተጽዕኖ አድራሽ ተላውጦዎች የተከበበ ነው፡፡ የተጽዕኖ አድራሾቹ ጣልቃገብነት በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርቱ ላይ ጎልቶ የሚታይበት ምክንያትም የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ተወልደው ካደጉበት፣ ከለመዱት ቋንቋና ባህል ወጣ ብለው ከተለየ ቋንቋና ባህል ጋር ለመላመድ በሚያጋጥሟቸው ስነልቦናዊ ችግሮች ምክንያት የተነሳ ነው Brown (1994)፡፡ ሁለተኛ ቋንቋን የመማር ሂደት የራስ ያልሆነን አዲስ የአሰራርና የአኗኗር ስርዓት የመልመድ ሂደት ነው፡፡ የሌሎችን ሰዎች አሰራር፣ ባህል፣ ወግ፣ እምነትና ስርዓት የመቀበል ግዴታን በራስ ላይ ማምጣት ነው፡፡ ምክንያቱም ማንኛውም ተማሪ ሁለተኛ ቋንቋን ሲማር የሚማረውን ቋንቋ ስርዓት፣ ወግና ባህል መከተል ይችል ዘንድ በተወሰነ መልኩ የራሱን ቋንቋ ስርዓት፣ ወግና ባህል የመተው ግዴታ ውስጥ ይገባል፡፡ ለዚህ ደግሞ የተማሪው ፍላጎት መኖር አስፈላጊ ነው (Brown 2000)፡፡

የመማር ማስተማር ሂደቱ ውጤታማ ይሆን ዘንድ ተማሪዎች ትምህርቱን ለመማር ያላቸው ፍላጎት ወሳኝነት አለው፡፡ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ማጥናት የተማሪዎችን ስነልቦናዊ ችግሮች በማቃለል ውጤታማ የሚሆኑበትን ሁኔታ ከማመቻቸት አንጻር ከፍ ያለ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ላይ ተጽዕኖ ከሚያደርሱ ተላውጦዎች መካከል ለመማር ማስተማር ሂደቱ የሚኖር አመለካከትና ፍላጎት ግንባር ቀደም ተጠቃሽ መሆኑን Gardner, et al., 2004) ያስረዳሉ፡፡

Willson (1971)፣ Hawit (1967)ን ጠቅሰው እንደሚያስረዱት ፍላጎት አንድን ነገር ለመተግበር ትኩረት የሚሰጥበት፣ እንዲሁም አንድን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚረዳ ውስጣዊ ግፊት፣ ዝንባሌና ስሜት ነው፡፡ አንድ ሰው አንድን ነገር ለማከናወን ትኩረት ሰጥቶና እራሱን እያዘጋጀ እያለ እንዳያከናውን በሚከለከልበት ጊዜ የብስጭት ስሜትን ሊፈጥር የሚችል ሃይል ነው በማለት ይገልጹታል፡፡

Hamlin (1996) በበኩላቸው አንድን ድምጽ እንደሰማን ማዳመጥ እንጀምራለን፤ ከዛም ስለጉዳዩ በማስተዋልና የልብ ትርታችን በፍጥነት እየመታ እናስባለን፤ በመጨረሻም ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥተን ከልብ ማዳመጥና የሚደመጠውንም በማስተዋል ሙሉ በሙሉ በስሜት በመዋጥ ስለጉዳዩ እናስባለን፡፡ ይህ የማሰብ ስሜት ፍላጎት ይባላል በማለት ያስረዳሉ::

Tarin (1997) ፍላጎት ማለት አንድ ግለሰብ ስሜቱንና ዝንባሌውን የሚገልጽበት መንገድ ነው፡፡ እንዲሁም የአንድን ነገር ምንነት ለማወቅ ትኩረት ሰጥቶ እንዲመለከት የሚገፋፋ ሃይል ነው፡፡ ይህም አንድን ነገር እንድንወደው ወይም እንድንጠላው የሚያደረግ ንቃተ ህሊናዊ ስሜት ነው በማለት ይገልጻሉ፡፡ በሌላ በኩል Skiner (1985)ን በመጠቀስ William (1990) እንደገለጹት፣ ፍላጎት የታቀደ ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚከናወንን ተግባር

መውደድና አለመውደዳችንን የሚያመለክት ውስጣዊ ተነሳሽነትና ለተፈለገ ነገር ትኩረት እንድንድንሰጥ የሚያደርግ ግፊት፣ ዝንባሌና ስሜት ነው በማለት ይገልጻሉ፡፡

በአጠቃላይ ከምሁራኑ ሃሳብ መረዳት እንደሚቻለው ፍላጎት ማለት በአንድ ነገር ለመሳብ ወይም ለመገፋት ምክንያት የሚሆን ውስጣዊ ስሜት ሲሆን አንድን ነገር ከመውደድና ከመጥላት ጋር በተያያዘ ለመምረጥ ወይም ላለመምረጥ ምክንያት ሊሆን የሚችል ህሊናዊ ውሳኔ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ተማሪው ለትምህርቱ አዎንታዊ ፍላጎት ሊኖረው ይገባል። ለመማር ፍላጎት የሌለው ከሆነ ትምህርቱን ፈጽሞ ሊማር አይችልም፤ ስለዚህ አንድን የትምህርት አይነት ለማስተማር በምንነሳበት ጊዜ ተማሪው ለሚማረው ትምህርት የሚኖረው ፍላጎት አስቀድሞ ሊታወቅ ይገባል፡፡ ፍላጎት ካለው ትምህርቱን በሚገባ መከታተል ይችላል፡፡ ፍላጎት የሌለው ተማሪ ግን ትምህርቱን በተገቢው መንገድ መከታተል አይችልም (Bugals1971)፡፡

ፍላጎት የሌለውን ተማሪ እንዴት? መለየት ይቻላል የሚለውን Guaraider (1985) ሲያስረዱ ተማሪው የሚሰጠውን ትምህርት በሚገባ የማይከታተል ከሆነ፣ ትምህርቱ ሲሰጥ ከልብ የማያዳምጥና በትክክል መረዳት የማይችል ከሆነ አብዛኛውን ጊዜ ተማሪው የመማር ፍላጎት የሌለው መሆኑን ያመላክታል፡፡ ተማሪው በሚሰጠው ትምህርት ምንም ፍላጎት የሌለው ከሆነ ደግሞ የመማር ማስተማሩ ተግባር አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ተማሪው ለሚሰጠው ትምህርት ፍላጎት እንዲኖረው የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ ፍላጎት የሌለውን ተማሪ ማስተማርም በክፍል ውስጥ የሌለን ተማሪ እንደማስተማር ይቆጠራል፡፡ በአጠቃላይ ተማሪው ስለሚማረው ትምህርት ፍላጎት ከሌለው የሚሰጠውን ትምህርት ትኩረት ሰጥቶ ለመከታተል አይነሳሳም፤ ተነሳሽነት ደግሞ ከፍላጎት ጋር ጥብቅ ተያያዥነት ያለው መሆኑን ያሳያል፡፡

ተማሪዎች በተማሩት ትምህርት መሰረት ምን ያህል ዕውቀት እንደቀሰሙና የተማሪዎች ግንዛቤ ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅና የታቀደው የተማሪዎች የባህሪ ለውጥ መምጣቱን ለማረጋገጥ በአጠቃላይ የትምህርቱ ዓላማዎች መሳካታቸውን ለመፈተሸ የተለያዩ ፈተናዎች ይሰጣሉ፡፡ በዚህም የተማሪዎች የትምህርት ውጤት ምን ያህል እንደሆነ ይመዘናል (Brown 2003)፡፡ የቋንቋ ትምህርት ውጤት ከአንድ የቋንቋ ትምህርት የመማር ሂደትና ወቅት በኋላ በሚዘጋጅና ለተማሪዎች በሚሰጡ ተከታታይ ምዘናዎች አማካኝነት ሊለካ የሚችል መሆኑን Huges (2003) ያስረዳሉ፡፡

በተማሪዎች የቋንቋ ትምህርትና ውጤት ላይ ተፅዕኖ ከማድረስ አንጻር በትምህርት ቤት ውስጥና ከትምህርት ቤት ውጪ የሚኖሩ የተጽዕኖ አከፋፈሎች እንዳሉ የሚያስረዱ ምሁራን አሉ፡፡ ውስጣዊ የሚባሉት ተማሪው በሚማርበት ትምህርት ቤት ውስጥ ሊገኙ

የሚችሉ ሲሆኑ የትምህርት ቤቱ አካባቢ፣ የመምህራን ማንነት፣ የትምህርት መሳሪያዎች ሁኔታ፣ የመመዘኛ መስፈርቶች፣ የትምህርት አሰጣጥ ሁኔታ፣ በትምህርት ቤቱ የሚገኙ የተለያዩ የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከላትና የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡ ውጫዊ የሚባሉት ደግሞ ከትምህርት ቤት ውጪ ሊኖሩ የሚችሉ የቤተሰብና የማህበረሰብ ባህላዊ ዳራዎች፣ የተለያዩ እምነቶችና አጠቃላይ ተማሪው የሚኖርበት ህብረተሰብ አስተሳሰቡና ልማዱ የሚሉ ሲሆኑ፤ እነኚህ ውጫዊ የተባሉት ሁኔታዎች በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ በተማሪዎች የቋንቋ ትምህርትና በሚያስመዘግቡት ውጤት ላይ ተፅዕኖ ማሳደራቸው አይቀርም፡፡

እንደ Scohon (1986) አገላለጽ ተማሪዎች ትምህርታቸውን በከፍተኛ ፍላጎት እንዲማሩና ጉጉት እንዲያድርባቸው በቅድሚያ ለሚማሩት ትምህርት አዎንታዊ የሆነ ፍላጎት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ የተማሪዎች ፍላጎት ከሚማሩት ርዕሰ ጉዳይ ጋር የሚገናኝ ከሆነ ደግሞ ቀደም ብሎ ካላቸው እውቀት ጋር አያይዘውና አዋህደው እንዲገነዘቡትና በቀላሉ መረዳት እንዲችሉ ይረዳቸዋል፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች የመማር ፍላጎት ካላቸው እየተሰጠ ያለውን ትምህርት በቀላሉ ሊረዱትና ሊያውቁት ከመቻላቸውም በላይ የተማሩትን ለረዥም ጊዜ በአዕምሯቸው ይዘው እንዲቆዩ፣ በተማሩትና በሚያነቡት ሁሉ እንዲደሰቱ፤ ጥሩ ልምድና ተግባር እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

በርካታ ልማዳዊ የማስተማሪያ ሞዴሎች የተማሪዎችን የመማር ፍላጎቶች ያላከበሩና ትምህርታዊ መረጃዎችን በማዳመጥ ብቻ እንዲቀበሉ የማድረግ ውሱንነቶች የነበሩባቸው ናቸው፡፡ ይህም ተማሪዎችን አዳማጭ ከማድረግ የዘለለ ተማሪዎቹ የሚማሩትን ይዘት ለማስታወስ፣ ለመመርመር፣ ከቀደሙ ልምዶቻቸውና ገጠመኞቻቸው ጋር ለማዛመድና ለማገናዘብ ጠቀሜታ ያልነበራቸው ናቸው (McCarthy, 2014)፡፡ ይህም አዳዲስ የማስተማሪያ ሞዴሎች በየጊዜው እየተፈጠሩ በተግባር እንዲፈተሹ ምክንያት የሆነ ሲሆን፤ በተለይ ፍላጎት ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ ለሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ አውድ ሰፊ አስተዋጽኦ ያለው ውጤታማ ሞዴል ነው (Renninger, Hidi and Krapp, 2012፣ 16-17)፡፡ በአጠቃላይ ፍላጎት የትምህርትን የመጨረሻ ግብ ለማሳካት ከፍተኛ ሚና አለው፡፡ ተማሪዎች ትምህርቱን በትኩረት እንዲከታተሉትና የሚሰጠውን ተግባር በአግባቡ እንዲያከናውኑ ፍላጎታቸውን ማነሳሳት

ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም ፍላጎት ከሌለ የመማር ማስተማሩን ሂደት በተገቢው መንገድ ማካሄድም ሆነ በስርዓተ ትምህርቱ የተቀረጸውን ግብ ማሳካት አዳጋች ያደርገዋል።

አንድ ሰው ብዙ ቋንቋዎችን አጣርቶ ማወቁ ልሳነ ብዙ ያደርገዋል፡፡ ይህም ለተግባቦቱ፣ ለማህበራዊ ግንኙነቱ ካለው መሰረታዊ ጠቀሜታ ባሻገር በተለያዩ ቋንቋዎች የመጻፍ፣ የማንበብ፣ የማዳመጥና የመናገር ችሎታውን ከፍ ያደርግለታል፡፡ በተለያዩ አካባቢዎች ተንቀሳቅሶ የመስራት አማራጩን ያሰፋለታል ተብሎም ይታሰባል፡፡ በዚህ የተነሳ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ በቋንቋ ፖሊሲ በተደገፈ መልኩ በአካዳሚኩ መስክ ተማሪዎች ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በተጨማሪ የሐገሪቱን የስራ ቋንቋና እንግሊዝኛን እንዲማሩ እየተደረገ ይገኛል (MOE 1994)፡፡ ስለሆነም ይህ ጥናት በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን ለመማር ያላቸውን ፍላጎትና የውጤት ተዛምዶን የሚመረምር ይሆናል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አንድ ተማሪ በቋንቋ ትምህርት ሂደቱ ውስጥ የሚኖረው ፍላጎት በሚያስመዘግበው የቋንቋ ትምህርት ውጤት፣ የመማር ተግባራቱ፣ በመማር ማስተማር ሂደቱ ውስጥ ሊመለከታቸውና ሊያሻሽላቸው በሚችላቸው ጉዳዮች ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትን የመማር ፍላጎትና በትምህርቱ ውጤታማ መሆን አለመሆን ጋር በተገናኘ በተለያየ ጊዜ በተለያዩ ተመራማሪዎች፣ በተለያዩ አካባቢዎችና በተለያዩ ቋንቋዎች ላይ ምርምሮች ተካሂደዋል፡፡

ከእነዚህ መካከልም Sufi (2009) በተማሪዎች ፍላጎትና በእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት መካከል ያለው ዝምድና ምን ይመስላል? በሚል በጃካርታ ሽሪፍ እስላሚክ ስቴት ዩኒቨርስቲ ባካሄዱት ጥናት በተማሪዎች ፍላጎትና በትምህርት ውጤታቸው መካከል ጉልህ ተዛምዶ ያለ መሆኑን አሳይተዋል፡፡ በዚህም እንግሊዝኛ ቋንቋን ለመማር ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች በትምህርቱ በሚያስመዘግቡት ውጤት ተጽዕኖ የሚያደርስበት መሆኑንና ፍላጎትና ውጤታማነት የርስበርስ ቁርኝት እንዳላቸው፤ ዝቅተኛ ፍላጎት ዝቅተኛ ውጤትን፤ ዝቅተኛ ውጤትም መልሶ ዝቅተኛ ፍላጎትን እንደሚያስከትል አመላክተዋል፡፡

Coler and Jergun (2001) በተማሪዎች ፍላጎትና በሂሳብ ትምህርት ውጤታማነት መካከል ተዛምዶ ይኖር ይሆን? በሚል በጀርመን ሚችጋን ዩኒቨርስቲ ባካሄዱት ጥናት በፍላጎትና በውጤታማነት መካከል ጉልህ ዝምድና (ተጽዕኖ) የለም፤ ነገር ግን ፍላጎት በትምህርት ዓይነት (በኮርስ ምርጫ) ላይ ተጽዕኖ እንደሚየሳድር አሳይተዋል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም ውጤታማነት በፍላጎት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር ሲሆን ውጤታማ የሆኑ ተማሪዎች በትምህርቱ ላይ የሚኖራቸው ፍላጎት ከደካማ ተማሪዎች የተሻለ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

በተመሳሳይም Alfayzah, Noro and Camnun (2020) በተማሪዎች ፍላጎትና አጫጭር ምንባቦችን አንብቦ በመረዳት ችሎታ መካከል ያለውን ተዛምዶ ለመመርመር በኢስላም

ኒጅሪይ የአልሁዱን ማካሳር ዩኒቨርስቲ በጎዋ ሁለተኛ ደረጃ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ በካሄዱት ምርምር ዝቅተኛ ተዛምዶ ያለው መሆኑን አሳይተዋል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡትን ጥናቶች ስንመለከታቸው ሁለተኛ ቋንቋን በመማር ፍላጎትና በትምህርት ውጤታማነት ላይ አተኩረው የተካሄዱ ቢሆንም ሁሉንም በጋራ የሚያስማሙ ግኝቶች አሉ ማለት ግን አያስደፍርም፡፡ ከዚህም የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ስኬትን በተመለከተ አሁንም በፍላጎትና በውጤት መካከል ተዛምዶ ላይ ምርምር ማካሄድ አስፈላጊ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

የሀገር ውስጥ ጥናቶችን ስንመለከትም አጥኝዋ ባደረገችው አሰሳ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩ ተማሪዎች ፍላጎትና በትምህርት ውጤታቸው መካከል ያለውን ተዛምዶ የፈተሹ ጥናቶች አላገኘችም፡፡ ሆኖም ግን በቀጥታ ፍላጎት ላይ ባይሆንም አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩ ተማሪዎች ተነሳሽነትና በትምህርት ውጤታቸው መካከል ያለውን ተዛምዶ የፈተሹ አለምነሽ (2001)፣ ክፍሌ (2002)፣ (ማረውና ዘሪቱ 2009) የሚሉ ጥናቶችን አግኝታለች፡፡ አጥኝዎቹ በምርምራቸው በተነሳሽነትና በውጤት መካከል ጉልህ ተዛምዶ ያለ መሆኑንም አሳይተዋል፡፡

የመማር ፍላጎት፣ የቋንቋ ችሎታና ውጤት እንደየቋንቋዎች ባህላዊ ዳራና ባህሪያት ልዩነት የሚያሳይ መሆኑን Parado (2004) ያስረዳል፡፡ የመማር ፍላጎት ባላቸው አካባቢዎች በሚገኙ ባህሎች ተጽዕኖ እንደሚደርስበትና ይህም በትምህርት ውጤታቸው ላይ ሊንጸባረቅ እንደሚችል አስረድተዋል፡፡ የተማሪዎች የቋንቋ መማር ፍላጎት ከተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት ውጤትና የቋንቋ ችሎታ ጋር ያላቸውን ተዛምዶ አስመልክቶ በአንድ የተለየ ቋንቋዊ ዳራና ባህላዊ ይዘት ባለው የተወሰነ አካባቢ ውስጥ በተከናወነ ጥናታዊ ስራ አማካኝነት የተገኘን ውጤት በአንድ ሌላ የተለየ ቋንቋዊ ዳራና ባህላዊ ይዘት ላለው አካባቢ ተመሳሳይ ውጤት አለው ወይም ሊኖረው ይችላል የሚል ድምዳሜ ላይ ሊያደርስ እንደማይችል ይታመናል፡፡ ይህ ማለት የየራሳቸው የሆኑ ቋንቋዊ ዳራና ባህል ባላቸው አካባቢዎች ውስጥ የተማሪዎች የቋንቋ መማር ፍላጎት ለተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት ውጤት የሚኖራቸው ሚና ልዩ እንዲሆን የሚያደርጉ አካባቢ ተኮር ተላውጦዎች ይኖራሉ ማለት ነው፡፡ ስለሆነም ይህ አካባቢ ተኮር ልዩነት ተጨማሪ ጥናት እንዲደረግ የሚጠቁም ነው፡፡

ይህ ጥናት በፍላጎትና በቋንቋ ትምህርት ላይ ስላተኮረ ከላይ ከተጠቀሱት የውጭ አገር ጥናቶች ጋር ሙሉ በሙሉም ባይሆን በከፊል ይመሳሰላል፡፡ በተመሳሳይም የአገረኛ ጥናቶቹ በቀጥታም ባይሆን በተዘዋዋሪ መልኩ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች ቋንቋውን የመማር ተነሳሽነትና የውጤት ተዛምዶ ላይ ስላተኮሩ ይመሳሰላሉ፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ጥናት በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በጥናቱ ተሳታፊዎች አፍ መፍቻ ቋንቋ፣ የክፍል ደረጃ፣ በመገኛ አካባቢ፣ ጥናቱ በተካሄደበት ጊዜ፣ በጥናቱ ተላውጦዎች ብዛት ከላይ ከቀረቡት የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ጥናቶቹ ይለያል፡፡

በተጨማሪም አጥኚዋ ካላት የማስተማር ተሞክሮ መረዳት እንደቻለችው ጥናቱ በሚካሄደበት አካባቢ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ የአብዛኞቹ ተማሪዎች ውጤት ዝቅተኛ ነው፡፡ ይህም ምናልባት ለውጤታቸው መቀነስ አንደኛው ምክንያት ፍላጎት

ይሆን? የሚል ጥያቄ እንድታነሳ አድርጓታል፡፡ ከዚህም ባሻገር ኢ-ቀጥተኛ በሆነ መልኩ ከአማርኛ ቋንቋ መምህራን ጋር ባደረገቻቸው ውይይቶች መረዳት እንደቻለችው የተማሪ ወላጆች ልጆቻቸው የአማርኛ ቋንቋን እንዲማሩ ያን ያህል ድጋፍ የሌላቸው መሆኑ በተማሪዎቹ ታላሚውን ቋንቋ መማር ፍላጎት ላይ ተጽእኖ ይኖረው ይሆን የሚለው ሁኔታም ለዚህ ጥናት መካሄድ አነሳሽ ምክንያት ነው፡፡

አጥኝዋ ከዚህ በላይ በተጠቀሱት መነሻ ሃሳቦች ላይ በማተኮር በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ለመማር ያላቸውን ፍላጎትና የውጤት ተዛምዶን ለማጥናት ተነሳስታለች፡፡ ይህን ከፊል ፍትነታዊ ጥናት ለማካሄድ አጥኚዋ የመረጠችው የማንበብ ክሂልን ነው፡፡ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት የጋለ የማንበብ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ብዙ ነገሮችን ለመረዳት ስለሚሹ ለመማር ያላቸው ተነሳሽነት እንዲንሰራራ ያደርጋል፡፡ በዚህ ምክንያት ማንበብ የተማሪዎችን የማወቅ ፍላጎት፣ የቃላት እውቀት፣ የመጻፍ ተነሳሽነት ያሳድጋል፡፡ አጠቃላይ የመማር ፍላጎታቸውን ለመንከባከብና ለማጎልበት ጠቀሜታ ይኖረዋል (Willemse Lunenberg & Korthagen, 2005) ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

### 1.3 የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች

1. የኦሮምኛ ቋንቋ አፈ-ፈት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል ያላቸው ፍላጎት በውጤታቸው ላይ ተጽዕኖው ምን ይመስላል?
2. የኦሮምኛ ቋንቋ አፈ-ፈት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፍላጎት ለማሻሻል በሚረዱ ብልሃቶች ትግበራ ያላቸው ምላሽ ምን ይመስላል?

### 1.4 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በጅማ ዞን ጢሮ አፈታ ወረዳ በዲምቱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ የኦሮምኛ አፈ-ፈት ተማሪዎች አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ የመማር ፍላጎትና በትምህርቱ ውጤት መካከል ዝምድና መኖር አለመኖሩን መመርመር ሲሆን ንዑሳን ዓላማዎቹም የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. የኦሮምኛ ቋንቋ አፈ-ፈት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል ያላቸው ፍላጎት በውጤታቸው ላይ ተጽዕኖው ምን እንደሚመስል መፈተሽ፤
2. የኦሮምኛ ቋንቋ አፈ-ፈት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፍላጎት ለማሻሻል በሚረዱ ብልሃቶች ትግበራ ያላቸው ምላሽ ምን እንደሚመስል መመርመር ናቸው፡፡

## 1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን የመማር ፍላጎትና በትምህርቱ ውጤት መካከል ያለውን ተዛምዶ በመለየት የመፍትሄ ሃሳቦችንና አስተያየቶችን ከማስቀመጥ አንጻር ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጠቀሜታዎች ያስገኛል ተብሎ ይታሰባል፡፡

1. የማስተማሪያ መሳሪያዎችን ለሚያዘጋጁ አካላት ስለተማሪዎች ፍላጎትና ስለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መሰጠት ስላለበት ትኩረት ጥቆማ ይሰጣል፡፡
2. በተማሪዎች የመማር ፍላጎትና በትምህርቱ ውጤት መካከል ያለውን ዝምድና በማሳየት መምህራን የመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ ለውጥ ማምጣት እንዲችሉ እንደግብዓት በመሆን ሊያግዝ ይችላል፡፡
3. የአማርኛ ቋንቋን በመማር ሂደት ውስጥ ዝቅተኛ ፍላጎትና ውጤት ላላቸው ተማሪዎች መምህራን አስፈላጊ እገዛና ማነቃቂያ መስጠት እንዲችሉ ሊረዳ ይችላል፡
4. ተማሪዎች ስለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸውን ፍላጎትና በትምህርቱ ያላቸውን ውጤታማነት እንዲገነዘቡት በማድረግ ወደፊት ምን ማድረግ እንዳለባቸው ጥቆምታ ይሰጣል፡፡
5. ወደፊት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፍላጎትና በትምህርቱ ውጤት መካከል ስላለው ዝምድና ላይ በጥልቀትና በስፋት ጥናት ማካሄድ ለሚሹ ተመራማሪዎች በመነሻነት ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ከቦታ አንጻር በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በጅማ ዞን ጢሮ አፈታ ወረዳ ከሚገኙ የአኮ፣ ገበራ፣ ራጋ፣ ዲምቱ እና ጌሼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በዲምቱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ብቻ የተወሰነ ነው፡፡ በተመረጠው ትምህርት ቤት ውስጥ በ2013 ዓ.ም በዘጠነኛ ክፍል ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ የሚገኙ በኦሮምኛ ቋንቋ አፈ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች የጥናቱ ተሳታፊዎች ናቸው፡፡ ጥናቱ ከይዘት አንጻር የመማር ፍላጎትና የውጤት ተዛምዶንና የምክንያትና ውጤት ትስስርን የሚቃኝ ይሆናል፡፡ ይህ ጥናት ከፍላጎት ባሻገር በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ላይ ተጽዕኖ የሚያደርሱ ሌሎች ተላውጦዎችን የመፈተሽ ትኩረት የለውም፡፡ ጥናቱ ከአማርኛ ቋንቋ አራቱ አበይት ክሂሎች በማንበብ ክሂል ላይ በማትኮር በቅድመ እና ድህረ-ትምህርት ፍትነት ውጤት ላይ ያተኩራል፡፡ በዚህ ጥናት ፍላጎት ነጻ ተላውጦ (Independent Variable) ሲሆን ውጤት ደግሞ ጥገኛ ተላውጦ (dependant Variable) ነው፡፡ ምክንያቱም የተማሪዎቹ ውጤት ፍላጎት በመኖር ወይም ባለመኖር ላይ ጥገኛ በመሆኑ ነው፡፡ የሚያተኩረውም መደበኛ በሆነው የክፍል ውስጥ ትምህርት ላይ ነው፡፡

## 1.7 የቁልፍ ቃላት ተግባራዊ ብያኔ

በዚህ ጥናት ውስጥ የቋንቋ ትምህርት ፍላጎት፣ ተዛምዶና ውጤት የጥናቱ ቁልፍ ቃላት ሲሆኑ ተግባራዊ ብያኔያቸውም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሁለተኛ ቋንቋ፡- ተማሪው ከአፍ መፍቻ ቋንቋው ቀጥሎ የሚለምደውና ከአፍ መፍቻ ቋንቋው ውጪ ለመማርም ሆነ ተግባቦት ለማድረግ የሚጠቀምበት ቋንቋ ነው፡፡

**ፍላጎት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ፡-** አማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች ቋንቋውን ለመማር ያላቸው ስሜት፣ ግፊት፣ ዝንባሌና ጥረት መሰረት በማድረግ የተማሪዎቹን የተግባቦት ችግሮች ለማቃለል የሚረዳ ታላሚውን ቋንቋ የማስተማሪያ ስልት ነው፡፡

**የማንበብ ፍላጎትና ውጤት ተዛምዶ፡-** አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች በሚኖራቸው የማንበብ ፍላጎትና በሚያስመዘግቡት የፈተና ውጤት መካከል የሚኖር አዎንታዊ ወይም አሉታዊ አንብቦ የመረዳት ውጤት ግንኙነትን ያመለክታል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት፤ክለሳ ድርሳናት

## 2.1 ፅንሰ ሀሳባዊ ቅኝቶች

### 2.1.1 የፍላጎት ምንነትና ጽንሰ ኃሳባዊ መሰረቶች

የመማር ፍላጎት በመማር ሂደት ለመበረታታት ከፍተኛው አነቃቂ ሀይል በመሆን የመማር ሂደትንና ውጤታማነትን ያመቻቻል፣ በመማር ወደ ከፍታ ለማደግ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ በመሆኑም ፍላጎት በትምህርት ውጤታማ ለመሆን እጅግ አስፈላጊ ተላውጦ ነው፡፡ ፍላጎት ስነልቦናዊ በሆነ መልኩ የሚገለጽ ስለ አንድ ርእሰ ጉዳይ ያለንን ትኩረት የሚወስን ብሎም በተደጋጋሚ እንድናከናውነው ፈቃደኛነታችንንና ትኩረታችንን የሚያመቻች ወይም የሚገድብ ጉዳይ ነው (McCarthy, 2014)፡፡

የተማሪዎች ፍላጎት ለመማር ያላቸውን ተነሳሽነት የሚያበረታታና በተለያዩ ስልቶች፣ ዘዴዎች ብልሃቶችና ሞዴሎች እንዲሁም በቀደሙ የመማር ልምዶቻቸው ላይ ተደግፎ የሚቀርበውን ስርአተ ትምህርትና መርሃ ትምህርት እንዲወዱት አለያም እንዲጠሉት የማድረግ አቅምን የሚወስን፣ ስነ-ትምህርታዊ አቀራረቦችን፣ ይዘቶችንና ጽንሰ ሀሳቦችን በመረዳት ረገድ ቁልፍ ሚና ያለው ነው (McCarthy, 2014)፡፡ የተማሪዎች እሾቶች /ጥያቄዎች/ (Needs) ለትምህርት አስፈላጊ የሆኑ እንደ መማሪያ ፊደላትና ቁጥር መለየት፣ መናገርና ችግር መፍታት ባሉ መሰረታዊ ሁኔታዎች እንዲሁም የትምህርት ይዘት እውቀት፣ ክህሎት፣ ዋጋ መስጠትና አመለካከት ላይ ይመሰረታሉ፡፡ የእነዚህ መሰረታዊ ግንዛቤዎች መኖር ተማሪዎች በትምህርቱ አውድ በመማር እንዲቆዩ፣ ችሎታቸውን እንዲያበለጽጉና ለመማርና ለመስራት አስፈላጊውን አክብሮት እንዲሰጡ ያደርጋቸዋል (Omrod, 2008)፡፡

በሌላ በኩል Reid (1995) እንደገለጹት፣ የመማር ምርጫ ተማሪዎች የሚማሩትን የትምህርት ይዘት ለመረዳት ያላቸው ችሎታ ብሎም በትምህርቱ አማካኝነት የቀረበላቸውን መረጃ በማብላላት ወደ ግንዛቤነት ለመለወጥ ያላቸውን ተነሳሽነት የሚያመላክት ነው፡፡ በReid መሰረት፣ የመማር ምርጫ ተማሪዎች ያላቸውን ተፈጥሯዊ፣ ልምዳዊና ፍላጎታዊ ዳራዎች መሰረት በማድረግ እውቀት፣ ክህሎትና ልምድ የሚገበዩበት መንገድ ነው፡፡ ይህም

በተዘዋዋሪ የሚያመለክተው እያንዳንዱ ተማሪ የሚማረው ትምህርት እንዴት ቢቀርብለት የበለጠ ውጤታማ ሊያደርገው እንደሚችል የየራሱ ፍላጎት ያለው መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

በReid (1995) እንደተገለጸው የመማር ፍላጎት /ምርጫ/ ተማሪዎች ስለሚማሩት ትምህርት አቀራረብ ላይ የተያዘ ባህሪና አመለካከት ሲሆን ይህም በአንድ በተወሰነ አውድ የሚቀርበውን ይዘት የመረዳት ተነሳሽነታቸውን ብቻ ሳይሆን ውጤታማነታቸውን ለማመቻቸት ወሳኝ መነሻ ነው፡፡ እንደReid ገለጻ፣ የመማር ፍላጎት መረጃን ለመቀበል፣ ወደ ግንዛቤነት ለመቀየርና ለረጅም ጊዜ በትውስት ከማቆየት ጋር ቁልፍ ተዛምዶ አለው፡፡ ተማሪዎች ያላቸው አጠቃላይ የመማር ይዞታ የሚቀርበው ትምህርት ከሚቀርብበት ስልት ጋር የተያያዘ ሲሆን ይህም መረጃን በመቀበል በአእምሮ ለማደራጀት እንዲሁም በመረጃ የተደገፈ ውሳኔ ለመስጠትና የመማር እሴቶችን ለመገንባት አጋዥ ነው፡፡

የመማር ፍላጎት ጽንሰሀሳብ በተማሪዎች የእለት ተእለት የመማር ክንዋኔ ውስጥ ቁልፍ ድርሻ አለው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች ከሚማሩት ትምህርት ጋር በተያያዘ መረጃዎችን የሚቀበሉባቸው የየራሳቸው ልምዶችና ፍላጎቶች ይዘው ስለሚገኙ ነው፡፡ ባለንበት ዘመን የትምህርት ባለሙያዎች ተማሪዎች ትምህርት ለመቀበል የሚጠቀሙባቸውን ግላዊ ስልቶችና ብልሃቶች በመመርመር በመማር ሂደት ተጨባጭ ለውጥ እንዲያሳዩና በሚኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ በሰፊው ሊጠቅሟቸው የሚችሉ ተግባራትን የማከናወን ብቃት እንዲቀዳጁ ለማድረግ የሚያስችሏቸውን ስነዘዴዎች፣ ስልቶችና ብልሃቶችን በመቀየስ ረገድ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ይገኛሉ (Willemse, Lunenberg and Korthagen 2005)፡፡

ተማሪዎች የሚማሩትን ትምህርት በራሳቸው እንዲቆጣጠሩ ለማድረግ የሚያግዙ መሰረታዊ መመሪያዎች በትምህርት ባለሙያዎች እይታ በሰፊው ተቀባይነት እያገኙ የመጡበት ምክንያት የተማሪዎችን የመማር ፍላጎትና ተነሳሽነት ከፍ ለማድረግ ባላቸው አይነተኛ ጠቀሜታ ነው፡፡ ከተማሪዎች የሚማሩትን ትምህርት የመቆጣጠር ሃላፊነት ጋር ተያይዞ የሚነሳው ጉዳይ ምን መማር እንደሚፈልጉ ወይም ምን አይነት እሾቶች ይዘው እንደሚገኙ ለማወቅ ባለው ጠቀሜታ ነው (Willemse, Lunenberg and Korthagen 2005)፡፡ ይህ የሚማሩትን ትምህርት የመቆጣጠር ድርሻ ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው የመማሩ ሂደት ዋንኛ ተዋናይ እንዲሆኑ፣ ተነሳሽነትና ተሳትፎአቸውን እንዲያጎለብቱና የውሳኔ ሰጪነት ክህሎት እንዲያሳድጉ እንደሚያደርጋቸው ይታመናል (Omrod, 2008)፡፡

በትምህርት ቤት የሚቀርቡ መርሐ-ትምህርታዊ ይዘቶች የተማሪዎችን ፍላጎቶች ያገናዘቡ እንዲሆኑ ማድረግ የሚያስፈልግበት ሌላው ምክንያት በተማሪዎቹ መካከል የሚታዩ የትምህርት አቀባበል /አረዳድ/ ልዩነቶችን መነሻ በማድረግ በወል ውጤታማ የሚያደርጓቸውን ስልቶችና ብልሀቶች ለመወሰንና በዚሁ መሰረት ትምህርቱን ለማቅረብ የሚያስችል መሳሪያ በመሆኑ ነው (Pashler, McDaniel, Rohrer & Bjork, 2008)፡፡ የተማሪዎችን ፍላጎት ያገናዘበ ትምህርት አስፈላጊነትን መሰረተሀሳብ የሚያራምዱ የዘርፉ ምሁራን እንደሚስማሙበት የመማር ፍላጎት ትውረት አላማ ውጤታማ ትምህርት የተማሪዎችን የመማር ምርጫ ያገናዘበና የሚማሩት ይዘት ከፍላጎቶቻቸው የተዛመደ መሆን አለበት (Pashler, McDaniel, Rohrer, & Bjork, 2008)፡፡

የተለያዩ ጥናቶች እንዳመላከቱት፣ የተማሪዎች የመማር እርካታና ውጤታማ የመማር ክንዋኔ በተለያዩ ተለዋዋጮች ይወሰናሉ፡፡ Wang (2003) እንደጠቆሙት፣ የመማር ሂደት ማህበራዊ ክንዋኔ ሲሆን በተማሪዎች መካከል የተለያዩ ተራክቦዎች፣ አሳታፊ መስተጋብሮች፣ የመማር ትብብሮችና መደጋገፎች እንዲኖሩ ያስፈልጋል፡፡ ይህም ተማሪዎቹ በሚማሩት ትምህርት ይዘት ፍላጎት እንዲያሳድሩ፣ እርስ በእርስ ልምዶቻቸውን እየተለዋወጡ እንዲማማሩና በንቁ ተሳትፎአቸው የመማሩን ሂደት እንዲቆጣጠሩት ያደርጋቸዋል፡፡

የተማሪዎች የመማር ፍላጎት በእሾቶቻቸው የሚመራ ትልቅ የአቅም ግንባታ ምንጭ እንደሆነ የሚገልጹት Hofer (2010)፣ ተማሪዎች የሚማሩት ትምህርት ለማወቅ ከሚሹት ጉዳይ ጋር የተያያዘ መሆን ተማሪዎች በትምህርቱ ላይ ከፍ ያለ ትኩረት እንዲሰጡ፣ ስለሚማሩት ይዘት በጥልቀት እንዲያሰላስሉ፣ አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው፣ የመማር ተነሳሽነታቸው እንዲጎለብትና ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ የተማሪዎችን ፍላጎትና ተነሳሽነት ከፍ ለማድረግ የሚረዳው በSubramaniam (2009) መሰረት፣ ትምህርቱን ከገሀዱ አለም የተማሪዎቹ እሾት ጋር እንዲጣጣም ማድረግና በእውኑ አለም ተጨባጭ ልምዶቻቸው ላይ እንዲገነባ አውዳዊ አድርጎ ማቅረብ ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የትምህርት ይዘታዊ ፍሬ ነገሮችና ጽንሰሀሳቦች ከመማሪያ ክፍልና ከትምህርት ቤት ባሻገር የገሀዱን አለም ተጨባጭ ተሞክሮዎች የሚወክሉ ወይም የሚያንጸባርቁ መሆን የሚገባቸውም የተማሪዎችን ፍላጎት ለማክበር ነው፡፡

የተማሪዎችን ሁኔታዊ ፍላጎት በጠበቀ መልኩ የሚሰጥ ትምህርት በመማር ሂደት ተማሪዎቹ ከፍ ያለ ትኩረትና ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ ሁኔታዊ ፍላጎት በተጠበቀበትና በእያንዳንዱ ተማሪ ዘንድ ተደራሽ በተደረገበት መማሪያ ክፍል ተማሪዎች በትምህርቱ ሂደት ዘላቂ ተነሳሽነትና ተሳትፎ እንዲያደርጉና በሚማሩት ይዘት ቀጣይ የሆነ የማወቅ ፍላጎት ኖሯቸው እንዲንቀሳቀሱ ለማድረግ አጋዥ ነው (Reid, 1995)፡፡ ፍላጎት-ተኮር ትምህርት የተማሪዎችን ፍላጎቶች መሰረት በማድረግ መርሐ-ትምህርታዊ ውሳኔ ለመስጠት ይረዳል፡፡ ይህም ትምህርቱ የተማሪዎቹን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስና የመማር ጥንካሬያቸውን፣ ችሎታቸውን፣ ፍላጎቶቻቸውን ለማሻሻል እንዲሁም ንቁ ተሳታፊነታቸውን ለማረጋገጥ ቁልፍ ድርሻ አለው፡፡ በመሆኑም የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት መንከባከብና ማጎልበት በሚማሩት የትምህርት ይዘት እንዲማረኩና ዝንባሌዎችን፣ ክህሎቶችን፣ ችሎታዎችንና ልምዶችን እንዲገነቡ ያደርጋል (Hoffmann, 2002)፡፡

በፍላጎት የተደገፈ የመማር ዝግጁነት ተማሪዎች ደረጃ በደረጃ ከበድ ያሉ አዳዲስ እውቀቶችን ያካተቱ ይዘቶችን በተነሳሽነት እንዲያስተናግዱ ያበረታታቸዋል፡፡ የሚቀርበው ትምህርት ይዘት የተማሪዎቹን የመማር ፍላጎት ያገናዘበ መሆኑ ተማሪዎች በተፈጥሯዊ ተሰጥኦዎቻቸው ውስጥ አብረዋቸው ያሉ የመማሪያ ስልቶችና ብልሃቶችን እንዲሁም የቀደሙ ልምዶቻቸውን በመፈተሽ ጽንሰሀሳቦችን እንዲረዱና ነገሮችንና ክስተቶችን በራሳቸው ስልት መርምረው ግንዛቤ እንዲያዳብሩ ለማድረግ አስተዋጽኦ አለው (Renninger, Hidi and Krapp, 2012)፡፡

የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ለማወቅ የመጀመሪያው ተግባር ተማሪዎቹ ምን ላይ ትኩረት እንደሚያደርጉና ምን መስራት እንደሚፈልጉ ማወቅ ነው፡፡ የተማሪዎች ፍላጎት አሰሳ ከተማሪዎች የቀደሙ ልምዶች ዳሰሳ መነሻ ማድረግ ይቻላል፡፡ ወይም የተለያዩ የፍላጎት አማራጮችን አቅርቦ ተማሪዎችን በማስወሰን ፍላጎቶቻቸውን ማወቅ ይቻላል፡፡ በርከት ያሉ ተማሪዎች ተመሳሳይ የእሾት ዳራዎችን ሊጋሩ ይችላሉ፡፡ ይህም በአንድ የተወሰነ ጉዳይ ላይ የጋራ ፍላጎት መኖርን ያመለክታል፡፡ የጋራ ፍላጎት መኖር የጋራ የመማር ዝግጁነት ወይም ልምድ የመቀበል ተነሳሽነት መኖሩን ገላጭ ነው፡፡ የፍላጎት አሰሳ ዋንኛው ጠቀሜታ ዝቅተኛ ውስጣዊ ግፊት ያላቸው ተማሪዎች ስለሚማሩት ትምህርት ያላቸውን ምልከታ ለማወቅ ብሎም ከፍላጎታቸው የተገናዘበ አዲስ የመማሪያ ብልሃት ለመከተል የግብአት ያህል ጠቀሜታ ያለው ነው፡፡

### 2.1.2 የፍላጎት ተኮር ትምህርት አስፈላጊነት

ፍላጎት ተኮር ትምህርት የትምህርቱን አቀራረብ ከተማሪዎች መሰረታዊ ፍላጎቶች ጋር አጣጥሞ ለማቅረብ የሚረዳ፣ የመማር ማስተማሩን ሂደት በተማሪዎቹ ውሳኔ ሰጪነት ሚና ለማስመርኮዝ ጠቀሜታ ያለው አዲስ አተያይ ሲሆን ምን እንደምናስተምር፣ ምን ያህል እንደምናስተምር፣ ለምን ያህል ጊዜ ትምህርቱ መሰጠት እንዳለበት ለመወሰን የሚረዳ በመሆኑ ተማሪዎች በመማር ሂደቱ ተደሳችነትና ተነሳሽነት እንዲኖራቸው የበኩሉ ድርሻ ከፍ ያለ ነው፡፡ በፍላጎት ተኮር ትምህርት ሂደት ተማሪዎች ንቁ ተሳታፊ ስለሚሆኑ የሚቀርብላቸውን ይዘት በራሳቸው ይቆጣጠሩ ዘንድ ተበረታችነት ያሳያሉ፤ የሚሰጧቸውን ተግባራትና ክንዋኔዎች በተራክቦ ያዳብራሉ፤ ስለሚማሩት ይዘት በተሻለ ኃላፊነት መንፈስ ስለሚያከናውኑ በተሻለ ቅልጥፍና ይሸፍኑታል ተብሎ ይታመናል (Renninger, Hidi and Krapp, 2012)፡፡

ፍላጎት ተኮር የመማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን እሾቶች ማእከል አድርጎ እንደመቅረቡ መጠን ተማሪዎቹ ወደ መማሪያ ክፍል ይዘዋቸው የሚመጧቸውን ልምዶች፣ አስተሳሰቦችና አሰራሮች በመጋራት የሚማሩትን ይዘት በፍጥነት በመሸፈን ወደ አዲስ ይዘት እንዲሸጋገሩ ያደርጋቸዋል፡፡ በትምህርቱ ይዘት ውስጥ አስቀድሞ የሚያውቋቸውን ጉዳዮች ከማያውቋቸው አዳዲስ ይዘቶች የመለየት እድል ስለሚያገኙ በአዳዲስ ጽንሰሀሳቦችና ትምህርታዊ ጉዳዮች ላይ ጉልህ አጽንኦት በማድረግ ትኩረቶቻቸውን አሰባስበው እንዲማሩ ለማድረግ ይረዳል (Hoffmann, 2002)፡፡

ፍላጎትን መሰረት ያደረገ ትምህርት ያሉትን ልዩ ልዩ አበይት ጠቀሜታዎች በማጠቃለል Renninger, Hidi and Krapp (2012) እንደሚከተለው በአጭሩ አቅርበዋል፡-

- መምህራን የተማሪዎችን ፍላጎቶች ከሚያስተምሩት ትምህርት ይዘት ጋር ደረጃውን በጠበቀ መልኩ በማቀናጀት የመማር ሂደትን ለተማሪዎቹ አስደሳችና አርኪ ለማድረግ ያስችላቸዋል፡፡
- በተማሪዎች ፍላጎት ላይ በተመሰረተ ትምህርታዊ አቀራረብ የተማሪዎች መነቃቃት ማጣት (የመደበር ስሜት) በጣም ውሱን ነው፡፡

- ፍላጎት ተኮር አቀራረብ የተማሪዎችን ስሜት ለማነሳሳት ከፍ ያለ ጠቀሜታ ያለው በመሆኑ ከሚማሩት ይዘት ጋር የሚዛመዱ በርካታ መረጃዎችን በአእምሯቸው ማቆየት ያስችላቸዋል፡፡
- ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ ከሚቀርቡላቸው ተግባራትና መልመጃዎች ዙሪያ ለመነቃቃት (motivation) የሚገጥሙት ትግል ያነሰ ይሆናል፡፡
- ተማሪዎች ከአንዱ ወደ ሌላው የመማር ክንዋኔ ከመሸጋገራቸው በፊት በአንድ የተወሰነ የትምህርት ይዘት፣ ተግባር፣ መልመጃ፣ ፕሮጀክት ለረዘመ ጊዜ ቆይተው መስራት የሚገባቸው መሆኑን በነጻነት ይወስናሉ፡፡
- ተማሪዎች በሚገባ በሚያውቋቸው ጉዳዮች ላይ ትኩረት ከማድረግ ይልቅ በማያውቋቸው ጉዳዮች ላይ ይበልጥ አጽንኦት አድርገው እንዲሰሩ ያደርጋቸዋል፡፡
- የገሃዱን አለም ተሞክሮና ልምድ ወደ መማሪያ ክፍል በማምጣት ስለሚማሩ ለህይወት ዘመን የሚሆን ግንዛቤ ያበረክትላቸዋል፡፡
- ትምህርቱ በተማሪዎች የገሃዱ አለም ተሞክሮና ልምድ ላይ ተመርኩዞ ስለሚቀርብ በነቃ ተሳትፎ የትምህርቱን ይዘት እንዲሸፍኑት ለማድረግ ይረዳል፡፡

በአጠቃላይ በተማሪዎች የመማር ፍላጎት ላይ ተመስርቶ የሚታቀድ ትምህርት ለተማሪዎቹ የተሻለ አረዳድ የሚጠቅሙ ተግባራትና ክንዋኔዎችን ለማቅረብ መጠነ ሰፊ አስተዋጽኦ ያለው ከመሆኑ ጋር ዘላቂነቱን የጠበቀ ስነትምህርታዊ ሞዴል ነው (Renninger, Hidi and Krapp, 2012፣ 16-17)፡፡

ፍላጎት በትምህርት ቤት ውስጥ በተለይም በሁለተኛ ወይም በውጭ ቋንቋ መማር ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡ ፍላጎት "አንድ ሰው ከይዘት አካባቢ ወይም ከተግባሩ ጋር አዎንታዊ ግንኙነት ሲኖረው የሚፈጠር ከፍተኛ ትኩረት እና ከአዎንታዊ ስሜት የመነጨ ተሳትፎ ነው" (Hiddy and Raniner, 2006፡112) ፡፡ በቅርቡ በቋንቋ ትምህርት መስክ የተከናወኑ ለውጦች በቋንቋ ትምህርት ፍላጎት ሚና ላይ የነበረው ትኩረት እንዲከለስ አድርገዋል፡፡ ፍላጎት የተማሪዎችን የበለጠ መስተጋብር ያስገኛል እናም የመማር ትኩረታቸውን እና ተነሳሽነታቸውን ያሳድጋል ተብሎ ይገመታል፡፡

Tobias (1994) እንደገለጹት፣ የፍላጎት ተፅእኖ በመማር እና የገበዩትን እውቀት ለረጅም ጊዜ ጠብቆ በማቆየት ሊገለጽ ይችላል፡፡ በመማር ሂደት ላይ ያተኮሩ ጥናቶች ተማሪዎች

ውጤታቸውን እንዴት ማሻሻል እንደሚችሉ ከደረሱባቸው ተጨባጭ ግኝቶች አንዱ ትምህርቱ በተማሪዎች ፍላጎት ላይ ተመርኩዞ ማቅረብ መሆኑን ይስማማሉ (Sofif፣ 1991)። Edis-Wiak (2010) ደግሞ የመማር ፍላጎትን መንከባከብ አስፈላጊነትን በአጽንኦት ያመላከቱ ሲሆን መምህራን የመማሪያ ክፍል እንቅስቃሴዎችን የተማሪዎቹን ማህበራዊ አካባቢ ችግር ፈቺ፣ ከገሀዱ አለም ተሞክሮ የመነጩ፣ በተማሪዎች ነባራዊ ልምዶች የተገናኙ፣ አነቃቂና አሳታፊ አድርገው በመንደፍ ከይዘቱ ዓላማዎች ሳያፈነግጡ ትምህርቱ ፍላጎትን የሚስብ እና የሚያታኩር አድርገው ሊያቀርቡ እንደሚችሉ ጠቁመዋል፡፡

## 2.1.3 ፍላጎት ተኮር ትምህርትን ለመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የማቅረብ ጠቀሜታ

ባለንበት ዘመን በተለይ በሁለተኛ ቋንቋ ማስተማር መስክ እድገት እየታየ በመምጣቱ ለመማር ፍላጎት ስለሚያበረክተው ሚናም የተለየ ትኩረት እየያዘ ይገኛል፡፡ ተማሪዎች የተሻለ ፍላጎት፣ ትኩረትና ተበረታችነት የሚኖራቸው በመስተጋብራዊ ክንውኖች ውስጥ ሲሳተፉ ነው የሚል እሳቤ በብዙ የዘርፉ አዋቂዎች እየታመነበት መጥቷል፡፡ በEidswick (2010) እንደተገለጸው፣ ፍላጎት በመማር ባህሪ ባለው ተጽእኖ ላይ አጽንኦት ማድረግ የተማሩትን ለረጅም ጊዜ እንዲያስታውሱት ለማድረግ የሚረዱ ስሜታዊ ምክንያቶችን ጠቀሜታ ላይ ማዋል ነው፡፡ ፍላጎት ተማሪዎች በጽናት የሚቆሙለት ባህሪያቸው በመሆኑ መምህራን ፍላጎታቸው ላይ የተመሰረቱ ይዘቶችንና የማስተማሪያ ዘዴዎችን በመምረጥ ወደ ክፍል ይዘው መምጣት ትምህርቱን ግባዊና ተማሪዎቹን ውጤታማ ለማድረግ ጠቀሜታ አለው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ Walkington & Sherman (2013)ም እንደገለጹት፣ መምህራን ተነሳሽ መሆን ያለባቸው ከተማሪዎች ፍላጎት ጋር የተዛመዱ ማራኪ ርእሶችን በመምረጥ የመማሪያ አውዱን ለተማሪዎቹ አስደሳች፣ የመማር ተግባራቱንም ተወዳጅ ማድረግ ይኖርባቸዋል ባይ ናቸው፡፡ እንደ Walkington & Sherman (2013) እምነት ፍላጎት ተኮር ቋንቋ ማስተማር (IBLT) የተማሪዎችን ፍላጎት ከፍ ለማድረግ አስተዋጽኦ አለው፡፡

በዚሁ መሰረት እንደ Hidi and Harackiewicz (2008) አገላለጽ፣ ትምህርት ቤቶችና መምህራን የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ለማሳደግ በሚያግዙና ውጤታማነታቸውን በሚያሻሽሉ ስልቶችና ብልሃቶች አስሶ በማቅረብ ላይ ብርቱ ትኩረት ሊያደርጉ ይገባል፡፡ በእርግጥ ተግባቦታዊና አሳታፊ የሆኑ ተግባራት ለግልና ለቡድን ውጤታማነት ተመራጭ

እየሆኑ መጥተዋል፡፡ እንደ Walkington & Sherman (2013) አገላለጽ፣ በፍላጎት ዙሪያ የሚደረግ አጽንኦት አዋጭ የሆኑ የማስተማሪያ ብልሃቶችን መጠቀም፣ ከመረጃዎች በመነሳት መወሰንን የሚጠይቅ ነው፡፡ ይህም ተማሪዎች የተሻለ አንብቦ የመረዳት ልምድና የተማሩትን መረጃ ለተራዘመ ጊዜ አስታውሶ የመጠቀም ችሎታ እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

በመማር ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ትምህርት የመምህራንና የትምህርት ባለሙያዎችን ከፍ ያለ ትኩረትና ጥረት የሚጠይቅ ጉዳይ ነው፡፡ የተማሪዎችን ፍላጎት ያከበረ ትምህርት ማቅረብ በተለይ የመምህራንን ዝግጁነት፣ ተነሳሽነት፣ አመለካከትና ብቃት የግድ ይላል፡፡ እነዚህ የመምህራን ዳራዎች ተሟልተው በተገኙበት እንዲሁም በአንድ መማሪያ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ብዛት የተመጠነ በሆነበት፣ ትምህርታዊ ይዘቶችን በተማሪዎች ፍላጎት ላይ ተመርኩዞ ለማቅረብ የሚረዳ ትምህርታዊ አውድ በቀላሉ መፍጠር ይቻላል (Wang, 2003)፡፡

ይህን ፍላጎት ተኮር የመማር እሳቤ ከትምህርት መጀመሪያ እድሜ ጋር አዛምዶ ማቅረብ ተማሪዎች ከጅምሩ ተሞክሮውን እየተገነዘቡ፣ አብዛኛውን የመማር ጊዜያቸውን በፍላጎት ላይ ተመርኩዘው በሚቀርቡ ልምምዶች ውስጥ እየተሳተፉ እንዲዘልቁ ስለሚያደርግ እያደጉ ሲሄዱ ስለራሳቸው መማር የበለጠ የኃላፊነት ስሜት ይሰማቸዋል፡፡ በትምህርቱ ሂደት ተደሳች ስለሚሆኑ ውጤታማ ያደርጋቸዋል ተብሎም ይታመናል (McCarthy, 2014)፡፡

በርካታ ልማዳዊ የማስተማሪያ ሞዴሎች የተማሪዎችን የመማር ፍላጎቶች ያላከበሩና ትምህርታዊ መረጃዎችን በማዳመጥ ብቻ እንዲቀበሉ የማድረግ ውሱንነቶች የነበሩባቸው ናቸው፡፡ ይህም ተማሪዎችን አዳማጭ ከማድረግ የዘለለ ተማሪዎቹ የሚማሩትን ይዘት ለማስታወስ፣ ለመመርመር፣ ከቀደሙ ልምዶቻቸውና ገጠመኞቻቸው ጋር ለማዛመድና ለማገናዘብ ጠቀሜታ ያልነበራቸው ናቸው (McCarthy, 2014)፡፡ ይህም አዳዲስ የማስተማሪያ ሞዴሎች በየጊዜው እየተፈጠሩ በተግባር እንዲፈተሹ ምክንያት የሆነ ሲሆን፤ በተለይ ፍላጎት ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ ለሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ አውድ ሰፊ አስተዋጽኦ ያለው ውጤታማ ሞዴል ነው (Renninger, Hidi and Krapp, 2012፣ 16-17)፡፡

ፍላጎት ተኮር ትምህርት በተለይ የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት እርከን ከፍ ባለ ሁኔታ ተዘንግቶ የቆየ ነገር ግን ለተማሪዎቹ የትምህርት አቀባበል ሰፊ አስተዋጽኦ የነበረው ሞዴል ነው፡፡ ፍላጎት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ ከሌሎች ተማሪ ተኮር በሆነ ብልሃት ማቅረቢያ አዳዲስ ብልሃቶች ጋር በመጣመር ተማሪዎች በመስራት-መማር፣ በትምህርቱ ሂደት ተሳትፎ የማድረግ ክንውኖችን ዘላቂ በሆነ መልኩ ለገሃዱ አለም ግንኙነቶቻቸው ወይም ተግባቦታዊ ፍላጎታቸው ጠቃሚ በሆኑ ስልቶች ማቅረብ ላይ የሚያተኩር በመሆኑ ያነቃቃቸዋል፤ የመማር ተነሳሽነትን ከፍ ለማድረግ ሁነኛ አስተዋጽኦ አለው (Renninger, Hidi and Krapp, 2012፣ 16-17)፡፡

በተለይ በሁለተኛ ደረጃ የትምህርት እርከን ተማሪዎች የሚማሩትን ትምህርት እንዲነድፉ ማድረግ የመማር ፍላጎታቸውን ለማንሰራራት ከሚጠቅሙ ብልሃቶች አንዱ ነው፡፡ ተማሪዎች ስለሚማሩት ይዘት የበለጠ ትኩረት እንዲኖራቸው፣ አላማ ይዘው እንዲነሱና የግል ሃሳቦቻቸውን በማዋጣት አንድን ትምህርታዊ ፕሮጀክት በተነሳሽነት አጠናቀው እንዲያቀርቡ እድል ይሰጣቸዋል፡፡ ይህ በግንባታውያን ንድፈ ሃሳብ ላይ ተመርኩዞ የቀረበ የመማሪያ ሞዴል ተማሪዎች ውስብስብ የሆኑ ተግባራትን ጊዜ ወስደው እንዲያከናውኑ፣ በቡድን ቅንጅቶች የተለያዩ ስራዎችን በጋራ እንዲሸፍኑ ለማድረግ ስለሚረዳ የመምህሩን ጊዜና ዝግጅት በመቀነስ ተማሪዎቹ በተሳትፎ እንዲማማሩ ያበረታታቸዋል፡፡ ካዳመጡት ይልቅ እያከናወኑ ከተማሩት የሚቀስሙት ልምድ ይበልጥ አይረሴ ስለሚሆን በትምህርቱ ሂደት ውጤታማ እንዲሆኑ፣ ያገኙትን እውቀትና ልምድ በሌሎች ተግባራትና የህይወት ዘመን አጋጣሚዎች አሸጋግረው እንዲጠቀሙባቸው ለማድረግ አጋዥ ነው (McCarthy, 2014)፡፡

በአጠቃላይ ፍላጎት በትምህርቱ ሂደት ለሚከናወን ማንኛውም ተግባር ግብ መምታት ከፍተኛ የሆነ አስተዋፅኦ ያበረክታል፡፡ ስለሆነም የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችና ክንውኖች ከተማሪዎች ፍላጎት ጋር ተቀናጅተው በመተግበር ተማሪዎችን ውጤታማ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ውጤታማነት የሚመነጨው ደግሞ ለትምህርቱ ትኩረት ሰጥቶ የመከታተልና በአስተውሎት የመመርመር ፍላጎት ይዞ በመገኘት ነው። ፍላጎት ላይ ተገቢ ትኩረት ከተደረገ ተማሪዎቹ በሚሰጠው ትምህርት ላይ ንቁና ተሳታፊ ሆነው ትምህርቱን ስለሚከታተሉ የመማር ማስተማር ሂደቱም ውጤታማ ይሆናል፡፡ የነዚህ ነገሮች አዎንታዊ

ቅንጅት ደግሞ የመማር ማስተማሩን ሂደት አስደሳችና ግብ መቺ ያደርገዋል፡፡ ለትምህርቱ ጥሩ ፍላጎት ያለው ተማሪ ደግሞ ውጤታማ ይሆናል፡፡

### 2.1.4 የፍላጎት አይነቶች

የሁለተኛ ቋንቋ መማር ተነሳሽነት ምርምር መሪ የሆኑት Gardner (2001)፣ Brown (2000)፣ ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነትን ውህዳዊና ጥቅማዊ በማለት በሁለት ይከፍሉታል (Justina, 2015)፡፡ በሌላ በኩል Williams & burdan (1997) ፍላጎትን በውስጣዊና ውጫዊ የፍላጎት ዓይነቶች አስተዋውቀዋል፡፡ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ከቋንቋው ተናጋሪዎች ባህል ጋር ትስስር ለመፍጠር የሚማሩ ከሆነ ፍላጎታቸው ውህዳዊ ሲሆን፣ በቋንቋው አንዳች ጥቅም ለማግኘት ከሆነ ደግሞ ፍላጎታቸው ጥቅማዊ ነው (Gardner, 2001፣ Brown, 2000)፡፡ በሌላ በኩል ሰዎች የሚያከናውኑት ተግባር ስለአንድ ነገር ለማወቅ፣ ለመረዳትና ደስታ ለማግኘት ከሆነ ተግባራቸው ውስጣዊ ፍላጎትን መሠረት ያደረገ ሲሆን፣ ከተግባሩ ውጭ ከሆነ አካል አዎንታዊ ግብረመልስ ለማግኘት የሚሠሩ ከሆነ ግን ተግባራቸው ውጫዊ ፍላጎትን መሠረት ያደርጋል (Justina, 2015፣ Williams & burdan, 1997)፡፡

ፍላጎት ለመወደስ፣ ሽልማት ለማግኘት፣ ለመመስገን፣ በፈተና ጥሩ ውጤት ለማስመዝገብ ወዘተ ባሉ ውጫዊ ግፊቶች ይጠናከራል (Eliot, et al., 2005, Brown, 2000፤ Ellis, 1994)፡፡ ውጫዊ ፍላጎት ወይም ተነሳሽነት ውስጣዊ ፍላጎት ወይም ተነሳሽነትን ሊቀንስ ይችላል (Gardner, 2001፣ Brown, 2000)፡፡ እንደተመራማሪዎቹ አተያይ በውስጣዊ ፍላጎት ለሚከናወን ተግባር ውጫዊ ሽልማቶች ሲሰጡ ውስጣዊ ፍላጎት ሊቀንስ ይችላል፡፡

### 2.1.5 የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ለመጠበቅ የሚረዱ ብልሃቶች

ጥናቶች እንዳመላከቱት በቀለሙ መስክ በበርካታ የትምህርት አይነቶች የተማሪዎች ፍላጎት ባልተጠበቀ መልኩ ከጊዜ ወደ ጊዜ ማዘቅዘቅ እንደሚታይበት የተመለከቱ ጥናቶች አሉ (Willemse, Lunenberg & Korthagen, 2005፣ Hidi and Harackiewicz, 2000፣ Wright, 2016)፡፡ ይህ ያልተጠበቀ ልምድ በአብዛኛው በአንደኛ ደረጃ የትምህርት እርከን ጎልቶ የሚታይ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በመካከለኛ ሁለተኛ ደረጃ የትምህርት እርከንም እንደሚንጸባረቅ (Hidi and Harackiewicz, 2008) ይጠቁማሉ፡፡ ለምሳሌ፡- በቻይና አንደኛ

ደረጃና መካከለኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይህ የፍላጎት ማነስ በተደጋጋሚ የሚታይ መሆኑን፣ ለዚህ ‹‹የመማር ተነሳሽነት ማነስ›› / learning weariness/ የሚል ብያኔ እንደተሰጠው ብሎም በጥናት እንደተረጋገጠው 17.38% የቻይና ገጠር አካባቢ መካከለኛ ደረጃ ተማሪዎች ‹‹የመማር ተነሳሽነት ማነስ›› ሰለባ እንደሆኑ የGuo & Zhang (2012) ሪፖርት ያስረዳል፡፡ በጽንሰ-ሃሳባዊ እና ተግባራዊ ጥናቶች አጽንኦት ሰጥተው እንዳቀረቡት ግለሰባዊ መንስኤዎችና አካባቢያዊ ምክንያቶች (Walkington & Sherman, 2013፣ Justina, 2015) ለቀለም ትምህርት ፍላጎት መቀዛቀዝ ዋንኛ ገፊ ምክንያቶች ሆነው ቀርበዋል፡፡ የቻይና ተማሪዎች የሚያነሱት ዋንኛ ምክንያት ከባድ ትምህርታዊ ጫናን ነው (Guo and Zhang, 2012)፡፡

ተማሪዎች የመማር ፍላጎት ኖሯቸው በመማር ማስተማሩ ሂደት ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ ቀዳሚው ተግባር በመማር አውዶች የተሻለ የሚመሰጡባቸውንና የሚደሰቱባቸውን ጉዳዮች ለይቶ በማወቅ እነዚህን የመማር ማስተማሩ ሂደት አካል ማድረግ ነው፡፡ ተማሪዎች የሚማሩት ትምህርት ይዘት ከፍላጎታቸው ጋር እንዲስማማ ለማድረግ በመማር ሂደት አብዝተው የሚያተኩሩባቸውንና ለመስራት የሚወዷቸውን ጉዳዮች በማሰስ እነዚህን የመማሪያ ቴክኒኮች የትምህርቱ እቅድ አካል በማድረግ ፍላጎታቸውን መያዝ እንደሚቻል Willemse, Lunenberg & Korthagen, (2005) ይገልጻሉ፡፡ በመማር ማስተማሩ አውድ ተማሪዎች ጥሩ ፍላጎት እንዲያሳድጉ ከማድረግ አንጻር የተማሪዎችን የመማር ችግሮች፣ የተነሳሽነት ጉድለቶች፣ ከቤተሰብ ጋር የተያያዙ አለመመቻቸቶች ለይቶ በማወቅ ለማቃለል መሞከር አስፈላጊ ነው፡፡ በመማር ማስተማሩ አውድ የተማሪዎችን ፍላጎት ለማምጣት Willemse, Lunenberg & Korthagen, (2005) በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ማትኮር እንደሚያስፈልግ ይጠቁማሉ፡-

ሀ) በተቻለ መጠን የመማር ማስተማሩን ሂደት ተማሪዎቹ እንዲቆጣጠሩት ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ መምህር መራሽ በሆነ መማሪያ ክፍል ውስጥ በርካታ መምህራን የመምህሩን የማስተማር ስልት ተከትለው የሚያዳምጡ፣ አብዛኞቹ ከተሳትፎ ተገልለው የመምህሩን እውቀትና ልምድ ብቻ በመቀበል የተወሰኑና የራሳቸውን የግል ልምዶች ለማንጸባረቅ ምቹ እድል የተነፈጉ ናቸው፡፡ ተማሪዎች የግል የመማር ልምዶቻቸውን ለማንጸባረቅ እድል ባገኙ መጠን ራሳቸውን የመማር ማስተማሩ ሂደት አካል በማድረግ ተሳትፎ፣ ተነሳሽነትና የአክብሮት አመለካከት ይሰማቸዋል፡፡

ተማሪዎች የትምህርቱ አካል መሆናቸው የሚፈጥርባቸው ስሜት ከፍ ባለ ቁጥር አዳዲስ ነገሮችን የመማር ተሞክሯቸው ይጎለብታል(Willemse, Lunenberg & Korthagen, 2005)፡፡

ለ) ለተማሪዎች በትምህርቱ ይዘት ላይ የተመሰረተ የማንበብ አውድ መፍጠር ለማንበብ ፍላጎትና ግፊት እንዲኖራቸው አጋዥ ነው፡፡ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት የጋለ የማንበብ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ብዙ ነገሮችን ለመረዳት ስለሚሹ ለመማር ያላቸው ተነሳሽነት እንዲንሰራራ ያደርጋል፡፡ በዚህ ምክንያት ማንበብ የተማሪዎችን የማወቅ ፍላጎት ያሳድጋል፡፡ ከዚህም ባሻገር የካበተ የቃላት እውቀት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ በድምጽ የተደገፈ ንባብ እንዲያካሂዱ ማድረግ ብቻ ሳይሆን በቤት ውስጥ ሲሆኑም የሚያነቧቸው ነገሮች ቢሰጧቸው አጠቃላይ የመማር ፍላጎታቸውን ለመንከባከብና ለማሳደግ ጠቀሜታ ይኖረዋል (Willemse, Lunenberg & Korthagen, 2005)፡፡

ሐ) በተማሪዎች የመማር ፍላጎት ላይ ትኩረት አድርጎ መስራት ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ለማድረግ ጠቀሜታ አለው፡፡ ተማሪዎች በምን በምን የመማር ብልሃቶችና ዘዴዎች ድጋፍ ሲማሩ ፍላጎታቸው ከፍ እንደሚል ማወቅ ፍላጎት ተኮር ትምህርትን ለማምጣትና የመማር ሂደትን ለተማሪዎቹ አስደሳችና አነቃቂ ለማድረግ መሰረታዊ ጉዳይ ነው (Willemse, Lunenberg & Korthagen, 2005)፡፡

መ) በጨዋታዎች ላይ የተመሰረተ ትምህርት (Game-based learning) እንደ አንድ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት በመያዝ የትምህርት ይዘትን ለማቅረብ በሚረዳ መሳሪያነቱ በእጅጉ ታዋቂ የፍላጎት መንከባከቢያ ብልሃት ነው፡፡ በጨዋታዎች ላይ የተመሰረተ ትምህርት ተማሪዎች የሚማሩትን ይዘት ጠለቅ ባለ ሁኔታ እንዲገነዘቡ ለማድረግና በአእምሮ የማሰብና የመመራመር ክህሎት እንዲያሳድጉ ሁነኛ አስተዋጽኦ ያለው የመማሪያ ብልሃት ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በጨዋታዎች ላይ የተመሰረተ ትምህርት አውድ በሚሳተፉበት ወቅት አእምሮአቸው ከአዳዲስ ነገሮች፣ አሰራሮችና ውጤቶች ጋር ለመተዋወቅ እድል ያገኛል፡፡ በጨዋታዎች ላይ የተመሰረተ ትምህርት እጅግ በጣም ጥሩ የአዳዲስ ጽንሰሀሳቦች፣ እውቀቶችና ሐሳቦችን የማቅረቢያ ብልሃት

ሲሆን ተማሪዎች የሚማሩትን ትምህርት በፍላጎት እንዲማሩ ለማድረግ ጠቀሜታ አለው (Willemse, Lunenberg & Korthagen, 2005)፡፡

ሠ) ተማሪዎች ወደ ክፍል ይዘው የሚመጧቸው ተፈጥሯዊ የሆኑ የመማር ስልቶች (learning styles) እንዳሏቸው በርካታ ጥናቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ነው፡፡ ተማሪዎች በተፈጥሯዊ መንገድ የያዙዋቸው የመማሪያ ስልቶች ለመማር ያሏቸው የግል ምርጫዎች በመሆናቸው ‹‹ትክክለኛ›› ወይም ‹‹የተሳሳተ›› የመማሪያ መንገድ ተብለው የሚፈረጁ አይደሉም፡፡ ለምሳሌ አንዳንድ ተማሪዎች ከማዳመጥ ይልቅ እያነበቡ ወይም እየተመለከቱ የመማር ፍላጎት አላቸው፡፡ ሌሎች ተማሪዎች ደግሞ ከማየት ወይም ከማዳመጥ ይልቅ እየሰሩ /እያከናወኑ/ የመማር ፍላጎት አላቸው፡፡ ሌሎች ማስታወሻ እየጻፉ ከመማር ይልቅ በማዳመጥ ብቻ የመማር ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች አሉ፡፡ መምህሩ ተማሪዎቹ በየትኛው ወይም የትኞቹ ተፈጥሯዊ የመማር ስልቶች የተሻለ ፍላጎት እንደሚያሳዩ በመገምገም የሚቀርበውን የትምህርት ይዘት ከተማሪዎቹ ተነሳሽነት ጋር አጣጥሞ ለማቅረብ ያስችለዋል (Willemse, Lunenberg & Korthagen, 2005)፡፡

ረ) መምህሩ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ሁሌም የተማሪዎቹን የመማር ፍላጎት ጠብቆ ወይም ተንከባክቦ ለመዝለቅ ተማሪዎች ዝግጁ ሆነው እንዲገኙ ማገዝ ይኖርበታል፡፡ በእርግጥ የመማር ዝግጁነት የጎደላቸው /የሌላቸው/ ተማሪዎች የሌሎች ተማሪዎች የመማር ዝግጁነትና ፍላጎት እንዲጓደል በአንድ ወይም በሌላ ጉዳይ ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የተማሪዎች የመማር ዝግጁነት ከስነልቦናዊ፣ ማህበራዊ፣ ቁሳቁሳዊ ወይም ሌሎች መሰረታዊ አስፈላጊ ሁኔታዎች ጋር ሊያያዙ ይችላሉ፡፡ መምህሩ የዝግጁነት ጉድለት መንስኤዎችን በስነልቦና ግንባታ በማስወገድ በተማሪዎቹ ዘንድ የመማር አዎንታዊ ፍላጎት እንዲፈጠር አስፈላጊውን ጥረት ማድረግ እንዳለበት ይመከራል፡፡ ተማሪዎች በወጣትነት እድሜ የሚገኙ እንደመሆናቸው መጠን ፍላጎትን በሚያጓድሉ መንስኤዎች የተከበቡ ናቸው፡፡ ይህ ችግር በመማር ፍላጎታቸው ላይ አሉታዊ በሆነ መልኩ ይንጸባረቃል፡፡ ከተሳትፎ መገለል፣ የጀመሩትን የቡድን ፕሮጀክት ከፍጻሜ አለማድረስ፣ የሌሎችን የመማር ፍላጎት ማወክ፣ የመማሪያ ክፍሉን ከመማር ግንኙነት ጋር የተያያዙ መሰረታዊ መርሆዎች አለማክበር፣ ወዘተ አሉታዊ ባህርያት ከተማሪዎች የዝግጁነት ጉድለት የሚዋረሱ ናቸው፡፡ በአንጻሩ በቂ የመማር ዝግጁነት

በሰፈነበት መማሪያ ክፍል በአብዛኛው የተማሪዎች የመማር ፍላጎት እንደሚጠበቀው ይሆናል (Willemse Lunenberg & Korthagen, 2005)፡፡

### 2.1.6 የመማር ፍላጎትና ውጤታማነት ግንኙነት

Linnenbrink and Pintrich (2008) እንደገለጹት፣ የመማር ፍላጎት ሲነሳ አብሮ በብዙዎች አእምሮ ታሳቢ የሚሆነው ጉዳይ ከሚማሩት የትምህርት አይነት ጋር ተያይዞ የሚገኘው የመማር ውጤታማነት (achievement) ነው፡፡ ይህ የመማር ፍላጎትና ውጤታማነት ሊጤን የሚገባው ከተማሪው የመማር ፍላጎት በጥሩ ሁኔታ ዳብሮ መገኘት ጋር መሆን ይኖርበታል፡፡ የፍላጎትና ውጤታማነት ትስስር በተበጁ የውጤት መለኪያ መሳሪያዎች በመደገፍ ተማሪው ባሳየው አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ውጤት ላይ ብቻ የሚመረኮዝ ከሆነ ወደ ትክክለኛ የፍላጎት ድምዳሜ ላያደርስ ይችላል (Hidi, 2013)፡፡ ባለፉት አሰርት አመታት ከቀረቡ እጅግ በርካታ የመማር ማስተማር ሂደት ላይ ያተኮሩ ጥናቶች መካከል ፍላጎትን እንደ አንድ ተለዋዋጭ ወስደው ያጠኑ ፍተሻዎች ይገኙበታል፡፡ የእነዚህ ፍተሻዎች ግኝቶች አልፎ አልፎ እርስ በርስ የሚቃረኑ ሆነው የሚገኙ ሲሆን የዚህ ተቃርኖ መንስኤ ሊሆን እንደሚችል የሚታሰበው የፍላጎት ጽንሰሀሳብ ግንዛቤና መለኪያ ልዩነት መኖሩ ነው፡፡ አንዳንድ ተመራማሪዎች ፍላጎትን ከአንድ ጊዜ የተማሪዎቹ ውጤታማነት ጋር ሲያዛምዱት፣ ሌሎች ደግሞ በሚማሩት ትምህርት ላይ በተማሪዎች ከጅምሩ የተያዘ ፍላጎት ለውጤታማነት መንስኤ እንደሆነ ያቀርባሉ (Hidi, 2010)፡፡

በዚህ ንኡስ ምእራፍ የተለያዩ የፍላጎት አይነቶች፣ እነዚህ የፍላጎት አይነቶች ከተማሪዎቹ የመማር ፍላጎትና ከውጤታማነት ጋር ያላቸው ተዛምዶ ተዳስሰው ቀርበዋል፡፡ በዚሁ መሰረት የፍላጎት ጽንሰሀሳብ የሚያመለክተው ተማሪዎች ለአንድ የተወሰነ የትምህርት አይነት /ይዘት/ ያላቸውን የመውደድ ስሜት በመማር ተራክቦ (affective reaction) የሚገልጹበት ስነልቦናዊ አቋም ነው (Barron & Harackiewicz, 2000)፡፡ የተለያዩ የፍላጎት አይነቶች እውቅና አግኝተዋል፡፡ እነዚህ የተለያዩ የፍላጎት አይነቶች የሚከፈሉት የተማሪዎችን አውዳዊ (situational) ፍላጎት ወይም ግላዊ (individual) ፍላጎት መሰረት በማድረግ ነው (Beck & McKeown, 2001)፡፡ አውዳዊ ፍላጎት የሚገልጸው ከአንድ የተወሰነ ወቅታዊ ሁነት (ለምሳሌ ድንገተኛ ድምጽ) ጋር ተያይዞ በተማሪዎች የሚፈጠር ፍላጎት፣ መነሳሳት ወይም ስሜት ነው፡፡ እንዲህ አይነቱ ፍላጎት ለምሳሌ፡- በፕሮጀክት ተግባር ከሌሎች አቻዎች ጋር አብሮ ለመስራት ጠቀሜታ፣ አንድን በማንበብ የተጠናቀቀ

ክንውን በስእል (ካርቱን/ አስደግፎ ለማቅረብ አነሳሽነት ይኖረዋል (Barron & Harackiewicz, 2000)፡፡ በሌላ በኩል ግለሰባዊ ፍላጎት የሚያመለክተው አንድ ተማሪ በአንድ የትምህርት አይነት ቅደም ተከተላዊ ይዘቶች ቀጣይነት ባለው መልኩ በተደጋጋሚ ለመሳተፍ የሚያሳየውን ዘላቂ ፍላጎት ነው፡፡ ምንም እንኳን ግለሰባዊ ፍላጎት በውስጣዊ ፍላጎትነቱ (intrinsic motivation) የሚቀርበው በአንድ ተመሳሳይ የመማር ሂደት (በተሰጡ ተግባራትና ክንውኖች ለተግባራቱ ሲባል ብቻ በማከናወናቸው የተማሪዎቹን ዘላቂ ደስተኛነት ጨምሮ) ተመሳሳይ ውጤትን ለመግለጽ ቢሆንም፣ ግለሰባዊ ፍላጎት የሚገለጸው ተማሪው እንደግለሰብ ከትምህርቱ ጋር ባለው ግንኙነት ነው (Jacobs & Eccles, 2010፣ Barron & Harackiewicz, 2000)፡፡

ምንም እንኳን ለማከማቸት በሚያስችሉት እውቀት ግንኙነትና በሚሰጡት መሰረታዊ ጠቀሜታ ቢለያዩም፣ ሁለቱም አውዳዊ ፍላጎትና ግለሰባዊ ፍላጎት በጥምረት የሚገልጹት ተማሪዎች በስነልቦናዊ አኳኋን ያላቸውን ፍላጎት ነው፡፡ አውዳዊ ፍላጎት ምናልባትም በአነስተኛ እውቀት ላይ የሚደገፍና ተማሪዎቹ ስለአውዱ ጠቀሜታ አዎንታዊ ዋጋ (positive value) ይሰጣሉ ተብሎ የግድ አይጠበቅም፡፡ ዝቅተኛ እውቀት ባለው ተማሪ ግፊት ላይ ተመርኩዞ አውዳዊ ፍላጎት ሊቀሰቀስ ይችላል፡፡ ለምሳሌ፡- አንድ ትምህርታዊ የቪድዮ ክሊፕ ለመመልከት የተያዘ ወቅታዊ ዝንባሌ፣ በአንድ ታሪክ ላይ የተመረኮዘ ስእላዊ መግለጫ የማቅረብ ስምምነት አውዳዊ ፍላጎትን መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ለምሳሌ ለታሪክ ትምህርት የተያዘ ግለሰባዊ ፍላጎት፣ በቋንቋ ትምህርት የንግግር ክሂል ላይ የተመረኮዘ የተግባቦት ምርጫ የሚያመለክቱት ተማሪዎቹ ለታሪክ እና/ወይም ለቋንቋ ትምህርቱ የንግግር ክሂል አስቀድሞ የተጠራቀመ እውቀትና በመረጃ ላይ የተመሰረተ ለተሳትፎ የሚረዳ አዎንታዊ ፍላጎት ያላቸው መሆኑን ነው፡፡ ይህ የተሳትፎ አዎንታዊ ፍላጎት ውስብስብ በሆኑ ተግባራትና ክንዋኔዎች ውስጥ በተነሳሽነት ለመሳተፍ ሁነኛ ጠቀሜታ እንዳለው ይታመናል (Gutherie & Cox, 2011)፡፡

በጥሩ ሁኔታ የጎለበተ የታሪክ ትምህርት ይዘት ፍላጎት ያለው ተማሪ በትምህርት አይነቱ ያለውን እውቀትና ግንዛቤ ይበልጥ እያጠለቀ በበለጠ ፍላጎት ትምህርቱን ለመቀበል ተነሳሽነት ይኖረዋል ተብሎ ይታሰባል (Gutherie & Cox, 2011)፡፡ በሁሉም መስፈርት በሚገባ የዳበረ የመማር ፍላጎት ያለው ተማሪ የመጠየቅ፣ የመከራከር፣ አቅጣጫ የመተለም፣ ተሳትፎ የማድረግ፣ ነገሮችን በጥልቀት የመመርመር፣ ወዘተ ስሜቶቹ ከፍ ያሉና

በውስብስብ ክንዋኔዎች ውስጥ በጽናት በመዝለቅ ስለሚማረው ትምህርት ይዘት የበለጠ ግንዛቤ ለመቅሰም ተነሳሽነቱ ከፍ ያለ ነው (Jacobs & Eccles, 2010)፡፡

ምንም እንኳን የመማር ፍላጎት በቤተሰብ ተጽእኖ ሊደረግበት የሚችል መሆኑ ባይካድም፤ የመማር ፍላጎት እድገት በተማሪዎች የመማሪያ ክፍል ውስጥ ተራክቧዊ ግንኙነት ሊሻሻል እንዲሁም ከማህበራዊ አካባቢ (environment) ጋር በሚካሄድ መስተጋብር ሊለወጥ ይችላል፡፡ ነገሮችን በቀመራዊ /ሂሳባዊ/ አተያይ የመገንዘብ፣ የመጠየቅና ማጠቃለያ የመስጠት አሰራርን የሙጥኝ ሊሉ የሚችሉ አንዳንድ ተማሪዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ይህም መምህራን ተማሪዎቹ የቀረበውን ይዘት ለመረዳት የተጓዙበትን መንገድ ለይቶ ለማወቅ እንዲሁም ተማሪዎች ያሉዋቸውን መረጃ የመቀበያ የተለያዩ ፍላጎቶች በሚገባ ለማጤን ያስችላቸዋል (Mitchell, 2003)፡፡

አብዛኛውን ጊዜ አውዳዊ ፍላጎቶች ጨርሶ ወደ ግለሰባዊ ፍላጎትነት የመለወጥ እድል የላቸውም፡፡ ፍላጎትን ለማሳደግ የሚረዱ ሁኔታዎች አሉ፡፡ ተማሪዎች ወደ መማሪያ ክፍል ይዘው የሚመጧቸው ልምዶችና አካባቢያቸውን ለመረዳት የሚከተሉት መንገድ ፍላጎትን ለማሳደግ ከሚያገለግሉ ሁኔታዎች መካከል ይካተታሉ፡፡ ተማሪዎች አስቀድሞ በውስጣቸው ያካበቱት ልምድ፣ ግለሰባዊ ምርጫ፣ ስለሁኔታዎች ያላቸው አተያይ ፍላጎትን ለመገንባት ጠቀሜታ አላቸው፡፡ አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ሁሉም ተማሪዎች ማለት ይቻላል አውዳዊ ፍላጎትና ግለሰባዊ ፍላጎት ይዘው ይገኛሉ (Murphy & Alexander, 2000)፡፡ ከዚህም ባሻገር እንዲህ አይነቶቹ ፍላጎቶች በተማሪዎቹ ሌሎች ፍላጎቶች መካከል ጣልቃ ገብተው የመከሰት እድል አላቸው፡፡ ለምሳሌ፡- ‹‹ሀ›› የተባለ ተማሪ ለእግር ኳስ፣ ለማንበብና ከጓደኞች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ዙሪያ በሚገባ ያደገ ፍላጎት አለው፡፡ በተጨማሪም ‹‹ሀ›› 10ኛ ክፍል ባዮሎጂ ሲማር የእንስሳትን ባህርያት በመለየት ፕሮጀክት አውዳዊ ፍላጎት /ግፊት/ ተፈጠረበት (Murphy & Alexander, 2000)፡፡ አውዳዊ ፍላጎቱ በነባሮቹ ለእግር ኳስ፣ ለማንበብና ከጓደኞች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ግለሰባዊ ፍላጎቶቹ መካከል የተፈጠረ አዲስ ፍላጎት ሆነ ማለት ነው፡፡ የተማሪ ‹‹ሀ›› ኬዝ ጥናት በሚከተሉት ነጥቦች ሊጠቃለል ይችላል፡፡ (1) የ‹‹ሀ›› ፍላጎታዊ ልምድ በተማሪው ፍላጎትና ውጤታማነት ግንኙነት ሊገለጽ ይችላል፤ (2) ይህ የፍላጎትና ውጤታማነት የምክንያትና ውጤት ግንኙነት ለተነሳሽነት (motivation) ጥናት እንደመነሻ ሊያገለግል ይችላል፤ እና

(3) ይኸው የፍላጎትና ውጤታማነት የምክንያትና ውጤት ተዛምዶ ለፍላጎት እድገት ምቹ እድል መፍጠር መቻሉን መገንዘብ ተገቢ ይሆናል (Murphy & Alexander, 2000)፡፡

### 2.1.7 በቋንቋ መማሪያ አውድ ፍላጎትን በተማሪዎቹ ዘንድ ለማስረጽ የቋንቋ መምህራን ሚና

ለሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ ክፍል የመምህሩ የአመራር ሚና ለተማሪዎች ፍላጎት መንሰራራት አይነተኛ ጠቀሜታ ያለው ነው፡፡ በዚህ ምክንያት መምህሩ ያልተቋረጠ የድጋፍ ሚና የመማር ማስተማሩን ሂደት በፍላጎት እንዲታገዝና ይበልጥ አነቃቂ እንዲሆን ያግዛል፡፡ በፍላጎት ማጠናከሪያ ስልቶች በሚገባ የተካኑ የቋንቋ መምህራን ትኩረት ማድረግ የሚገባቸው የተማሪዎችን ፍላጎቶች ከመንከባከብ ባሻገር ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋቸውን በፍላጎትና ተነሳሽነት እንዲማሩ አስፈላጊውን ጥረትና እገዛ ሁሉ ማድረግ ነው (Wright, 2016)፡፡

የተለያዩ የዘርፉ ምሁራን እንደሚገልጹት ሁሉም አእምሯዊ ተግባራትና ክንዋኔዎች በፍላጎት ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ መምህሩ በተለይ ከሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ አውዱ ጋር በተያያዘ የሚያካሂዳቸው ግሬቶች፣ አነሳሽነቶች፣ የሚያቀርባቸው ሞዴሎችና ምሳሌዎች በተማሪዎቹ ዘንድ መነሳሳት ለመፍጠር የሚያስችሉ በሚገባ የተደራጁ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ከስነልቦናዊ ዘውግ አኳያ ተማሪዎቹ በውስጣቸው በሚገባ ስርአት ያልያዘ የቋንቋ መገንዘብ ፍላጎት አላቸው፡፡ ስለሆነም የቋንቋ መምህሩ ይህን የተማሪዎቹን ስርአት ያልያዘ ፍላጎት መነሻ በማድረግ ተማሪዎቹ ሁለተኛ ቋንቋውን በንቁ ተሳትፎና ተነሳሽነት እንዲማሩ በማድረግ የቋንቋ መማሩን ሂደት እንዲቆጣጠሩት ቢያደርግ ጥሩ ይሆናል፡፡ ለዚህም የመምህሩ የአመራር ሚና ከዚህ በታች በተጠቀሱ ዝርዝር ጉዳዮች ላይ አጽንኦት ማድረጉ ለውጤታማነት ይረዳል (Huang, 2011)፡፡

#### 2.1.7.1 ተማሪዎቹ የቋንቋ መማር አስተሳሰብ እንዲያዳብሩ ማድረግ

ምንም እንኳን ተማሪዎች ምሉእ የሆነ አትኩሮት ያላቸው ሆነው ቢገኙም ለረጅም ጊዜ በተግባራት ላይ አትኩረው የመስራት ተመሳሳይ ፍላጎት ይዘው ላይገኙ ይችላሉ፡፡ የቋንቋ መምህሩ ይህን በመገንዘብ ተማሪዎቹ የትምህርቱን አላማ፣ ለተማሪዎቹ የሚያስገኘውን ጠቀሜታ፣ ተግባሩን የሚያከናውኑበትን ብልሃትና ከእያንዳንዳቸው የሚጠበቁ የተሳትፎ

ግንኙነቶች አስቀድሞ በመግለጽ በተማሪዎቹ ዘንድ አስፈላጊውን ቅድመ ግንዛቤ በመፍጠር ፍላጎታቸውን ቢያነሳሳ ጥሩ ተሳትፎና ውጤታማ ተራክቦ ለማካሄድ ያስችላል (Huang, 2011)፡፡

### 2.1.7.2 ተማሪዎች በእውቀትና ክህሎት ሊደርሱበት የሚገባ ፍላጎትን በውስጣቸው ማስረጽ

John Locke በአንድ ወቅት እንደገለጸው፣ ‹‹ፍላጎት በሌለበት ጠንካራ ተግባር ሊኖር ከቶ አይችልም፡፡›› በዚሁ መሰረት ተማሪዎች ጊዜና ነባር ልምዶቻቸውን በአግባቡ በመጠቀም ራሳቸውን ችለው እንዲማሩ፣ ፈጠራዊ በሆነ መንገድ ችግሮችን እንዲፈቱ፣ የተበረታታ የክፍል ውስጥ ተሳትፎና የገሃዱ አለም መስተጋብራዊ ልምምዶችን በተነሳሽነት እንዲያከናውኑ ማበረታታትና ማትጋት አስፈላጊ ይሆናል (Gu, 2010)፡፡

### 2.1.7.3 ተማሪዎች የሚደረስባቸው የቋንቋ መማር ግቦችን እንዲያስቀምጡ ማበረታታት

የሚደረስባቸው እውነተኛ /ተጨባጭ/ የቋንቋ መማር ግቦችን ማስቀመጥና እነዚህን ትምህርታዊ ግቦች በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ለመጨበጥ የሚደረግ ትምህርታዊ እንቅስቃሴ በተማሪዎች አስተሳሰብ ውስጥ የመማር ፍላጎትን ለማስረጽ ቁልፍ ጠቀሜታ አለው፡፡ ተማሪዎች ግቦቻቸውን የመዳረሻ ነጥባቸው ማገናዘቢያ አድርገው በትኩረት በመመልከት ከተቀመጡት ግቦች ትይዩ ትምህርታዊ እርምጃ እንዲያሳዩ ውስጣዊ ግፊትና ተነሳሽነት ይፈጥርላቸዋል (Gu, 2010)፡፡ በመሆኑም የቋንቋ መምህራን በቋንቋ ትምህርቱ መጀመሪያ ተጨባጭ ሊሆኑ የሚችሉ ትምህርታዊ ግቦችን በመርሐ-ትምህርቱና በተማሪዎቹ የቋንቋ መማር ፍላጎቶች ላይ ተመርኩዞ ተማሪዎቹን ባሳተፈ መልኩ ቢቀርጽ ተማሪዎቹ የስኬት አስተሳሰብ እንዲይዙ፣ አስቀድሞ ከሚሰሩት የተሻለ እንዲሰሩና በመማር ማስተማሩ ሂደትም የበለጠ ተሳታፊ ሊሆኑ እንደሚችሉ ይታሰባል (Huang, 2011፤ (Kolb & Kolb, 2009፤ McClanaghan, 2008)፡፡

#### 2.1.7.4 ተማሪዎች በራስ የመተማመን ስሜት እንዲገነቡ ማበረታታት

በብዙ የዘርፉ ምሁራን ዘንድ የጋራ መግባባት ላይ የተደረሰበት ጉዳይ በራስ መተማመን ለከፍተኛ ውጤታማነት እንደ ድልድይ የሚያገለግል መሆኑ ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ተማሪዎች በራስ የመተማመን አስተሳሰብ ይዘው የሚገኙ ከሆነ ውጤታማነት /ስኬታማነት/ አይቀሬ መዳረሻቸው ይሆናል፡፡ ይሁንና ቤት በአንድ ሌሊት ተገንብቶ እንደማይጠናቀቅ ሁሉ በራስ የመተማመን አስተሳሰብም በአንዴ የሚጨበጥ ጉዳይ አይደለም፡፡ በራስ መተማመን በአጭር ጊዜ የሚደረስበት ግብ ባይሆንም ለተማሪዎች የመማር ሰብእና መገንባት እጅግ አስፈላጊ ግብአት ነው (Kolb & Kolb, 2009፣ McClanaghan, 2008)፡፡ ከሁሉም በፊት የቋንቋ መምህራን ራሳቸው ለተማሪዎች መልካም ምሳሌ /ሞዴል/ በመሆን በራስ የመተማመን ሰብእናን እንዲላበሱ አነሳሽ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የቋንቋ መምህራኑ ስኬታማ ለመሆን የሚያስችሉ እድሎችና አማራጮችን እንዲለማመዱ ለማድረግ የሚያስችሉ የግንኙነት አውዶችን በመተግበር ያሉዋቸውን ችሎታዎች እንዲያሳዩ ፍላጎታቸውን ማንሰራራት አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በመጨረሻም መምህራን ለተማሪዎቻቸው ልዩ ልዩ ችሎታዎች እውቅና መስጠትና መሸለም እንደ አንድ የማበረታቻ ስልትም፣ ጠቃሚ የሆነ በራስ መተማመን የመገንቢያ መንገድም ነው (Wright, 2016)፡፡

#### 2.1.7.5 በመምህሩና በተማሪዎች መካከል አዎንታዊ ግንኙነት መፍጠር

ተማሪዎች በትምህርቱ ሂደት ላይ ከፍ ያለ ፍላጎት የሚያሳድሩት ከመምህሩ ጋር ጤናማ የሆነ ግንኙነት ሲኖራቸው ነው፡፡ የተማሪዎች የመማር ፍላጎት ከመምህሩ ጋር ባላቸው ግንኙነት ጤናማነት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ተማሪዎች መምህራቸውን የሚያደንቁ ከሆነ የመምህሩን ትምህርት ይወዱታል፤ በዚህ የተነሳ የሚቀርቡትን ይዘቶች በመማር ፍላጎት ታግዘው ይቀስማሉ፡፡ በመሆኑም መምህራን በተቻላቸው አቅም ከተማሪዎች ጋር መልካም የሆነ ግንኙነትን በመጠበቅ፣ በመተማመን፣ በመከባበር፣ በመዋደድ የመማሪያ አውዱን ለቋንቋ ትምህርት ፍላጎት መንከባከቢያነት ማዋል ይኖርባቸዋል (Fine, 2003፣ Tomlinson, 2007)፡፡

### 2.1.7.6 የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ለማንሰራራት የሚረዱ አዳዲስ የማስተማሪያ ብልሃቶችን መተግበር

በተወሰነ መልኩ በእርግጥ አብዛኛዎቹ ልማዳዊ የማስተማሪያ ሞዴሎች የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ለመንከባከብና ለማጎልበት ጠቀሜታቸው ያነሰ መሆኑን በርካታ ጥናቶች ያመለክታሉ (Gu, 2010፣ Jacobs & Eccles, 2010፣ Barron & Harackiewicz, 2000)፡፡ ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተቀምጠው በአብዛኛው ንቁ አዳማጭ በመሆን እንደ ባዶ ጠርሙስ የሚንቆረቆርላቸውን ብቻ መቀበል ጠቀሜታውና ውጤታማነቱ ያነሰና ኢ-ንቁ የሚያደርጋቸው ነው፡፡ በመሆኑም ተመራማሪዎች የተለያዩ አዳዲስ /ምትክ/ የማስተማሪያ ዘዴዎችንና ብልሃቶችን በመቀየስ የመማር ሂደትን አሳታፊና ተራክቦአዊ ለማድረግ ሞክረዋል (Fine, 2003፣ Tomlinson, 2007)፡፡ ማህበረሰብ በማያቋርጥ የእድገት ሂደት በመለወጥ ላይ እንደመገኘቱ ሁሉ የማስተማሪያ ዘዴዎችም ከዚሁ ለውጥ ጋር ተያይዘው በመሻሻል ላይ ይገኛሉ፡፡ በዚህም የተነሳ የቋንቋ መምህራን እነዚህን አዳዲስ የቋንቋ መማሪያ ሞዴሎች በመተግበር የቋንቋ መማሪያ አውዱን አስደሳችና መስህባዊ አድርገው ለተማሪዎቻቸው ማቅረብ ይኖርባቸዋል (Gu, 2010፣ Jacobs & Eccles, 2010፣ Barron & Harackiewicz, 2000)፡፡ የተለያዩ በቋንቋ መማሪያ አውድ ፍላጎትን ከፍ በማድረግ ተማሪዎችን ውጤታማ ለማድረግ ጠቀሜታ ያላቸው ብልሃቶች በዘርፉ ምሁራን ቀርበዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል በመደጋገፍ መማር፣ ብጤን ማስተማር እና ማነቃቃት የመሳሰሉት ናሙና ብልሃቶች የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ለማነሳሳት ባላቸው ቀጥተኛ ድጋፍ እዚህ መጠቀስ አስፈልጓል፡፡

ሀ) *የቃላት ጫወታ፡-* የቃላት ጫወታ በማስመሰል ላይ ተመስርቶ ፍላጎትን ከፍ ለማድረግ የሚቀርብ መማሪያ ብልሃት ነው፡፡ የጫዋታ ህግጋትና ውሳኔዎችን አስቀድሞ በማብራራት የጨዋታውን አሸናፊ መለያ ነጥቦችን በግልጽ ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡ በሚገባ የተደራጀ የቃላት ጫዋታ ተማሪዎች ረቂቅ ሀሳቦችን በቀላሉና በፍጥነት በመተግበር የንግግር ክሂል፣ ውሳኔ የመስጠት እና አስመስሎ ሚና የመጫወት ችሎታዎችን እንዲያዳብሩ ለማድረግ አስተዋጽኦ አለው (MOE, 2004፣ ICDR, 2009)፡፡

*ለ) የፕሮጀክት ክንዋኔ፡-* የፕሮጀክት ክንዋኔ ከህይወት ተሞክሮ መማርን መሰረት ያደረገ ሲሆን ግላዊና ማህበራዊ ችግሮችን ማቃለል ላይ ያተኮረ የቡድን ሥራ ነው፡፡ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያልቀረቡ አካባቢያዊ የአኗኗር ገጽታዎችን ናሙና ወስዶ ለመፈተሽ

ጠቀሜታ ያለው ነው፡፡ በዚህ ብልሃት ሊካተቱ የሚችሉ ፍላጎት አነሳሽ ተግባራትን መምህሩ መርጦ በማቅረብና ተማሪዎቹ እንዲመረምሩ በማድረግ ተማሪዎች በታቀደ መልኩ በጥንቃቄ እንዲሰሩና ውጤቱን እንዲያቀርቡ ሊያደርጋቸው፤ የተሻለ የሰሩ ቡድኖችን በመምረጥ ሊያበረታታ ወይም እውቅና ሊሰጥ ይችላል (MOE, 2004፣ ICDR, 2009)፡፡

*ሐ) ሚና ጫወታ፡-* ሚና ጫወታ አንዱ የተማሪዎችን ፍላጎት ለመያዝ የሚረዳ ማስተማሪያ ብልሃት ሲሆን ትኩረቱ ተማሪዎች አስመስለው እንዲያከናውኑ ማድረግ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ቃለመጠይቅ አቅራቢና ቃለመጠይቅ ሰጪ፣ ወላጆችና ልጆች፣ ሐኪም እና በሽተኛ፣ አለቃና ሰራተኛ፣ ወዘተ ሚናዎችን ተማሪዎች አስመስለው ሊተውኑ ይችላሉ፡፡ ይህ ዘዴ በአብዛኛው የትምህርቱን ይዘት ተውኔታዊ ተግባቦታዊ አድርጎ ለማቅረብ አጋዥነቱ ከፍ ያለ ሲሆን የትምህርቱን ሂደትም እየተዝናኑ እንዲማማሩበት ለማድረግም ጠቀሜታ ያለው ነው፡፡ በአብዛኛው የእውኑ አለም ግልባጭ የሆኑ ድርጊቶችና ግንኙነቶች ተሰናድተው የሚቀርቡበት እድል ሰፊ ነው፤ ይህም ትምህርቱን ትውስታ ፈጣሪ ወይም አይረሴና አዝናኝ ለማድረግ ይረዳል፡፡ ሆኖም በሚና ጫዋታ የሚቀርበው ትምህርት በመጫወት ለመማር እንጂ ጫዋታ ብቻ ላይ ያተኮረ እንዳይሆን መምህሩ በቅድመ-ዝግጅት ወቅት አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል (MOE, 2004፣ ICDR, 2009)፡፡

*መ) ለችግሮች መፍትሔ በማቅረብ መማር፡-* ችግር ፈቺ የማስተማሪያ ብልሃት የተማሪዎችን ፍላጎት ለማነሳሳት ከሚረዱ ብልሃቶች አንዱ ነው፡፡ ICDR (2009) እንዳቀረበው፣ በችግር ላይ ተመስርቶ የሚቀርብ ክፍተትን ለመሙላት የሚቀርብ ብሎም ውጤቶችንና የመፍትሄ አማራጮችን ለመጠቆም የሚረዳ ክንውን ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ውጤቱ ወይም መፍትሄው የችግሩን ክፍተት መሙላትን ታሳቢ አድርጎ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ በዚህ የተነሳ ይህ ሂደት ‹‹ዘዴ--ውጤት ትንተና›› (means-ends analysis) ተብሎ ይጠራል፡፡ በዚህም የተነሳ ችግር ፈቺ ፍላጎት ተኮር ብልሃት ተማሪዎቹ በሚገኙበት የክፍል ደረጃ ባላቸው የእውቀት ክፍተት ላይ ተመስርተው የሚፈለገውን አዲስ እውቀትና ክህሎት ለመጨበጥ እንዲችሉ ያግዛቸዋል (ICDR, 2009)፡፡

*ሠ) እርስ በእርስ በመደጋገፍ መማር፡-* በMOE (2004፣ 94) እንደተገለጸው፣ በመደጋገፍ መማር ተማሪዎች ትንንሽ ቡድኖችን መስርተው እርስ በርስ በመማማር የራሳቸውን

መረዳት ከፍ ለማድረግም ሆነ ሌሎች እንዲረዱ ለማገዝ አብረው የሚሰሩበት አውድ ነው፡፡ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ድግግሩዊ መማር በአዎንታዊ አቻዊ ግንኙነትና እርስ በእርስ መደጋገፍ ከፍ ወዳለ የመማማር ውጤታማነት ለመድረስ የሚያግዝ ብልሃት ነው፡፡

*ረ) ብጤን ማስተማር፡-* ብጤን ማስተማር አንዱ አሳታፊ ማስተማሪያ ብልሃት ሲሆን በዚህ ብልሃት በመታገዝ ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ አቻዎቻቸውን በማስተማር ሂደት ራሳቸውም እውቀት እንዲገበዩ የሚደረግበት ፍላጎትን ከፍ ለማድረግ ጠቃሚ ሂደት ነው፡፡ ይህ ስልት ተማሪዎች የግል ተሞክሮዎቻቸውን ከጥልቅ መረዳት ጋር ለማጣመር የሚረዳቸው ነው፡፡ ስልቱ ተማሪዎች ከመምህራቸው ግብረ-መልስ ማግኘት እንዲችሉ ተደርጎ መደራጀት ይኖርበታል (ICDR, 2009)፡፡

*ሰ) ማነቃቃት፡-* ማነቃቃት ተማሪዎች ሀሳብ ማመንጨት እንዲችሉ ለማድረግ በሰፊው ታዋቂ አገልግሎት ያለው ብልሃት ነው፡፡ ተማሪዎች በማነቃቃት በተደገፈ የመማር ክንዋኔ በርካታ የተለያዩ ሀሳቦችን በአጭር ጊዜ ሊያመነጩ ይችላሉ (Fine, 2003፣ Tomlinson, 2007)፡፡ ማነቃቃት ተማሪዎች በአንድ የተወሰነ ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ ሀሳቦቻቸውን በነጻነት እንዲያንጸባርቁ ለማድረግ እንዲሁም መምህሩ ተማሪዎቹ በቀረበው ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ ያላቸውን የቀደመ ግንዛቤ ለማወቅ ይረዳል፡፡ ከማነቃቃት ብልሃት ትግበራ ጋር ተያይዞ መታወቅ ያለበት በተማሪዎቹ የሚሰጡ አስተያየቶችን ሁሉ መቀበል፣ በአስተያየቶች ላይ ትችት ከማቅረብ መቆጠብ፣ አንዱ አስተያየት ሰጪ ተማሪ ሌላው ተማሪ በሰጠው አስተያየት መነሻ የማዳበሪያ ሀሳብ ሊያቀርብ መቻሉ እንዲሁም ይህ ክንዋኔ ከ10 ደቂቃ የበለጠ ጊዜ መውሰድ የሌለበት መሆኑን ነው (Bainbridge, 2014፣ Tomlinson, 2005፣ Tomlinson, 2007)፡፡

### 2.1.7.7 የተለያዩ ቋንቋ ነክ ተግባራትን መገልገል

በሰፊው እንደሚታወቀው መማሪያ ክፍል የቋንቋ ልምምዶችን ለማካሄድና ለመማር ዋንኛው ስፍራ ነው፡፡ በመሆኑም መምህራን ከልማዳዊው ማስተማሪያ ዘዴ ተላቀው ልዩ ልዩ አውዳዊ ተግባራትና ክንውኖችን ለተማሪዎቹ ማቅረብ፣ አገላለጾችንና ድርጊቶችን በድርጊት ጭምር እንዲለማመዱ ማድረግና ተማሪዎችን ማነቃቃት ይኖርባቸዋል ((Kolb & Kolb, 2009፣ McClanaghan, 2008፣ Tomlinson, 2005)፡፡ የቋንቋ ትምህርት ዋንኛ ግብ የተማሪዎችን ተግባቦታዊ ችሎታ ማሳደግ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ተግባቦት የሚገለጸው በቋንቋ መማሪያ አውዱ ከሚቀርቡ ተግባራት ጋር በመቀናጀት መሆን ይኖርበታል፡፡ መስህባዊ የሆኑ የቋንቋ ተግባራት ተማሪዎቹ በማስመሰል፣ ሚና በመጫወት፣ ተግባቦት በማካሄድ፣ ወዘተ ተማሪዎቹን ለማሳተፍ ይረዳሉ፡፡ ይህም የተማሪዎችን የቋንቋ ብቃትና ተፎካካሪነት ለማሳደግ አይነተኛ አስተዋጽኦ አለው (Wright, 2016፣ Huang, 2011)፡፡ ይህም ቀደም ሲል በ ICDR (2009) እና MOE (2004) የቀረቡትን ሃሳቦች የሚያጠናክር ነው፡፡

### 2.1.7.8 ለተማሪዎች እውቅና መስጠትና መሸለም

Lincoln የተባለ አዋቂ እንደገለጸው ‹‹እያንዳንዱ ሰው ሽልማት መፈለጉ የሰው ተፈጥሮአዊ ባህሪ ነው፤ በጣም የሚሳበው ግን ለአድናቆት ነው፡፡›› ተገቢ የሆነ እውቅና በራሱ እንደሽልማት የሚቆጠር ነው፡፡ በተለይ ለተማሪዎች በራስ የመተማመን ችሎታቸውን ከፍ ያደርግላቸዋል፤ የመማር ፍላጎታቸውን ለማነሳሳትም መጠነ ሰፊ ጠቀሜታ አለው፡፡ ቀጣይ የሆነ የማበረታቻ ስልት መኖር ተማሪዎች በደስተኛነት መንፈስ ለውጤታማነት በይበልጥ እንዲሰሩ ፍላጎት ይፈጥርባቸዋል (Wright, 2016፣ Huang, 2011)፡፡

### 2.1.8 ማበረታቻን ለቋንቋ መማር ፍላጎት ግብአት የማድረግ ጠቀሜታ

ጥናቶች እንደጠቆሙት፣ ማበረታቻ ለተማሪዎች የመማር ፍላጎት መጎልበት እጅግ ጠቃሚ አስተዋጽኦ ያለው መሳሪያ ነው፡፡ የማበረታቻ ስልቶች ለተማሪዎች ንቁ መማር ግብአት በሚደረጉበት አውድ የተማሪዎችን ኢ-ንቁነት ባህሪን በማስወገድ አለያም በመቀነስ ለሚማሩት ትምህርት የተሻለ አስተውሎት ወይም ትኩረት እንዲሰጡ ያግዛል፡፡

በማበረታቻ ስልቶች በሚገባ የታገዙ ተማሪዎች በሰፊው ይነቃቃሉ፤ ይበረታታሉ፤ ለመማርም ጉልህ ትኩረት ይሰጣሉ፡፡ የተማሩትን የማስታወስ ችሎታቸው መሻሻል ስለሚያሳይ ውጤታማ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል (Bainbridge, 2014፣ Tomlinson, 2005፣ Tomlinson, 2007)፡፡

በተመሳሳይ በማበረታቻና ተማሪዎች በተፈጥሮ የታደሏቸው የመማሪያ ስልቶች (learning styles) መካከል ጠንካራ ቅንጅት አለ፡፡ በመማር ልምምድ ወቅት እነዚህን የመማሪያ ስልቶች እንደ ምርጫቸው ለመጠቀም ተነሳሽ ስለሚሆኑ መበረታታን ይጨምርላቸዋል (Fine, 2003፣ Tomlinson, 2007)፡፡ ምንም እንኳን በሰፊው የተለመዱት መምህራንና አጠቃላዩ የትምህርት ስርአት የማበረታቻ ትኩረት የተማሪዎችን ተፈጥሯዊ ችሎታ ለመመዘን በሚረዱ መደበኛ መለኪያዎች (grades) መሆኑ ቢታወቅም የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ለማጎልበት የሚረዱ ስልቶችን ማመቻቸትና ማቀናጀት ተገቢ ነው (Honigsfeld & Schiering, 2004፣ Winger, 2005)፡፡ በእርግጥ ማበረታቻ የመምህራኑን የማነቃቂያ ስልቶች ብቻ የሚመለከት ሳይሆን የተማሪዎች ራስን በራስ የመመዘንና ከውጤት በፊት የመማር ሂደትን በራሳቸው ለመቆጣጠር የሚያሳዩትን ተሳትፎና ጥረት ጭምር ማካተትን ይጠይቃል፤ ይህም የመማር ፍላጎትን ለማጠናከር የበኩሉ አስተዋጽኦ አለው (Bainbridge, 2014)፡፡

ተማሪዎች በሰፊ ጥረታቸው ታግዘው፣ በልዩ ልዩ ተግባራትና ልምምዶች ታግዘው ተምረው የሚያገኙት ከፍተኛ ውጤት ይበልጥ ደስተኛ እንዲሆኑና እንዲበረታቱ ያደርጋቸዋል (Tomlinson, 2005)፡፡ ይህም ቀጣይ ለሆነ የረጅም ጊዜ የመማር ፍላጎትና ተነሳሽነት ገንቢ አስተዋጽኦ አለው፡፡ የረጅም ጊዜ የመማር ፍላጎትና ተበረታችነት በአካዳሚኩ መስክ ቀጣይነት ያለው አእምሯዊ እድገትና መሻሻል ለማሳየት እንዲሁም እውቀትና ክህሎትን ለመገብየት ጉልህ አስተዋጽኦ ይኖረዋል (Bainbridge, 2014፣ Tomlinson, 2005)፡፡ እውቀትና ክህሎትን የመገብየት ሂደት ተማሪዎች እንዴት መማር እንዳለባቸው ማወቅንና መበረታታትን ይጠይቃል (Kolb & Kolb, 2009፣ McClanaghan, 2008)፡፡ ስለዚህ በመማር ጥረታቸው የተበረታቱ ተማሪዎች ስለ መማር ሂደት ሰፊ ግንዛቤና ተግባራዊ ተሞክሮ ይኖራቸዋል፤ በአካዳሚክ ተግባሮቻቸው ከሌሎች መሰሎቻቸው በጣም በተሻለና ውጤታማ በሆነ መልኩ የተለያዩ ክንዋኔዎችን በብቃት የመወጣት ባህሪም ያዳብራሉ (Kolb & Kolb, 2009፣ McClanaghan, 2008)፡፡

## 2.2 የፍላጎት ንድፈ-ሀሳባዊ መሰረቶች

የ Hidi እና Renninger ባለ አራት ገጽታ የፍላጎት እድገት ሞዴል የተሟላ እና በሰፊው እውቅና ያገኘ የቀለም ትምህርትን ፍላጎት መሰረተ-ሃሳብ የሚያሳይ ንድፈ-ሃሳባዊ ሞዴል ነው፡፡ የፍላጎት ጥናት ፈር ቀዳጅ የሆነው Herbart (1776—1841) ፍላጎትን ከቀለም ትምህርት ጋር በማያያዝ ለትምህርት አላማ ግባዊነት ካለው ጠቀሜታ አንጻር ካመላከተ በኋላ፣ በርካታ የዘርፉ ተመራማሪዎች ፍላጎት ለተማሪዎች ውጤታማነት ያለውን አስተዋጽኦ ሲፈትሹ ቆይተዋል፡፡ በዚሁ መሰረት በበርካታ አጥኚዎች ፍላጎት የተማሪዎችን ብቃት፣ ቅልጥፍና፣ ጥረት ከፍ ለማድረግ፣ የትምህርት ተሳትፎን ለማጠናከር፣ የመማር ቀጣይ ተነሳሽነትን ለመጠበቅ ያለው ጠቀሜታ እውቅና ተሰጥቶታል (ምሳሌ፡- Guo & Zhang, 2012፣ Walkington & Sherman, 2013፣ Tomlinson, 2007)፡፡

በምእራባውያን ዘንድ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ደረጃና የውጤት ተዛምዶ ለመለካት የሚያገለግሉ በርከት ያሉ ግለ-መሳሪያዎች (self-report instruments) ተዘጋጅተው በስራ ላይ ውለዋል፡፡ ከእነዚህ አብዛኛዎቹ መለኪያዎች /ስኬሎች/ ውስን በሆነ መልኩ ስሜታዊነትን (emotion) ወይም የዋጋማነት ምንዝሮች (value components) በመማር ፍላጎት ያለውን ተጽእኖ ለመፈተሽ የረዱ ናቸው (Hidi & Harackiewicz, 2008)፡፡

የመማር ፍላጎት ልዩ የሆነ መነቃቃት ላይ የሚመሰረት ተላውጦ ሲሆን ተማሪዎች የሚወዱት ወይም የሚመርጡት የመማሪያ ይዘትና ግብአትን ከተወሰነ የትምህርት ግብ፣ ተግባርና ልምምድ ጋር አሰናኝቶ ለተማሪዎቹ ስነልቦናዊ ዝግጅት በሚመጥን ቅንጅት ማቅረብን የሚጠይቅ አሰራር ነው (Hidi and Renninger, 2006)፡፡ በሰው--ቁስ (person-object) ንድፈ-ሃሳብ መሰረት የፍላጎት እድገት ጽኑ መሰረት በወቅቱ የሚካሄደው የሰውና ቁስ የአውድ መስተጋብር ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር ፍላጎት ሁኔታዊ (situational) እና ግለሰባዊ (individual) ፍላጎት ተብሎ በሁለት ፈርጆች ይከፈላል (Justina, 2015፣ Hidi, 2010)፡፡ ሁኔታዊ ፍላጎት አውድ ተኮር በሆነ መልኩ ለቀረበው ጉዳይ ትኩረት መስጠትንና ስሜታዊ በሆነ መንገድ መስተጋብር ለማካሄድ የተያዘ ፍላጎትን ያመለክታል (Hidi, 2010፣ Hidi and Renninger, 2006)፡፡ በሌላ በኩል ግለሰባዊ ፍላጎት ደግሞ ለአንድ የተወሰነ ይዘት ቀጣይነት ያለው ፍላጎት ይዞ መገኘትን የሚወክል ብያኔ ነው፡፡ ግለሰባዊ ፍላጎት

ከአውዳዊ ፍላጎት በመነሳት /በመመንጨት/ በየጊዜው የሚያድግ ባህሪ ነው (Hidi and Renninger, 2006)፡፡ በዚሁ መሰረት ምንም እንኳን ግለሰባዊ ፍላጎት ለብዙ ጊዜ የሚቆይ ባህሪ ቢሆንም፣ ሁለቱም የፍላጎት አይነቶች አዎንታዊ በሆነ መልኩ የተማሪዎችን የመማር ትኩረት ለመሳብ፣ አእምሮአዊ ክንውኖችን ለማሳለጥ እና የሚያከናውኑትን ተግባር እንዲወዱት በማድረግ ረገድ ገንቢ ተጽእኖ ያላቸው ናቸው (Hidi, 2010፣ 2013)፡፡

የተማሪዎች የመማር ፍላጎቶች የሚገለጹባቸው በርካታ የመማር ፍላጎት ስያሜዎች (ለምሳሌ፡- ስነ-ትምህርታዊ፣ ግለሰባዊ፣ ግላዊ፣ አእምሮታዊ) በመባል በተወሰነ መልኩ እርስ በርስ በመተካካት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ቀደምት ጥናቶች ትኩረት ያደረጉት የትምህርት አይነቶች አጠቃላይ ፍላጎት ላይ ነው፡፡ ይሁንና ተማሪዎች ከሚቀርቡላቸው የትምህርት አይነቶች በአብዛኛው በአንዳንዶቹ ላይ ከሌሎቹ በተሻለ ሁነኛ ፍላጎት ያሳያሉ፡፡ በዚህ የተነሳ ባለንበት ዘመን የቀረቡ ጥናቶች በመማር ፍላጎት ላይ አጽንኦት የሚያደርጉት ክፍለ እክብ ማእቀፍ (domain-specific construct) በመፍጠር ነው (Walkington & Sherman, 2013፣ Justina, 2015)፡፡ ይህም ዘመኑ የደረሰበትን የፍላጎት አስተሳሰብ የሚያመለክት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ሂሳብ የመማር ፍላጎት፣ እንግሊዝኛ የመማር ፍላጎት፣ በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ፍላጎት፣ የአማርኛ ግጥሞችን የማንበብ ፍላጎት፣ ወዘተ እያልን የተማሪዎችን ፍላጎት መተንተን እንችላለን ማለት ነው፡፡ በዚህ መሰረት የዚህ ጥናት ንድፈ-ሃሳባዊ መሰረት በመማር ግለሰባዊ ፍላጎት ላይ የተዋቀረ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም የመማር ግለሰባዊ ፍላጎት ከአውዳዊ ፍላጎት ተነስቶ /መንጭቶ/ ያደገና የደረጀ ፍላጎት በመሆኑ በተማሪዎቹ ዘንድ በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል የተያዘውን ፍላጎት ለመተንበይ ስለሚያስችል ነው፡፡

አራት የፍላጎት ዘርፎች ሞዴሎችና በሞዴሎቹ የታቀፉ አላባዎች በHidi and Renninger (2006) ጎልብተዋል፡፡ ይህ በእነ Hidi የተዘጋጀው የፍላጎት ዘርፎች ሞዴል የተሟላና በሰፊው በስራ ላይ የዋለ ብሎም የመማር ፍላጎት ደረጃን የሚያሳይ በመሆኑ ነው፡፡ የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ በአውዳዊ ፍላጎት ዘርፍ የሚካተቱ ንኡሳን ዘርፎች የአውዳዊ ፍላጎት አነሳሾች (triggered situational interest) እና በእንክብካቤ የተደገፈ አውዳዊ ፍላጎት (maintained situational interest) ናቸው፡፡ በአውዳዊ ፍላጎት ዘርፍ የተካተቱት እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ዘርፎች በአካባቢያዊ አነሳሽ /አነቃቂ/ ሁኔታዎች የሚደገፉ፣ ለጊዜው ብቻ የሚቆዩና በሌሎች ኃይሎች /ለምሳሌ መምህራን፣ ወላጆች፣ የክፍል ቴስት፣

የሴሚስተር ፈተና፣ ብሄራዊ ፈተና፣ ወዘተ/ የሚገፋፉ ፍላጎቶች ናቸው (Hidi and Renninger, 2006)፡፡ በሌላ በኩል የመጨረሻዎቹ ሁለቱ የፍላጎት ንኡሳን ዘርፎች ተገላጭ ግለሰባዊ ፍላጎት (emerging individual interest) እና ብልጹግ ግለሰባዊ ፍላጎት (well-developed individual interest) በግለሰባዊ ፍላጎት ዘርፍ የሚካተቱ ንኡሳን ዘርፎች ናቸው፡፡ በእነዚህ የፍላጎት እርከኖች የመማር ፍላጎት በራሳቸው በተማሪዎቹ መነሳሳት በሚገባ የደረጀ ደረጃ ላይ የደረሰ ጠንካራ ፍላጎት መኖሩን የሚገልጽ ሲሆን በዚህ የፍላጎት እርከን የሚፈረጁ ተማሪዎች የማንንም አነሳሽነት ወይም ግፊት ሳይፈልጉ በራሳቸው ነጻ ፍላጎት መማርን የሚያከናውኑ ናቸው (Hidi and Renninger, 2006)፡፡

Hidi and Renninger (2006) አያይዘው እንደጠቆሙት፣ እያንዳንዱ የፍላጎት ዘርፍ በተለያየ መጠን በስሜታዊ፣ እውቀታዊ እና እሴታዊ ባህርያት ይገለጻል፡፡ ከዚህም ባሻገር በመማር ሂደት ተማሪዎች የሚኖራቸው የተሳትፎ መጠን በየዘርፎቹ ይለያያል፡፡ በብልጹግ ግለሰባዊ የመማር ፍላጎት የሚፈረጁ ተማሪዎች ራስን በመቆጣጠርና በትጋት መንፈስ በሚማሩት ትምህርት የመሳተፍ፣ ደግሞ ደጋግሞ የመሳተፍ ጽኑ አቋም ያላቸው፣ ከባድ ወይም አስቸጋሪ አውዳዊ ሁኔታዎችን ተቋቁሞ የማለፍ ባህሪ የሚያሳዩ ናቸው (Hidi and Renninger, 2006)፡፡

በዚህ መሰረት ብልጹግ ግለሰባዊ የመማር ፍላጎት በቀጣይ አራት ክፍሎች ይመደባሉ፡፡ እነዚህም ከፍተኛ ስሜት፣ እሴታማነት፣ እውቀትና ተሳትፎ ማድረግ ናቸው፡፡ የከፍተኛ ስሜት ምንዝሮች የሚያመለክቱት በተግባራት ዙሪያ አዎንታዊ ስሜት መኖርን ነው፡፡ (ለምሳሌ፡-ተደሳችነት፣ መቀስቀስ፣ ፍክ ስሜት ውስጥ መገኘት ይጠቀሳሉ) Hidi and Renninger, 2006)፡፡ የእሴታማነት ምንዝሮች የሚያመለክቱት የሚያከናውኑት ተግባር ምን አይነት ጠቀሜታ እንደሚያስገኝላቸው መገንዘብን ነው፡፡ (ለምሳሌ፡- በእንግሊዝኛ ቋንቋ መጻፍን መለማመድ ለአለማቀፋዊ ተግባቦት ያለውን አስተዋጽኦ ማወቅ) Hidi and Renninger, 2006)፡፡ የእውቀት ምንዝሮች የሚያመለክቱት በተወሰነ የትምህርት መስክ የእውቀት ክምችት ባለቤት ሆኖ የመገኘት ፍላጎትን ነው፡፡ Tomlinson (2007) እንደጠቆሙት፣ የእውቀት ክምችት ባለቤትነት ከፍላጎት ጋር አዎንታዊ ቀጥተኛ ተዛምዶ ያለው ነው፡፡ የተሳትፎ ምንዝሮች የሚያመለክቱት በአንድ የተወሰነ የመማር ክንዋኔ ውስጥ ንቁ የተሳታፊነት ዝንባሌን አስቀድሞ ለመተንበይ የሚረዳ ነው፡፡ ከፍተኛ የሆነ ግለሰባዊ ፍላጎት ያዳበሩ ተማሪዎች በበርካታ የመማር ተግባራት የመሳተፍ ተነሳሽነት ይዘው

የሚገኙ ናቸው፡፡ እንደ Omrod (2008) ገለጻ፣ ተሳትፎ ፍላጎትን በማስቀጠል፣ በማጠናከርና በማጥለቅ አንድን የተወሰነ የመማር መስክ በስፋት ለማወቅ ከፍ ያለ ጠቀሜታ አለው፡፡

## 2.3 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በሀገር ውስጥ ክፍሌ (2002 ዓ.ም) እና አለምነሽ (2001 ዓ.ም) አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በመማር ተነሳሽነትና በውጤት መካከል ያለውን ተዛምዶ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ጥናት አቅርበዋል፡፡ ጥናቶቹ የትኩረት ተመሳስሎ እንዳለቸው ሁሉ ልዩነትም አላቸው፡፡ የዓለምነሽ የጥናት ተሳታፊዎች የአዊኛ ቋንቋ፣ የክፍሌ የጉምዝኛ አፍፊት መሆናቸው አንዱ ልዩነታቸው ነው፤ በተጨማሪም ዓለምነሽ 7ኛና 8ኛ፣ ክፍሌ 9ኛ ክፍል ላይ ነው ያተኮሩት፡፡ ከዚህ በተረፈ ሁለቱም ተነሳሽነትን በጽሑፍ መጠይቅ የለኩ ሲሆን፣ የተሳታፊዎችን የአማርኛ ቋንቋ ችሎታ ለመለካት ግን ፈተና በራሳቸው አላዘጋጁም፤ የመደበኛውን ትምህርት የዓመት አጋማሽ ፈተና ውጤት ከሮስተር በመመዝገብ ነው መረጃ የወሰዱት፤ ይህም የመረጃውን ትክክለኛነትና አስተማማኝነት ጥያቄ ውስጥ ያስገበዋል፡፡ ከዚህም ሌላ በዓለምነሽ ጥናት ውስጣዊና ውጫዊ የተነሳሽነት ዓይነቶች ብቻ በመጠይቁ የተካተቱ ሲሆን፣ በክፍሌ እነዚህን ጨምሮ ውህዳዊና ጥቅማዊ የተነሳሽነት ዓይነቶች ተካተዋል፡፡ በተጨማሪም በዓለምነሽ ጥናት ፆታ ጣልቃገብ ተላውጦ ሲሆን በክፍሌ ግን አይደለም፡፡ የክፍል ደረጃ በሁለቱም ጥናቶች በጣልቃገብ ተላውጦነት አልተካተተም፡፡ እንዲሁም በዓለምነሽ ጥናት የጽሑፍ መጠይቁ ጥያቄዎች አብዛኞቹ ተነሳሽነትን ሳይሆን የመማር ብልሀትን የሚመለከቱ በመሆናቸው የይዘት ትክክለኛነት ይጎድላቸዋል፡፡ በክፍሌ ጥናት ግን ሁሉም ጥያቄዎች ተነሳሽነት ላይ ያተኩሩ ቢሆኑም ብዙዎቹ ከተዘጋጁና በጥናት ከተፈተሹ ረዥም ዘመን ያስቆጠሩና ማሻሻያም ያልተደረገባቸው በመሆናቸው ወቅታዊነት ይጎድላቸዋል፡፡

ይህም ጥናት በተነሳሽነትና በቋንቋ ትምህርት ላይ ስላተኮረ ከላይ ከተጠቀሱት አገረኛ ጥናቶች ጋር ይቀራረባል፡፡ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት፣ በመማር ተነሳሽነትና በውጤት ተዛምዶ ላይ ስላተኮረና የጽሑፍ መጠይቅን እንደአንድ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ስለተጠቀመ ከሁለቱ ጥናቶች ጋር ይመሳሰላል፡፡ ይሁን እንጂ ጥናቱ የተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ለማግኘት ለዚሁ ተብሎ የተዘጋጀ ፈተናን በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት በመጠቀሙ፣ በጥናቱ ተሳታፊዎች አፍ መፍቻ ቋንቋ፣ የክፍል ደረጃና መገኛ አካባቢ፣ ጥናቱ በተካሄደበት ጊዜ፣ በጽሑፍ መጠይቁ ጥያቄዎች ዓይነት፣

ይዘትና ወቅታዊነት፣ በጥናቱ ተላውጦዎች፣ እንዲሁም በአቀራረቡም ከሁለቱ ጥናቶች ይለያል፡፡

የኔሰው (1990)፣ ‹‹በሁለተኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ክሂላቸውን ለማዳበር ተራክቧዊ የንባብ ክሂልን ማስተማሪያ ሞዴል በክፍል ውስጥ ተጠቅሞ ማስተማር ያለው አስተዋጽኦ›› በሚል ርእስ ያቀረቡት ጥናት ተቃኝቷል፡፡ የየኔሰው ጥናት ዋነኛ ዓላማ አድርጎ የተነሳው ተራክቧዊ የንባብ ክሂልን ማስተማሪያ ሞዴል በሁለተኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ክሂላቸውን ለማዳበር ያለውን አስተዋጽኦ በመፈተሽ ላይ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት አጥኚው በባሌ ዞን በአዳባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ጥናቱን ያካሄዱ ሲሆን፣ የመረጡት የጥናት ስልት ከፊል ፍትነታዊ ነው፡፡ ጥናቱ ከመካሄዱ በፊት በብድግ ብድግ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ሃምሳ ተማሪዎችን በመምረጥ በሁለት ቡድኖች ከፍለው የተጠኚ (ሙከራ) እና የጥብቅ (ቁጥጥር) ቡድኖችን በመመስረት የጥናቱ ተሳታፊ አድርገዋል፡፡ በቅድመ ፈተና ያገኙት መረጃን መሰረት በማድረግ በሁለቱ ቡድኖች መካከል የባህሪ ተመሳሳይነት የሚታይ መሆኑን አረጋግጠው ከቅድመ ፈተና በኋላ ጥብቅ ቡድኑን በልማዳዊ ዘዴ ማስተማሪያ ክፍል፣ ተጠኚ ቡድኑን በተራክቧዊ ዘዴ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል ለአምስት ሳምንታት ካስተማሩ በኋላ በድህረትምህርት ለሁለቱም ቡድኖች አንድ አይነት ፈተና ከሰጡ በኋላ በተገኘው ውጤት በተራክቧዊ ዘዴ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል የተማሩት ተማሪዎች ውጤታቸው የተሻሻለ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

የየኔሰው ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰሉባቸውና የሚለያዩባቸው ነጥቦች አሉ፡፡ ሁለቱም ጥናቶች በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ላይ ማትኮራቸው፣ በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ክሂላቸውን ለማዳበር በሚረዱ የማስተማሪያ ዘዴዎች አዋጭነት ላይ አትኩረው መቅረባቸው፣ በአማርኛ ቋንቋ የንባብ ክሂል አተገባበርን የፈተሹ መሆናቸው እንዲሁም በከፊል ፍትነታዊ ዘዴ ላይ የተመረኮዙ ሆነው መቅረባቸው ከሞላ ጎደል የጥናቶቹን ተመሳሳይነት ማሳያ ናቸው፡፡ በሁለቱ ጥናቶች መካከል የሚታዩ ልዩነቶች ደግሞ የየኔሰው የቀደመ ጥናት በተራክቧዊ ዘዴ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል ትግበራ ላይ ያተኮረ ሲሆን ይህ ጥናት በአማርኛ ቋንቋ መማር ፍላጎትና የውጤት ተዛምዶ ላይ ያተኮረ መሆኑ፣ የየኔሰው ጥናት በባሌ ዞን በአዳባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ11ኛ

ክፍል ተማሪዎች ላይ ትኩረት ያደረገ ሲሆን ይህ ጥናት በጅማ ዞን በጢሮ አፈታ ወረዳ በዲምቱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሚማሩ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ያተኮረ መሆኑ አውዳዊ ልዩነቶች ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ለመቃኘት እንደተሞከረው በፍላጎት፣ በሁለተኛ ቋንቋ መማርና በትምህርቱ ውጤታማ መሆን/አለመሆን ላይ በየጊዜው በተለያዩ ተመራማሪዎች፣ በተለያዩ አካባቢዎች፣ በተለያዩ ቋንቋዎች ላይ ምርምሮች ተካሂደዋል፡፡ ሁሉንም በጋራ የሚያስማሙ ግኝቶች አሉ ለማለት ግን አያስደፍርም፡፡ ከዚህም የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ስኬትን በተመለከተ አሁንም በፍላጎትና በውጤት መካከል ተዛምዶ ላይ ምርምር ማካሄድ አስፈላጊ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ይህም ጥናቱን ለማካሄድ በቀዳሚነት አነሳስቷል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት፤የአጠናን ስልትና የጥናቱ ዘዴ

## 3.1 የጥናቱ ንድፍ

የጥናቱ አብይ አላማ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ የዲምቱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የመማር ፍላጎት ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ጋር ያለውን ተዛምዶ መመርመር ነበር፡፡ የተማሪዎችን የማንበብ ክሂል ወጤታማነት ለመፈተሽ በዚህ ጥናት አንብቦ የመረዳት ክሂልን በመውሰድ በቅድመ እና ድህረ-ትምህርት ፈተና ላይ የተመረኮዘ መረጃ ትንተና ላይ ያተኮረ በመሆኑ ከፊል ፍትነታዊ (Quasi-experimental) የጥናት ንድፍን ተከትሏል፡፡ ይህ ስልት የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖችን በመመስረትና ቅድመ እና ድህረ-ትምህርት ፈተናዎች ላይ በመመርኮዝ በሚሰበሰቡ የፈተና መረጃዎችን በመጠናዊ ስልት ለመተንተን ባለው ጠቀሜታ የተመረጠ ነው፡፡

## 3.2 የጥናቱ አካላይ

ይህ ጥናት በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን ጢሮ አፈታ ወረዳ ካሉት ዲምቱ፣ ጌሼ፣ አኮ፣ ራጋ እና ገበራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል በአመቺ ንሞና በተመረጠው ዲምቱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2013 የትምህርት ዘመን በመማር ላይ በሚገኙ ኦሮምኛ አፈ-ፈት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችን ያጠቃለለ ነው፡፡

## 3.3 የናሙና አመራረጥ ዘዴ

### 3.3.1 የወረዳ አመራረጥ

ጥናቱ የተካሄደው በኦሮምያ ክልል ጅማ  ዞን ሲሆን በጂማ ዞን 23 ወረዳዎች ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ የጢሮ አፈታ ወረዳ  በአመቺ ንሞና ዘዴ (Convinance Sampling) በመጠቀም ተመርጧል፡፡ ይህ ወረዳ የተመረጠበት ምክንያት የአጠኚዋ የመኖሪያ አካባቢ ስለሆነ ምርምሩን ለማካሄድ ሊገጥሟት ከሚችሉ የአካባቢ እንግድነት፣ የጊዜና የገንዘብ እጥረት አንጻር በአጥኚዋ መገኛ ወረዳ ጥናቱን ማካሄድ አመቺ በመሆኑ እንዲሁም ለስራው ተባባሪና ፈቃደኛ መምህራንና ተማሪዎች በትምህርት ቤቶቹ ውስጥ ለማግኘትና የጥናቱን መረጃዎች በተቀላጠፈ ሁኔታ ለመሰብሰብ ያስችላል የሚል እምነት ስላላት ነው፡፡

### 3.3.2 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

በጢሮ አፈታ ወረዳ ከሚገኙ አምስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (ጌሼ ፣ ዲምቱ ፣ አኮ፣ ገበራ እና ራጋ ሲባ) መካከል ለዚህ ጥናት የተመረጠው ዲምቱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፡፡ ትምህርት ቤቱ አመቺ የናሙና ዘዴን በመጠቀም የተመረጠ ሲሆን ይህ ትምህርት ቤት የተመረጠበት ዋና ምክንያት አጥኚዋ ከዚህ ቀደም ታስተምርበት የነበረና ለመኖሪያ አካባቢዋ ቅርብ ስለሆነ ምርምሩን ለማካሄድ ሊገጥማት የሚችለውን የጊዜና የገንዘብ እጥረት ለማቃለል አመቺ በመሆኑና ለጥናቱ ስራ የመረጃ አሰባሰብ ሂደት ተባባሪና ፈቃደኛ መምህራንና ተማሪዎች በትምህርት ቤቱ ውስጥ በመኖራቸው መረጃዎችን በተቀላጠፈ ሁኔታ ለመሰብሰብ ያስችላል በሚል እምነት ተተኳሪ ተደርጓል፡፡

### 3.3.3 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

የጥናቱ ተተኳሪዎች በዲምቱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2013 ዓ.ም የሚማሩ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ እነዚህ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የተመረጡበት ምክንያትም ተማሪዎቹ ገና ሁለተኛ ደረጃን የሚጀምሩበት ደረጃ ላይ የሚገኙ በመሆኑ ዉጤቱ መሰረት ተደርጎ ለሚተለመው መፍትሄ የተሻለ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ ተማሪዎች የሚገኙበት የክፍል ደረጃ ስለሆነ እንዲሁም ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ይልቅ በሁለተኛ ደረጃና ከዚያ በላይ በሆኑ ደረጃዎች የሚማሩ ተማሪዎች መረጃዎችን በተሻለ ሁኔታ መስጠት ይችላሉ በሚል ታሳቢ ነው፡፡ በዕድሜ ከፍ ያሉ ተማሪዎች ዝቅ ካሉት በተሻለ ስለአፍ መፍቻና ሁለተኛ ቋንቋ ያላቸውን ፍላጎት በግልፅ ሊያንፀባርቁ ይችላሉ የሚል እምነት አጥኚዋ ስላላት ነው፡፡

### 3.3.4 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

በዲምቱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ 7 የዘጠነኛ መማሪያ ክፍሎች የሚገኙ ሲሆን በእያንዳንዱ የዘጠነኛ መማሪያ ክፍል ውስጥ በአማካይ 40 ተማሪዎች በድምሩ 280 ተማሪዎች እየተማሩ ይገኛሉ፡፡ ጥናቱ በልማዳዊ ማስተማሪያ ዘዴና በፍላጎት ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዘዴ የሚማሩ የቁጥጥርና የሙከራ ቡድኖችን በመውሰድ በቅድመ-ትምህርትና ድህረ-ትምህርት ላይ ያተኮረ መረጃ በመሰብሰብ መተንተንን ያለመ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ በእድል ሰጪ የናሙና ዘዴ የተለያዩ ተማሪዎችን ከተለያዩ ክፍሎች አውጣጥቶ ለማስተማር መሞከር ተጠኚዎቹን የሁለት ቡድን አባላት ለትምህርት አቀራረብ በሚፈለገው መልኩ ከየመማሪያ ክፍሉ አውጣጥቶ በየጊዜው ማሰባሰብ አዳጋች ያደርገዋል፡፡ የባህሪ ተላውጦ በጥናቱ ውጤት ላይ የሚያስከትለውን ተጽእኖ ለመቆጣጠር ሲባል የተመረጠው የሁለት ክፍል ተማሪዎችን እንዳሉ በመውሰድ በአማካይ ከ40 /አርባዎቹ/ መካከል የተሻሉትን በቅድመ-ትምህርት ፈተና አጣርቶ የቁጥጥር ቡድንና የሙከራ ቡድን መመስረት ነው፡፡

በዚሁ መሰረት ዕድል ሰጭ የንሞና ዘዴን በመጠቀም የተመረጡት ሁለት መማሪያ ክፍሎች 9B እና 9E መማሪያ ክፍሎች ናቸው፡፡ ቀጥሎ በተማሪዎቹ መካከል ሊኖር የሚችለው የተለያየ የመረዳት ባህሪ ተላውጦ በጥናቱ ውጤት ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ተጽእኖ ለመቆጣጠር ሲባል አንጻራዊ ተመሳሳይ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች የጥናቱ ተሳታፊ ማድረግ በማስፈለጉ በ9B እና 9E ክፍሎች ከሚገኙ 40 /አርባ/ ተማሪዎች መካከል 25 /ሃያ አምስት/ በድምሩ 50 /ሃምሳ/ ተማሪዎችን በቅድመ-ትምህርት ፈተና የማጣራትና ወደ ጥናቱ አውድ የማምጣት ስራ ተከናውኗል፡፡ በዚሁ መሰረት ከሁለቱም ተተኳሪ ክፍሎች አንጻራዊ ተቀራራቢ የተሻለ ውጤት ያላቸው ተማሪዎች በቅድመ-ትምህርት ፈተናው ተለይተው በየመማሪያ ክፍላቸው 25 /ሃያ አምስት/ ሆነው ተመድበዋል፡፡ ቀጣዩ ተግባር ሁለቱን ክፍሎች የቁጥጥር ቡድንና የሙከራ ቡድን አድርጎ መሰየም ነው፡፡ በዕድል ሰጭ የንሞና ዘዴ በመጠቀም በእጣ የ9B ክፍል የቁጥጥር ቡድን ሲሆን ሌላው የ9E ክፍል የሙከራ ቡድን ሆኗል፡፡

## 3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

በጥናቱ ዓላማ መሠረት የተመረጡት ሁለት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የፍላጎትን መጠን መለኪያ የጽሑፍ መጠይቅና በቅድመ-ትምህርትና ድህረ-ትምህርት የሚቀርቡ የአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ፈተና /የችሎታ መለኪያ ፈተና/ ናቸው፡፡

### 3.4.1 የችሎታ መለኪያ ፈተና

ፈተና የተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ ችሎታ ለማወቅ በመረጃ መሰብሰቢያነት አገልግሎት ሰጥቷል፡፡ ፈተናው ከመዘጋጀቱ በፊት በክፍል ደረጃው መማሪያ መጽሐፍ ላይ ካሉት ይዘቶች ተማሪዎቹ የተማሯቸውን ከዘጠነኛ ክፍል መምህራን እቅዶች፣ ከመማሪያ መጽሐፉና ከተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ደብተሮች ለመለየት ጥረት ተደርጓል፡፡ ከዚያም መማሪያ መጽሐፉን መሠረት በማድረግና በትምህርት ቤቱ የተለመዱ የፈተና ዓይነቶችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ፈተናው አዲስነቱን ለመጠበቅ ከመማሪያ መጽሐፉ የምንባብ ይዘቶች የሚመሳሰሉ በቅድመ እና ድህረ ትምህርት ቀርበው የፈተና መረጃ ለመሰብሰብ አገልግሎት ላይ የዋሉ ሁለት ምንባቦች ከሌሎች ምንጮች በመውሰድ አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎቹ በቅድሚያ በአጥኚዋ ተዘጋጅተዋል፡፡ የአንብቦ መረዳት ፈተናው በሁለት ምንባቦች ላይ የተመሰረቱ ከእያንዳንዱ ምንባብ 15 /አስራ አምስት/ የምርጫ ጥያቄዎች ተውጣጥተው የቀረቡበት ሲሆን እርማቱ የተከናወነው ከ30 ነጥብ /ማርክ/ በመስጠት ነው፡፡ (የቀረቡት ሁለት ምንባቦችና ከምንባቦቹ የተውጣጡ በአጠቃላይ 30 ጥያቄዎች በቅድመ እና ድህረ-ትምህርት የፈተና መረጃ ለመሰብሰብ አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡)

#### የፈተና አስተማማኝነት መለኪያዎች

የጥያቄዎቹንና አማራጭ መልሶችን አቀራረብ ተገቢነት ለማረጋገጥ በቅድሚያ አማርኛ ቋንቋ ለሚያስተምሩ ሁለት መምህራን፣ ቀጥሎም አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው ሁለት መምህራን በጥንቃቄ እንዲመለከቱትና አስተያየት እንዲሰጡበት ከተደረገ በኋላ የጥያቄ አቀራረቦች፣ በመልስ አማራጮች ውስጥ የሚታዩ አሻሚነት ያላቸው አወቃቀሮች እንዲስተካከሉ ወይም እንዲቀየሩ ተደርጓል፡፡ የተቀየሩት ጥያቄዎች ምንባቦቹን ሳያነቡ ጥያቄዎቹን በጠቅላላ እውቀትና በግምት እንዲመልሱ ፍንጭ ይሰጣሉ

ተብሎ አስተያየት የተሰጠባቸው ሶስት ጥያቄዎች ሲሆኑ በጥያቄዎቹና መልሶቻቸው አቀራረብ ላይ አስፈላጊው ጥንቃቄ ተደርጎ ተዘጋጅተዋል፡፡ ቀጥሎም ጥያቄዎቹ አጠቃላይ የቋንቋ ፈተና ባህርያትን ያሟሉ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥም በጅማ ዩኒቨርሲቲ የጥናቱ አማካሪዎች ቀርቦ አስተያየት ከተሰጠባቸው በኋላ በአስተያየቶች የተደገፈ ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡ በሌላም በኩል ለዋናው ጥናት መረጃ መሰብሰቢያ ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት በጥናቱ ባልታቀፉ ሌሎች 25 የገበሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የሙከራ ጥናት (Pilot Study) ተካሂዷል፡፡ በተገኘው የክሮንባች አልፋ ስታቲስቲካዊ ልኬት 0.775 (ከ0.5 በላይ) በመሆኑ የፈተናው የአስተማማኝነት መጠን በክሮንባኽ አልፋ ልኬት አስተማማኝነቱ ተረጋግጦ ለዋናው ጥናት መረጃ መሰብሰቢያነት ውሏል፡፡

ፈተናው በአጥኚዋና በአንድ ፈቃደኛ የአማርኛ ቋንቋ መምህር እገዛ ሁለቱም ቡድኖች በሁለት መማሪያ ክፍሎች ለሙከራና ለቁጥጥር ቡድኑ በአንድ ቀንና ሰአት እንዲፈተኑት የተደረገ ሲሆን የሙከራ ጥናት (Pilot Study) ተሞክሮን መሰረት በማድረግ ለፈተናው የተፈቀደው ጊዜም 1፡30 (አንድ ሰዓት ተኩል) ተሰጥቷቸው ፈተናውን አጠናቀው መልሰዋል፡፡ ስለፈተናው አላማና የአሰራር ሂደትም አጥኚዋ ለሁሉም የጥናቱ ተሳታፊ ቡድኖች ማብራሪያ በመስጠት ግንዛቤ አስጨብጣለች፡፡ የተማሪዎች የመልስ መስጫ ወረቀት አንድ የተቆረጠ መልስ ብቻ ያለው በመሆኑ በአጥኚዋ ታርሟል፡፡

### 3.4.2 የጽሑፍ መጠይቅ

ለዚህ ጥናት በስራ ላይ የዋለው የጽሁፍ መጠይቅ መረጃ መሰብሰቢያ አንብቦ የመረዳት ፍላጎት አሰሳ መጠይቅ ነበር፡፡ የጽሁፍ መጠይቁ አማርኛ ቋንቋ የመማር ፍላጎት፣ በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ፍላጎት እና ችሎታ አሳሽ ጥያቄዎችን አካትቷል፡፡ የጽሑፍ መጠይቁ የተማሪዎችን አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የመማር ፍላጎት መጠንን በተመለከተ አስፈላጊውን መረጃ ለማግኘት የቀረበው ለሙከራ ቡድን ተጠኚዎቹ አባላት ብቻ ነበር፡፡ የመጠይቅ ጥያቄዎቹ ሙሉ በሙሉ የሊከርት ስኬል የጽሁፍ መጠይቅ አቀራረብ ስልትን በመከተል ከ‹‹ፈጽሞ አልስማማም›› እስከ ‹‹ሙሉ በሙሉ እስማማለሁ›› ባለአምስት አማራጭ መልሶችን ይዘው በሰንጠረዥ ቀርበዋል፡፡ በዚሁ መሰረት ከከፍተኛ ወደዝቅተኛ ‹‹ሙሉ በሙሉ እስማማለሁ›› (5 ነጥብ)፣ ‹‹እስማማለሁ›› (4 ነጥብ)፣ ‹‹አቋም አልያዝኩም›› (3 ነጥብ)፣ ‹‹አልስማማም›› (2 ነጥብ)፣ እና ‹‹ፈጽሞ አልስማማም›› (1 ነጥብ)

ይዘዋል፡፡ ይህም ተሳታፊዎቹ በተቀላጠፈ አኳኋን መጠይቁን ሞልተው እንዲያጠናቅቁ ለማድረግ ረድቷል፡፡

የጽሁፍ መጠይቁን አስተማማኝነት ለመጠበቅ ከዚህ ቀደም በትምህርት ቤትና በዩኒቨርሲቲ በስራ ላይ ውሎ ተግባራዊነቱ የተረጋገጠ ከNational Research Council (2003) እና Schiefele (2008) አጠቃላይ የመማር ፍላጎት እና አንብቦ የመረዳት መጠይቆችን ወደ አማርኛ ቋንቋ በመመለስ ለዚህ ጥናት እንዲስማሙ አድርጎ አጣጥሞ የመጠቀም አቅጣጫን ጥናቱ ተከትሏል፡፡ በዚሁ መሰረት ከፍ ሲል የተጠቀሱት ምንጮች ባቀረቧቸው የመጠይቅ ጥያቄዎች በመደገፍ ‹‹አጠቃላይ ፍላጎት››ን የሚወክሉ 20 /ሃያ/ ጥያቄዎች፣ ‹‹የማንበብ ፍላጎት››ን የሚወክሉ 12 /አስራ ሁለት/ ጥያቄዎች፣ እንዲሁም ‹‹የማንበብ ችሎታ››ን የሚመለከቱ 8 /ስምንት ጥያቄዎች በጽሁፍ መጠይቁ ተካተው ቀርበዋል፡፡ በጽሁፍ መጠይቁ የተካተቱ ጥያቄዎች አጠቃላይ ብዛት 40 /አርባ/ ነው፡፡ ስለመጠይቁ አሞላል የተጠኚዎቹን ሁለተኛ ቋንቋ ተማሪነት ግምት ውስጥ በማስገባት አጥኚዋ አጠገባቸው በመሆን በሁለተኛ ቋንቋቸው ጭምር ማብራሪያ ሰጥታ አስሞልታለች፡፡

የጥያቄዎቹን ተገቢነት ከፍ ለማድረግና የትርጉም አሻሚነትን ለማስወገድ ወደ አማርኛ ተመልሶ የቀረበውን የጽሁፍ መጠይቅ ለሁለት በአማርኛ ቋንቋ ሁለተኛ ዲግሪ ላላቸው መምህራን ቀርቦ በሰጡት አስተያየት መሰረት መሻሻል የሚገባቸው ጉዳዮችን በተሻሉ አቀራረቦች በመለወጥ ለጥናቱ አማካሪዎች ቀርበው ይሁንታ በማግኘታቸው ለመስክ መረጃ ስብሰባ በአገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የመጠይቅ ጥያቄዎቹን አስተማማኝነት ከፍ ለማድረግ ለዋናው ጥናት በስራ ላይ ከመዋሉ አስቀድሞ ከተጠኚዎቹ ውጪ ባሉ 25 የዲምቱ ሁለተኛ ደረጃ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የሙከራ ጥናት (Pilot Study) ተካሂዷል፡፡ የሙከራ ጥናቱን ተከትሎም የፈተናው የአስተማማኝነት መጠን በክሮንባክ አልፋ ልኬት ተሰልቶ አስተማማኝነቱ 0.688 (ከ0.5) የሚበልጥ የመሆኑን አስተማማኝነት ግምት ውስጥ በማስገባት ለዋናው ጥናት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ስለመጠይቁ አላማና የአሰራር ሂደትም አጥኚዋ ለሙከራ ቡድኑ ተሳታፊ ተማሪዎች ማብራሪያ በመስጠት አስሞልታለች፡፡ ተማሪዎቹ የየራሳቸውን ትክክለኛ ስሜትና ባህርይ ያንፀባርቁ ዘንድም በመጠይቁ አሞላል ሂደት መረጃ እንዳይለዋወጡ ከፍተኛ ጥንቃቄ ተደርጓል፡፡

### 3.5 የትምህርቱ አቀራረብና የማስተማሪያ መሳሪያ ዝግጅት

#### 3.5.1 የትምህርቱ አቀራረብ

በዚህ ጥናት የሙከራ ቡድኑን አባላት ፍላጎት ተኮር በሆነ የማስተማሪያ ዘዴ በማስደገፍ እንዲሁም የመቆጣጠሪያ ቡድኑን አባላት በልማዳዊው የማስተማሪያ ዘዴ ለ6 ሳምንታት እንዲማሩ ተደርጓል፡፡ ትምህርቱ ለሁለቱም ቡድኖች የቀረበው በአጥኚዋ አማካኝነት ሲሆን፤ ከማስተማሪያ ዘዴ በቀር ተመሳሳይ የሆኑ የምንባብ ይዘቶች /ግብአቶች/ ቀርበውላቸው እንዲማሩ ተደርጓል፡፡ በአንድ የአማርኛ ቋንቋ መምህር የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑን አከታትሎ ማስተማር ያስፈለገበት ምክንያት የመምህር ተላውጦ በጥናቱ ውጤት ላይ ሊያሳድር የሚችለውን አሉታዊ ተጽእኖ ለመቆጣጠር ሲባል ነው፡፡ በዚሁ መሰረት አንድ አይነት ይዘቶችን ከ9ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ በመምረጥ ሁለቱን ቡድኖች በሳምንት ለ1 /አንድ/ ክፍለጊዜያት እና ተጨማሪ የ2 /ሁለት/ ሰአት ቱቶሪያል ትምህርት በተለያዩ መማሪያ ክፍሎች እንዲማሩ ተደርጓል፡፡ ይህም ለአማርኛ የተመደበው ክፍለ-ጊዜ በሳምንት አንድ ክፍለ ጊዜ ብቻ በመሆኑ የጊዜ ጥበት የአንብቦ መረዳት ትምህርቱ ተደራሽነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንዳያስከትልና በጥናቱ ውጤት አስተማማኝነት ላይ ችግር እንዳይፈጥር ለመከላከል ሲባል የተወሰደ አማራጭ ነው፡፡ ሁለቱም ቡድኖች ከመደበኛ ፈረቃቸው ውጪ የ2 /ሁለት/ ሰአት ትምህርት ተሰጥቷቸው ስልጠናውን ካጠናቀቁ በኋላ ድህረ-ትምህርት ፈተና እንዲፈተኑ ተደርጓል፡፡

#### 3.5.2 የማስተማሪያ መሳሪያ ዝግጅት

በዚህ ጥናት ለሙከራ ቡድኑ ተጠኚዎች ለስድስት ሳምንታት ሲደመር የሁለት ሰአት ቱቶሪያል የቀረበላቸው የአንብቦ መረዳት ትምህርት በይዘቱ ተመሳሳይ ሆኖ ለመቆጣጠሪያ ቡድኑ አባላት የተለመደውን የማንበብ ትምህርት ልማዳዊ አተገባበር በመከተል በ9ኛ ክፍል አማርኛ የተማሪው መጽሐፍ የቀረቡ ምንባቦችና አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች ተተግባሪ ተደርገዋል፡፡ ለሙከራ ቡድኑ የቀረቡትን ምንባቦችና አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች ፍላጎት ተኮር ዘዴዎችን በምእራፍ ሁለት በንኡስ ቁጥር 2.1.7 በቋንቋ መማሪያ አውድ ፍላጎትን በተማሪዎች ዘንድ ለማስረጽ የቋንቋ መምህራን ሊያከናውኗቸው የሚገቡ ተግባራትን በማካተት እንዲለማመዱ ተደርጓል፡፡

በዚህ ጥናት የተማሪዎቹን አንብቦ የመረዳት ፍላጎት ለማሻሻልና ለማጠናከር ለሙከራ ቡድኑ ተጠኚዎች የቀረቡላቸው የማንበብ ትምህርቶች በሚከተሉት በቋንቋ መማሪያ አውድ ፍላጎትን በተማሪዎቹ ዘንድ ለማስረጽ የሚረዱ ተግባራት የተደገፉ ነበሩ፡፡ ተግባራቱ በክለሳ ድርሳናት ምእራፍ በተለይ ከ2.1.7.1 እስከ 2.1.7.8 የተዘረዘሩትን የፍላጎት አላባዎች በመከተል የተቀናጁ ናቸው፡፡

1. ተማሪዎቹ የቋንቋ መማር አስተሳሰብ እንዲያዳብሩ ማድረግ፣
2. ተማሪዎች በእውቀትና ክህሎት ሊደርሱበት የሚገባ ፍላጎትን በውስጣቸው ማስረጽ፣
3. ተማሪዎች የሚደረስባቸው የቋንቋ መማር ግቦችን እንዲያስቀምጡ መገፋፋት፣
4. ተማሪዎች በራስ የመተማመን ስሜት እንዲገነቡ ማበረታታት፣
5. የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ለማንሰራራት የሚረዱ አዳዲስ የማስተማሪያ ብልሃቶችን መተግበር (የቃላት ጫዋታ፣ የፕሮጀክት ክንዋኔ፣ ሚና ጫዋታ፣ ችግር ፈቺ የማስተማሪያ ብልሃት፣ በመደጋገፍ መማር፣ ብጤን ማስተማር እና ማነቃቃት)፣
6. ማበረታቻን ለቋንቋ መማር ፍላጎት ግብአት ማድረግ (ለተማሪዎች እውቅና መስጠትና መሸለም) የአንብቦ መረዳት ትምህርቶቹ አካል ተደርገው የሙከራ ቡድኑ ትምህርት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

### 3.6 የመረጃ አተናተን ዘዴ

ከተሳታፊዎች የተገኙት መረጃዎች ለትንታኔ ከመቅረባቸው በፊት በአግባቡ የማደራጀትና የማጠናቀር ስራ ተሰርቷል፡፡ በዚሁ መሰረት መረጃዎች ለትንተና በሚያመች መልኩ ኮድ ተደርገው በውጤት መመዝገቢያ ሰንጠረዥ (Code Sheet) ላይ እንዲሰፍሩ ተደርጓል፡፡ የተሰበሰቡትን መጠናዊ መረጃዎች ትክክለኛነት የማረጋገጥ ስራ ከተሰራ በኋላ መረጃዎቹ የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ባላቸው ግንኙነት መሰረት ተደራጅተው በSPSS Version 20 የመረጃ ማብላያ ቋት በማስገባት ውጤቱ ተተንትኗል፡፡ በዚሁ መሰረት በቅድመ እና ድህረ-ትምህርት የተሰበሰቡት አንብቦ መረዳት ላይ ያተኮሩ የፈተና መረጃዎች ትንተና ተካሂዷል፡፡ የጥናቱ ተሳታፊ ሁለት ቡድኖች ወደ ትምህርቱ ከመግባታቸው በፊት ያላቸውን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተመሳሳይነት ለማወቅ የተፈተኑት ቅድመ-ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና እንዲሁም ትምህርቱ እንደተጠናቀቀ ሁለቱ ቡድኖች የተፈተኑት ድህረ-ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤትም ለየቡድኖቹ በየአንጻራቸው በገላጭና ድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ አማካይ

ውጤትና መደበኛ ልይይት ተሰልቶ ቀርቧል፡፡ በሁለቱ ቡድኖች አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማወቅ በነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት (independent samples t-test) ተተንትኖ ከማብራሪያ ጋር ቀርቧል፡፡ ይህንንም ተከትሎ በፍላጎትና በውጤት መካከል ያለውን ተዛምዶ ለመተንተንም ፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ (Pearson Correlation coefficient) ቀመር ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በዚህ ስታቲስቲካዊ ማሳያ በመታገዝ የጥናቱን የመጀመሪያውን መሰረታዊ ጥያቄ መልሷል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ በቅድመ-ትምህርትና በድህረ-ትምህርት ለሙከራ ቡድኑ በቀረበላቸው መጠይቅ የተገኘው ባለ 5 /አምስት ነጥብ/ የሊከርት ስኬል ምላሽ በገላጭና ድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ አማካይ ውጤትና መደበኛ ልይይት እንዲሁም በዳግም ልኬት ናሙናዎች ቲ-ቴስት (Paired-samples t-test) ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ ይህም የጥናቱን ሁለተኛውን መሰረታዊ ጥያቄ ለመመለስ ረድቷል፡፡

# ምዕራፍ አራት፤የመረጃ ትንተና እና የዉጤት ማጠቃለያ

የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ሁለት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ተግባር ላይ ውለዋል፡፡ አንደኛው የመረጃ መሰብሰቢያ በቅድመ-ትምህርትና ድህረ-ትምህርት ላይ ያተኮረ የአንብቦ መረዳት ፈተና ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በቅድመ-ትምህርት እና ድህረ-ትምህርት ለሙከራ ቡድኑ ተጠኚዎች የቀረበ የጽሁፍ መጠይቅ ነበር፡፡ በዚሁ መሰረት ቅድመ-ትምህርት ፈተናው ከ2 /ሁለት/ የዘጠነኛ መማሪያ ክፍሎች እንዳሉ የተወሰዱ 40 /አርባ/ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ቀርቦላቸው እንዲፈተኑ በማድረግ በአንጻራዊ የተሻለ ውጤት ያመጡት 25 /ሃያ አምስት/ የሁለት መማሪያ ክፍሎች ተማሪዎች በየክፍላቸው ተወስደው፤ በቀላል እጣ ንሞና አንዱን ክፍል የሙከራ፣ ሌላኛውን ክፍል የቁጥጥር ቡድን በማድረግ በየመማሪያ ክፍላቸው የዋናው ጥናት ተሳታፊ ተደርገዋል፡፡ ድህረ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተናው ደግሞ በተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎች (ተለምዷዊው እና ፍላጎት ተኮር) ለስድስት ሳምንታት ሲደመር ሁለት የቱቶሪያል ሰአታት ሽፋን ተለያይተው የማንበብ ክሂል ትምህርት ከመማራቸው በቀር በሌሎች ተላውጦዎች የጎላ ልዩነት የማይታይባቸውን የቁጥጥርና የሙከራ ቡድን ተማሪዎች የችሎታ ልዩነት ለመፈተሽ ያስቻለ ነው፡፡

በዚህ ምዕራፍ ፍላጎት ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ የተጠኚዎቹን አንብቦ የመረዳት ክሂል ለማዳበር እንዲሁም የተጠኚዎቹን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሻሻል አስተዋጽኦ ማበርከት አለማበርከቱን ለመለካት ዋነኛ መሳሪያ የሆኑት የአንብቦ መረዳት ፈተናዎች በአማካይ ውጤቶችና መደበኛ ልይይት ብሎም የውጤት ልዩነት የጉልህነት ደረጃ በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት (independent samples t-test) አማካይነት በሰንጠረዥ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ፍላጎት ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ ከሙከራ ቡድን ተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ተዛምዶ ለመተንተንም ፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ (Pearson Correlation coefficient) ቀመር ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በሌላም በኩል በቅድመ-ትምህርትና በድህረ-ትምህርት ለሙከራ ቡድኑ -- አጠቃላይ ፍላጎት፣ አንብቦ የመረዳት ፍላጎትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለመለካት -- የቀረበላቸው ባለሶስት ዘርፍ መጠይቅ የተገኘው ባለ 5 /አምስት ነጥብ/ የሊከርት ስኬል ምላሽ በዳግም ልኬት ናሙናዎች ቲ-ቴስት (Paired-samples t-test) ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

## 4.1 የጥናቱ ውጤት ትንተና

የመጀመሪያው የትንተናው ክፍል ያተኮረው በቅድመ-ትምህርት ለጥናቱ የተመረጡት የሁለት ቡድኖች ተማሪዎች በየአንጻራቸው የቁጥጥር ቡድኑ በነባሩ /ልማዳዊው የማስተማሪያ ዘዴ እና የሙከራ ቡድኑ በፍላጎት ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ ከመማራቸው በፊት በአንብቦ መረዳት ክሂል እውቀታቸው መሰረታዊ ልዩነት ያላቸው መሆን አለመሆናቸውን በመፈተሽ ላይ ነው፡፡ በዚህ መሰረት መረጃው በገላጭ እና በድምዳሚያዊ ስታትስቲክስ (inferential statitics) ተሰልቷል፡፡ ውጤቱም በሰንጠረዥ 1 እና 2 እንደሚከተለው ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

### ሰንጠረዥ 1፡- የሙከራው እና የቁጥጥሩ ቡድኖች የቅድመ-ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና አማካይ ውጤቶች የገላጭ ስታትስቲክስ ንጽጽር

| ተጠኚ | የናሙና መጠን (n) | አጠቃላይ የቡድን ውጤት | አማካይ ውጤት (mean) | መደበኛ ልይይት (S.D.) | መደበኛ የአማካይ ስህተት (Std. Error Mean) |
|---|---|---|---|---|---|
| የሙከራ ቡድን | 25 | 412 | 16.48 | 2.62 | .523 |
| የቁጥጥር ቡድን | 25 | 407 | 16.28 | 2.89 | .579 |

በሰንጠረዥ 1 ለቁጥጥርና የሙከራ ቡድኑ ተመሳሳይ አንብቦ የመረዳት ፈተና (ከ30 ነጥብ የተያዘለት) ቀርቦላቸው ያገኙት አጠቃላይ የቡድን ውጤትና አማካይ ውጤት ከመደበኛ ልይይት ጋር በገላጭ ስታቲስቲክስ ተሰልቶ ቀርቧል፡፡ ስለቁጥጥሩና የሙከራው ቡድኖች የቅድመ-ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና አጠቃላይ የቡድን ውጤትና አማካይ ውጤቶችና መደበኛ ልይይቶች በሰንጠረዥ 1 ከሰፈረው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው፤ ከሁለቱ ቡድኖች አጠቃላይ የቡድን ውጤት የሙከራው ቡድን 412 ከቁጥጥሩ ቡድን በቅድመ-ትምህርት በ05 /አምስት/ ነጥብ ብቻ በልጦ መገኘቱን፣ እንዲሁም አማካይ ውጤቶቹ በንጽጽር ሲታዩ የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ቅድመ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና አማካይ ውጤት (16.48) ከቁጥጥሩ ቡድን ተማሪዎች ቅድመ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና አማካይ ውጤት (16.28) በ0.20 በልጦ መጠነኛ ልዩነት ማሳየቱን እንመለከታለን፡፡

እንዲሁም የቁጥጥሩ ቡድን ተማሪዎች ቅድመ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና መደበኛ ልይይት (2.89) ከሙከራው ቡድን ተማሪዎች ቅድመ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና መደበኛ ልይይት (2.62) በ0.27 በልጦ መጠነኛ ልዩነት አሳይቷል፡፡ ይሁን እንጂ የሁለቱም ቡድኖች ቅድመ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት ከአማካይ ውጤቱ ያለው ርቀት ሲታይ ከፍና ዝቅ የሚል ሳይሆን ተቀራራቢና አንድ ወጥነት ባህሪ የሚታይበት መሆኑን እንረዳለን፡፡

በትንተናው መሰረት የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ቅድመ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና አማካይ ውጤት ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ቅድመ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና አማካይ ውጤት በ0.20 እንደበለጠ ተረጋግጧል፡፡ ነገር ግን በመካከላቸው ስላለው ልዩነት የጉልህነት ደረጃ እርግጠኛ ለመሆን ድምዳሚያዊ ስታትስቲክስ መጠቀም ስለሚያስፈልግ በሠንጠዥ 2 እንደቀረበው የነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

**ሰንጠረዥ 2፡- የሙከራው እና የቁጥጥሩ ቡድኖች የቅድመ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና አማካይ ውጤቶች የነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ንጽጽር**

| ተጠኚ | የናሙና መጠን (n) | አማካይ ውጤት (mean) | መደበኛ ልይይት (S.D.) | የነጻነት ደረጃ (df) | የ«ቲ» ዋጋ (t-value) | የጉልህነት ደረጃ (sig.2-tailed) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የሙከራ ቡድን | 25 | 16.48 | 2.62 | 24 | -.314 | .757* |
| የቁጥጥር ቡድን | 25 | 16.28 | 2.89 | | | |

*ማስታወሻ፡- የጉልህነት ደረጃ አለ ለማለት $p<0.05$ (የፒ ዋጋ ከ0.05 በታች) መሆን ይኖርበታል፡፡

ከላይ በሰንጠረዥ 2 በቀረበው የነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ንጽጽር መረጃ መሰረት በቁጥጥሩና በሙከራው ቡድኖች የቅድመ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን መረዳት ይቻላል፡፡ መረጃው በነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተሰልቶ በሁለቱም ቡድኖች አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ውጤቱ ($t= -.314$, $df= 24$, $p= .757$) አሳይቷል፡፡ የጉልህነት ደረጃ ማነጻጸሪያው

p 0.757 ከ $p<0.05$ ከፍ ያለ ብልጫ ማሳየቱ ጉልህ የውጤት ልዩነት አለመኖሩን ለመመዘን ይረዳል፡፡ ይህም ሁለቱ ቡድኖች በተለያዩ አንብቦ መረዳትን መማሪያ ዘዴዎች ከመማራቸው በፊት በአንብቦ መረዳት መሰረታዊ ችሎታቸው ጉልህ ልዩነት እንደሌላቸው (ወይም በተመሳሳይ አንብቦ የመረዳት የብቃት ደረጃ ላይ እንደሚገኙ) ያሳያል፡፡

የመጀመሪያው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ፣ *የኦሮምኛ ቋንቋ አፊ-ፊት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል ያላቸው ፍላጎት በውጤታቸው ላይ ተጽዕኖው ምን ይመስላል?* የሚል ሲሆን ይህም ሁለቱ የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖች በየአንጻራቸው በፍላጎት ተኮር የማስተማር ዘዴ እና በተለምዷዊው አንብቦ መረዳትን የማስተማሪያ ዘዴ ለስድስት ሳምንታት እና ተጨማሪ ሁለት ሰአታት አንብቦ መረዳትን በተግባር ሲለማመዱ ከቆዩ በኋላ፤ ከአንብቦ መረዳት ማስተማሪያ ዘዴ ተላውጦ በስተቀር በቅድመ-ትምህርት አንብቦ በመረዳት ብቃታቸው አንጻራዊ ተመሳሳይነት ይታይባቸው በነበሩት የሙከራ ቡድንና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች መካከል ጉልህ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ልዩነት መኖር አለመኖሩን መፈተሽን ያለመ ነበር፡፡ በዚሁ መሰረት ይህንኑ የጥናቱን የመጀመሪያውን መሰረታዊ ጥያቄ ለመመለስና ፍላጎት ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ ተላውጦ የተማሪዎቹን የማንበብ ክሂል ችሎታ ከማዳበር ጋር ያለውን ተዛምዶ ለመፈተሽ ስታቲስቲካዊ መረጃው በገላጭና በድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ ተተንትኗል፡፡ ውጤቱም በሠንጠረዥ 3 እና 4 ተመልክቷል፡፡

**ሰንጠረዥ 3፡- የሙከራው እና የቁጥጥሩ ቡድኖች ድህረ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና አማካይ ውጤቶች የገላጭ ስታትስቲክስ ንጽጽር**

| ተጠኚ | የናሙና መጠን (n) | አጠቃላይ የቡድን ውጤት | አማካይ ውጤት (mean) | መደበኛ ልይይት (S.D.) | መደበኛ የአማካይ ስህተት (Std. Error Mean) |
|---|---|---|---|---|---|
| የሙከራ ቡድን | 25 | 513 | 20.52 | 1.98 | .396 |
| የቁጥጥር ቡድን | 25 | 434 | 17.36 | 2.81 | .562 |

ከላይ በሰንጠረዥ 3 በገላጭ ስታቲስቲክስ የቀረበው መረጃ የቁጥጥሩንና የሙከራውን ቡድኖች የድህረ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና አጠቃላይ የቡድን ውጤቶች፣ አማካይ

ውጤቶችና መደበኛ ልይይቶች ያሳያል፡፡ በሠንጠረዡ ለንጽጽር በሚረዳ መልኩ ከቀረበው መረጃ ማጤን እንደሚቻለው የሙከራ ቡድኑ እና የቁጥጥር ቡድኑ አንብቦ የመረዳት ፈተና አማካይ ውጤቶች በንጽጽር ሲታዩ፤ የሙከራው ቡድን ተጠኚዎች ድህረ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና የሙከራው ቡድን ተጠኚዎች አጠቃላይ የቡድን ውጤት 513 ከሙከራው ቡድን ተጠኚዎች አጠቃላይ የቡድን ውጤት 434 በ79 ነጥብ ብልጫ እንዳሳየ እንመለከታለን፡፡ በሌላ በኩል የሙከራው ቡድን ተጠኚዎች ድህረ-ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት 20.52 ከቁጥጥር ቡድኑ ተጠኚዎች ድህረ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና አማካይ ውጤት 17.36 በ3.16 በልጦ እንደሚገኝ ለመረዳት ተችሏል፡፡

ከዚህም ጎን ለጎን የሙከራው ቡድን ተጠኚዎች ድህረ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና መደበኛ ልይይት 1.98 ከቁጥጥሩ ቡድን ተጠኚዎች ድህረ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና መደበኛ ልይይት 2.81 በአማካይ መደበኛ ልይይት 0.83 በማነስ ልዩነት ማሳየቱን መረጃው ያመለክታል፡፡ ይህም የሚያመለክተው በድህረ-ትምህርት አንብቦ መረዳት ፈተናው የሙከራ ቡድን ተጠኚዎች ያገኙት ውጤት ከአማካይ ውጤቱ ያለው ርቀት ጠባብ መሆኑን እና ከቁጥጥር ቡድኑም የውጤት አማካይ ርቀት ያነሰ መሆኑን ነው፡፡ እነዚህን የገላጭ ስታቲስቲክ ውጤቶች መረጃ መሰረት በማድረግ በተጨማሪ ለመግለጽ የሚቻለውም የቁጥጥር እና የሙከራ ቡድኖቹ ድህረ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት ከአማካይ ውጤቱ ያለው ርቀት ተቀራራቢ ወይም የውጤት ከፍና ዝቅ የማለት ጠባዩ ያነሰ መሆኑን ይሆናል፡፡

ስታቲስቲካዊ ትንተናው እንዳመለከተው የሙከራው ቡድን ተጠኚዎች ድህረ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና አማካይ ውጤት ከቁጥጥር ቡድን ተጠኚዎች ድህረትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና አጠቃላይ የቡድን ውጤት የ79 ነጥብ ብልጫ፣ እንዲሁም አማካይ ውጤት የ3.16 ብልጫ ያለው መሆኑን አሳይቷል፡፡ ይህ የውጤት ብልጫ አነሰም በዛ ሊመዘገብ የቻለው ደግሞ የሙከራ ቡድኑ ተጠኚዎች በተዘጋጀላቸው ፍላጎት ተኮር አንብቦ የመረዳት ልምምድ አውድ የተሰጧቸውን ተግባራት ሲያከናውኑ በመቆየታቸው እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ ይሁንና በቁጥጥር ቡድኑና በሙከራ ቡድኑ ተጠኚዎች መካከል ስለሚታየው የአማካይ ውጤት ልዩነት የጉልህነት ደረጃ እርግጠኛ ለመሆን ደግሞ ድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ መተግበር ያስፈልጋል፡፡ በሠንጠረዥ 4 የነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ፍተሻ

በማካሄድ በሁለቱ ቡድኖች መካከል የሚታየው አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት የጉልህነት ደረጃ ተተንትኗል፡፡

**ሰንጠረዥ 4፡- የሙከራው እና የቁጥጥሩ ቡድኖች የድህረ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና አማካይ ውጤቶች የነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ንጽጽር**

| ተጠኚ | የናሙና መጠን (n) | አማካይ ውጤት (mean) | መደበኛ ልይይት (S.D.) | የነጻነት ደረጃ (df) | የ«ቲ» ዋጋ (t-value) | የጉልህነት ደረጃ (sig.2-tailed) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የሙከራ ቡድን | 25 | 20.52 | 1.98 | 24 | 5.179 | .000* |
| የቁጥጥር ቡድን | 25 | 17.36 | 2.81 | | | |

*ማስታወሻ፡- የጉልህነት ደረጃ አለ ለማለት $p<0.05$ (የፒ ዋጋ ከ0.05 በታች) መሆን ይኖርበታል፡፡

ከላይ በነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተሰልቶ በሰንጠረዥ 4 በቀረበው የድምዳሜ ስታቲስቲክስ መረጃ እንደተመለከተው፣ በሙከራ ቡድኑ እና በመቆጣጠሪያ ቡድኑ የድህረ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል ያለውን የአማካይ ውጤት ልዩነት የጉልህነት ደረጃ ቀርቦ እናገኛለን፡፡ የነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት መረጃው በሁለቱ ቡድኖች አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ውጤቱ (t= 5.179, df = 24, p= .000) አመልክቷል፡፡ ከስታቲስቲካዊ መረጃው በግልጽ ማጤን እንደሚቻለው አንብቦ መረዳትን በፍላጎት ተኮር አንብቦ መረዳት ማስተማሪያ ዘዴዎች ድጋፍ ለመማር ተጋልጠ ወይም እድል ያገኙት የሙከራው ቡድን ተጠኚዎች በነባሩ ወይም ልማዳዊው አንብቦ መረዳት ማስተማሪያ ዘዴ ከተማሩት የቁጥጥሩ ቡድን ተጠኚዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጉልህ ልዩነት ማሳየታቸውን ነው፡፡ p 0.000 ከ $p<0.05$ አንሶ መገኘቱ የሁለቱ ቡድኖች ድህረ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት አማካይ ውጤት ጉልህ በሚባል ደረጃ ልዩነት መታየቱን አመላካች ነው፡፡ ይህም ፍላጎት ተኮር አንብቦ መረዳትን ማስተማሪያ ዘዴ ከልማዳዊው አንብቦ መረዳትን ማስተማሪያ ዘዴ የተሻለ በሚያደርጉት ፍላጎት ላይ ላተኮሩ ተግባራት አጽንኦት በማድረጉ የሙከራ ቡድኑን ተጠኚዎች የማንበብ ፍላጎትና ያነበቡትን የመገንዘብ ችሎታ ለማሻሻል ጠቀሜታ ያለው መሆኑን ያመለክታል፡፡

የትንተናውን ውጤት መሰረት በማድረግም የመጀመሪያው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ፣ *የኦሮምኛ ቋንቋ አፊ-ፊት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል ያላቸው ፍላጎት በውጤታቸው ላይ ተጽዕኖው ምን ይመስላል?* ለሚለው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ የማንበብ ፍላጎትና ያነበቡትን የመገንዘብ ችሎታ ለማሻሻል ጉልህ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን በተግባር ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ይህንን የተጠኚዎቹን በመማሪያ አውድ ልዩነት ላይ የተመሰረተ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለውጥ ይበልጥ ለማረጋገጥ እያንዳንዱ ቡድን በቅድመ-ትምህርትና ድህረ-ትምህርት ያስመዘገበውን አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት በማነጻጸር መፈተሽ ያስፈልጋል፡፡ በዚሁ መሰረት የሙከራ ቡድኑ አባላት በቅድመ-ትምህርትና በድህ-ረትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤቶች መካከል የቱን ያህል የመሻሻል ልዩነት ማሳየት እንደቻሉ ለማወቅ በተደረገው ፍተሻ የተገኘው ውጤት እንደሚከተለው በሰንጠረዥ 5 እና 6 ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 5:- የሙከራው ቡድን የቅድመ-ትምህርትና ድህረ-ትምህርት አንብቦ መረዳት ፈተና አማካይ ውጤቶች የገላጭ ስታትስቲክስ ንጽጽር**

| የሙከራ ቡድን | የናሙና መጠን (n) | አማካይ ውጤት (mean) | መደበኛ ልይይት (S.D.) | መደበኛ የአማካይ ስህተት (Std.Error Mean) |
|---|---|---|---|---|
| ቅድመ-ትምህርት | 25 | 16.48 | 2.62 | .523 |
| ድህረ-ትምህርት | 25 | 20.52 | 1.98 | .396 |

በሠንጠረዥ 5 በቀረበው የገላጭ ስታቲስቲክስ መረጃ በተናጠል የሙከራውን ቡድን የቅድመ-ትምህርትና ድህረ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና አማካይ ውጤቶችና መደበኛ ልይይቶች ያሳያል፡፡ በሠንጠረዡ ከቀረበው መረጃ መረዳት እንደሚቻለውም አማካይ ውጤቶቹ በንጽጽር ሲታዩ የሙከራው ቡድን ተጠኚዎች ድህረ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና አማካይ ውጤት 20.52 ከቅድመትምህርቱ አንብቦ የመረዳት ፈተና አማካይ ውጤት 16.48 የ4.04 አማካይ ውጤት ብልጫ ማሳየቱን እንመለከታለን፡፡

ከዚህም ጎን ለጎን የሙከራው ቡድን ተጠኚዎች ድህረ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና መደበኛ ልይይት 2.62 ከቅድመ-ትምህርቱ አንብቦ የመረዳት ፈተና መደበኛ ልይይት 1.98 በ0.64 አንሶ ልዩነት አሳይቷል፡፡ ይህም የሚያመለክተው የሙከራው ቡድን ድህረ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት ከአማካይ ውጤቱ ያለው ርቀት ከቅድመ-ትምህርቱ የአማካይ ውጤት ርቀት በተሻለ መልኩ የጠበበ ልዩነት ያለው መሆኑን ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የሙከራው ቡድን ተጠኚዎች በፍላጎት ተኮር አንብቦ የመረዳት ልምምድ አውድ ከቆዩ በኋላ ከቅድመ-ትምህርቱ አንብቦ የመረዳት ፈተና በአንድ በኩል የውጤት መሻሻል ሲያሳዩ በሌላ በኩል ደግሞ የእያንዳንዳቸው ውጤት ከአማካይ ውጤቱ ያለው ርቀት በተሻለ ሁኔታ ጠብቦ በመካከላቸው የሚታየው አንብቦ የመረዳት ልዩነትም ከቅድመ-ትምህርቱ አንብቦ የመረዳት ፈተና ሲነጻጸር ቀንሶ ተገኝቷል ማለት ነው፡፡

ከፍ ሲል በቀረበው ትንተና መሰረት የሙከራው ቡድን ተጠኚዎች ድህረ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና አማካይ ውጤት ከቅድመ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና አማካይ ውጤት በ4.04 እንደበለጠ ውጤቱ አመልክቷል፡፡ በሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ቅድመ እና ድህረ-ትምህርት ፈተናዎች መካከል ስላለው የአማካይ ውጤት ልዩነት የጉልህነት ደረጃ እርግጠኛ ለመሆን ግን ድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ መጠቀም የሚያስፈልግ በመሆኑ በሠንጠዥ 6 የዳግም ልኬት ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተግባራዊ ሆኗል፡፡

**ሠንጠረዥ 6፡- የሙከራው ቡድን ቅድመ-ትምህርትና ድህረ-ትምህርት አንብቦ መረዳት ፈተና አማካይ ውጤቶች የዳግም ልኬት ናሙናዎች ቲ-ቴስት ንጽጽር**

| የሙከራ ቡድን | የናሙና መጠን | አማካይ ውጤት (mean) | መደበኛ ልይይት (S.D.) | የነጻነት ደረጃ (df) | የ«ቲ» ዋጋ | የጉልህነት ደረጃ (sig.2-tailed) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ-ትምህርት | 25 | 16.48 | 2.62 | 24 | 7.385 | .000* |
| ድህረ-ትምህርት | 25 | 20.52 | 1.98 | | | |

*p<0.05

ከላይ በሰንጠረዥ 6 የቀረበው የዳግም ልኬት ናሙናዎች ቲ-ቴስት የሙከራው ቡድን ተማሪዎች የቅድመ-ትምህርትና ድህረ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተናዎች አማካይ ውጤቶች መካከል ያለውን ልዩነት የጉልህነት ደረጃ ያመለክታል፡፡ የሁለቱ አውዶች የፈተና ውጤት መረጃዎች በዳግም ልኬት ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተሰልቶ በቅድመ-ትምህርቱና በድህረ-ትምህርቱ ፈተናዎች አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ውጤቱ (t= 7.385, df= 24, p= .000) አመላክቷል፡፡ ይህም የሚያሳየው የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች አንብቦ መረዳትን በፍላጎት ተኮር የማስተማሪያ ዘዴዎችና ፍላጎትን ማእከል ባደረጉ አንብቦ የመረዳት ተግባራዊ ልምምዶች ቆይታ በኋላ አስቀድሞ ከነበራቸው አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጉልህ የሆነ አንብቦ የመረዳት ፍላጎትና ችሎታ መሻሻል ማሳየታቸውን ነው፡፡ በዚህ መሰረት ፍላጎት ተኮር የማስተማሪያ ዘዴው አንብቦ የመረዳት ፍላጎታቸው እንዲያድግና አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው እንዲሻሻል ረድቷቸዋል ከሚል ድምዳሜ ላይ መድረስ ይቻላል፡፡ ይህ ደግሞ ቀደም ሲል የሙከራው ቡድን ከቁጥጥር ቡድኑ የበለጠ ውጤት ማስመዝገቡን በነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት የተገኘውን ውጤት ያረጋግጣል፡፡

በተመሳሳይ በቁጥጥር ቡድኑ ተጠኚዎች የቅድመ-ትምህርትና የድህረ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተናዎች ውጤቶች መካከል ልዩነት ስለመኖር /አለመኖሩ የአማካይ ውጤቶች ንጽጽር በማድረግ የተገኘው ውጤት እንደሚከተለው በሰንጠረዥ 7 እና 8 ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 7:- የቁጥጥር ቡድኑ የቅድመ-ትምህርትና ድህረ-ትምህርት አንብቦ መረዳት ፈተና አማካይ ውጤቶች የገላጭ ስታትስቲክስ ንጽጽር**

| የቁጥጥር ቡድን | የናሙና መጠን (n) | አማካይ ውጤት (mean) | መደበኛ ልይይት (S.D.) | መደበኛ የአማካይ ስህተት (Std.Error Mean) |
|---|---|---|---|---|
| ቅድመ-ትምህርት | 25 | 16.28 | 2.89 | .579 |
| ድህረ-ትምህርት | 25 | 17.36 | 2.81 | .562 |

በሰንጠረዥ 7 የቁጥጥር ቡድኑ የቅድመ-ትምህርትና ድህረ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና አማካይ ውጤቶችና መደበኛ ልይይቶች ቀርበዋል፡፡ በሰንጠረዡ ከቀረበው መረጃ

መረዳት እንደሚቻለውም አማካይ ውጤቶቹ በንጽጽር ሲታዩ የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ድህረ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና አማካይ ውጤት (17.36) ከቅድመ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና አማካይ ውጤት (16.28) በ1.08 በልጦ ይገኛል፡፡

ከዚህም ጋር የድህረ-ትምህርቱ አንብቦ የመረዳት ፈተና መደበኛ ልይይት (2.81) ከቅድመ-ትምህርቱ አንብቦ የመረዳት ፈተና መደበኛ ልይይት (2.89) በ0.08 በማነስ ልዩነት አሳይቷል፡፡ ይህም ከትምህርቱ በኋላ የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ድህረ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት ከአማካዩ ያለው ርቀት ተቀራራቢ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ከላይ በቀረበው ትንተና መሰረት የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ድህረ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና አማካይ ውጤት ከቅድመ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና አማካይ ውጤት በ1.08 እንደበለጠ መረጃው ያመለክታል፡፡ በድህረ-ትምህርቱ የተገኘው የአንብቦ መረዳት ፈተና አማካይ ውጤት ከቅድመ-ትምህርቱ የአንብቦ መረዳት ፈተና አማካይ ውጤት ስላለው ልዩነት የጉልህነት ደረጃ እርግጠኛ ለመሆን ግን ድምዳሚያዊ ስታትስቲክስ መጠቀም ስለሚያስፈልግ ከስር በሰንጠዥ 8 እንደተመለከተው የዳግም ልኬት ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

**ሰንጠረዥ 8፡- የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ-ትምህርትና ድህረ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና አማካይ ውጤቶች የዳግም ልኬታ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ንጽጽር**

| የቁጥጥር ቡድን | የናሙና መጠን | አማካይ ውጤት (mean) | መደበኛ ልይይት (S.D.) | የነጻነት ደረጃ (df) | የ«ቲ» ዋጋ | የጉልህነት ደረጃ (sig.2-tailed) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ-ትምህርት | 25 | 16.28 | 2.89 | 24 | -6.647 | .069 |
| ድህረ-ትምህርት | 25 | 17.36 | 2.81 | | | |

p<0.05

በሰንጠረዥ 8 የቀረበው የድምዳሜ ስታቲስቲክስ መረጃ በቁጥጥር ቡድኑ በቅድመ-ትምህርትና ድህረ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል ያለውን ልዩነት የጉልህነት ደረጃ ያሳያል፡፡ መረጃው በዳግም ልኬታ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተሰልቶ

በቅድመ-ትምህርቱና በድህረ-ትምህርቱ ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ውጤቱ (t= -6.647, df = 24, p= 0.069) አመላክቷል፡፡ (p= 0.069 ከ$p<0.05$ በልጦ መገኘቱን ልብ ይሏል፡፡) ከዚህ በግልጽ የምንገነዘበው የቁጥጥር ቡድኑ ተጠኚዎች በልማዳዊው አንብቦ መረዳት ማስተማሪያ ዘዴ አንብቦ መረዳትን ከተማሩ በኋላ በአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ጉልህ ለውጥ አለማምጣታቸውን ነው፡፡ ይህም ቀደም ሲል በነጻ ናሙናዎች ቲ- ቴስት የተገኘው ውጤት የሙከራው ቡድን ድህረ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና አማካይ ውጤት ከቁጥጥር ቡድኑ እንደበለጠ የሚያሳውን በድጋሚ ያረጋግጣል፡፡

ሌላው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ *የኦሮምኛ ቋንቋ አፈ-ፈት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፍላጎት ለማሻሻል በሚረዱ ብልሃቶች ትግበራ ያላቸው ምላሽ ምን ይመስላል?* የሚለው ሲሆን፤ የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በፍላጎት ተኮር የማስተማሪያ ብልሃቶች የተደገፉ አንብቦ የመረዳት ልምምዶች በኋላ በፍላጎት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴው ትግበራ ያገኙት አጠቃላይ ግንዛቤ ቀድሞ ከነበራቸው ግንዘቤ ተሽሎ መገኘት አለመገኘቱን፣ የአንብቦ መረዳት ፍላጎታቸው መሻሻል አለመሻሻሉን እንዲሁም የማንበብ ችሎታቸው ላይ ያለውን ለውጥ ለማወቅ በጽሁፍ መጠይቅ አማካኝነት በቅድመ እና ድህረ-ትምህርት የተሰበሰበው መረጃ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ ውጤቱም በሰንጠረዥ 9 እና 10 ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 9፡- የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በፍላጎት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ ላይ ያላቸው ፍላጎት ቅድመ እና ድህረ-ትምህርት የጽሑፍ መጠይቅ አጠቃላይና አማካይ ውጤት የገላጭ ስታትስቲክስ ንጽጽር**

| የጽሁፍ መጠይቅ | የናሙና መጠን (n) | አጠቃላይ አማካይ ውጤት | አማካይ ውጤት (mean) | መደበኛ ልይይት (S.D.) | መደበኛ የአማካይ ስህተት (Std. Error Mean) |
|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ-ትምህርት | 25 | 100.20 | 2.51 | .139 | .0219 |
| ድህረ-ትምህርት | 25 | 151.28 | 3.78 | .127 | .0201 |

ከላይ በሰንጠረዥ 9 የቀረበው ስታቲስቲካዊ መረጃ የሙከራውን ቡድን የቅድመ-ትምህርትና ድህረ-ትምህርት በፍላጎት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ ላይ ያላቸው ፍላጎት ቅድመ እና ድህረ-ትምህርት የጽሑፍ መጠይቅ አጠቃላይ አማካይ ውጤት የገላጭ ስታቲስቲክስ ንጽጽርን ያሳያል፡፡ በዚሁ መሰረት በሰንጠረዡ ከቀረበው ስታቲስቲካዊ መረጃ መረዳት እንደሚቻለው በድህረ-ትምህርቱ በፍላጎት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ ላይ ያላቸው ፍላጎት አጠቃላይ አማካይ ውጤት (151.28) ከቅድመ-ትምህርቱ የጽሑፍ መጠይቅ አጠቃላይ አማካይ ውጤት (100.20) በ 51.08 በልጦ ይገኛል፡፡ በሌላ በኩል በድህረ-ትምህርት በፍላጎት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ ላይ ያሳዩት ፍላጎት አማካይ ውጤት (3.78) ከቅድመ-ትምህርቱ አማካይ ውጤት (2.51) የ1.27 አማካይ ውጤት ብልጫ አሳይቷል፡፡

ከዚህም ጋር የሙከራው ቡድን ድህረ-ትምህርት በፍላጎት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ ላይ ያላቸው ፍላጎት የጽሑፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት መደበኛ ልይይት (0.139) ከቅድመ-ትምህርቱ የጽሑፍ መጠይቅ መደበኛ ልይይት (0.127) በ0.012 አንሶ መጠነኛ ልዩነት አሳይቷል፡፡ ይህም ከፍላጎት ተኮር ትምህርቱ ትግበራ በኋላ የተጠኚዎቹ በፍላጎት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ ላይ ያላቸው ፍላጎት የጽሑፍ መጠይቅ ውጤት ከአማካዩ ያለው ርቀት እየጠበበ መሄዱን የሚያመለክት ነው፡፡ በአጠቃላይ የመደበኛ ልይይቱ ርቀት ጠባብ መሆን ተጠኚዎቹ ለጽሁፍ መጠይቁ የሰጧቸው ምላሾች ከአማካይ ውጤቱ ያለው ርቀት ወጥነት ያለው ወይም በተመሳሳይ መንገድ ምላሽ የሰጡ መሆኑን ይጠቁማል፡፡

ከላይ በቀረበው ትንተና የሙከራው ቡድን ተማሪዎች ድህረ-ትምህርት በፍላጎት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ ላይ ያላቸው ፍላጎት መለኪያ የጽሑፍ መጠይቅ አጠቃላይ አማካይ ውጤት ከቅድመ-ትምህርቱ በፍላጎት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ ላይ ያላቸው ፍላጎት የጽሑፍ መጠይቅ አጠቃላይ አማካይ ውጤት በ51.08 እንዲሁም በ1.27 አማካይ ውጤት እንደበለጠ የገላጭ ስታቲስቲክሱ ንጽጽራዊ ውጤት አመላክቷል፡፡ በቅድመ-ትምህርት እና በድህረ-ትምህርት ደረጃ ስላለው ልዩነት የጉልህነት ደረጃ እርግጠኛ ለመሆን ደግሞ ድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ በሰንጠዥ 10 የዳግም ልኬት ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተተግብሯል፡፡

ሰንጠረዥ 10፡- የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በፍላጎት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ ላይ ያላቸው ፍላጎት ቅድመ እና ድህረ-ትምህርት የጽሑፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት ልዩነት በዳግም ልኬት ናሙናዎች ቲ-ቴስት

| የጽሁፍ መጠይቅ | የናሙና መጠን | አማካይ ውጤት (mean) | መደበኛ ልይይት (S.D.) | የነጻነት ደረጃ (df) | የ«ቲ» ዋጋ | የጉልህነት ደረጃ (sig.2-tailed) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ-ትምህርት | 25 | 100.20 | .139 | 24 | -37.399 | .000 |
| ድህረ-ትምህርት | 25 | 151.28 | .127 | | | |

$p<0.05$

በሰንጠረዥ 10 እንደቀረበው በሙከራ ቡድኑ በቅድመ-ትምህርትና ድህረ-ትምህርት በፍላጎት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ ላይ ያላቸው ፍላጎት አማካይ ውጤት መካከል ያለውን ልዩነት የጉልህነት ደረጃ ያሳያል፡፡ መረጃው በዳግም ልኬት ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተሰልቶ በቅድመ-ትምህርቱና በድህረ-ትምህርቱ በፍላጎት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ ላይ ያላቸው ፍላጎት አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ውጤቱ (t= -37.399, df= 24, p= .000) አመላክቷል፡፡ p= .000 ከ $p<0.05$ የሚያንስ መሆኑ በሁለቱ ዙር ምላሾች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ጠቋሚ ነው፡፡ ከዚህ የምንረዳውም የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በፍላጎት ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ ላይ የተመሰረቱ አንብቦ የመረዳት ልምምዶችን ካካሄዱ በኋላ አስቀድሞ ስለ ማስተማሪያ ዘዴው ጠቀሜታ ከነበራቸው ፍላጎት ጉልህ ልዩነት ማሳየቱን ነው፡፡ በዚህም መሰረት በፍላጎት ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ በመደገፍ አንብቦ መረዳትን ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ፍላጎት ለማሳደግ የሚያስችል መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

ከላይ የቀረበው ትንተና ያመለከተው ተጠኚዎቹ ለፍላጎት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ አጠቃላይ ትግበራ በድህረ-ትምህርት ያሳዩት ፍላጎት ከቅድመ-ትምህርቱ የቱን ያህል ተሽሎ እንደተገኘ በጥቅል የፍላጎት ልኬት ደረጃ ነበር፡፡ ቀጥሎ ደግሞ የሙከራ ቡድኑ ተጠኚዎች በቅድመ እና ድህረ-ትምህርት ለቀረበላቸው የፍላጎት መለኪያ የጽሁፍ መጠይቅ

‹‹አጠቃላይ የስነዘዴው ፍላጎት››፣ ‹‹በዘዴው አንብቦ የመረዳት ፍላጎት›› እና ‹‹የማንበብ ችሎታ›› ተላውጦዎች የሰጧቸው ምላሾች አማካይ ውጤቶች መካከል መመሳሰል መኖር አለመኖሩን ለመፈተሽ ተሞክሯል፡፡ ለሶስቱ የፍላጎት ተላውጦዎች - ‹‹አጠቃላይ የስነዘዴው ፍላጎት››፣ ‹‹በዘዴው አንብቦ የመረዳት ፍላጎት›› እና ‹‹የማንበብ ችሎታ›› - የሰጧቸው የጽሁፍ መጠይቅ ምላሾች በተናጠል በገላጭ ስታቲስቲክስ እና ዳግም ልኬት ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተሰልተው ከዚህ በታች በሰንጠረዥ 11 እና 12 ቀርበዋል፡፡

**ሰንጠረዥ 11፡- የሙከራ ቡድኑ ተጠኚዎች የቅድመ እና ድህረ-ትምህርት ለፍላጎት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴው ተላውጦዎች የሰጧቸው የጽሁፍ መጠይቅ ምላሾች የገላጭ ስታቲስቲክስ ንጽጽር**

| የፍላጎት ተላውጦዎች | የጽሁፍ መጠይቅ | የናሙና መጠን | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | መደበኛ የአማካይ ስህተት |
|---|---|---|---|---|---|
| አጠቃላይ ፍላጎት | ቅድመ-ትምህርት | 25 | 49.76 | .138 | .0316 |
| | ድህረ-ትምህርት | 25 | 74.16 | .1123 | .0253 |
| የማንበብ ፍላጎት | ቅድመ-ትምህርት | 25 | 30.04 | .1137 | .0328 |
| | ድህረ-ትምህርት | 25 | 46.64 | .0699 | .0202 |
| የማንበብ ችሎታ | ቅድመ-ትምህርት | 25 | 20.40 | .1811 | .0641 |
| | ድህረ-ትምህርት | 25 | 30.48 | .1146 | .0405 |

ከላይ የቀረበው መረጃ የጽሁፍ መጠይቁ ባተከረባቸው ሶስቱ የፍላጎት ተላውጦዎች የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በቅድመ እና ድህረ-ትምህርት የሰጧቸውን ምላሾች አማካይ ውጤቶች የገላጭ ስታቲስቲስ ንጽጽርን ያሳያል፡፡ በዚሁ መሰረት የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ድህረ-ትምህርት አጠቃላይ የስነዘዴው ፍላጎት አማካይ ውጤት (74.16) ከቅድመ-ትምህርቱ አጠቃላይ የስነዘዴው ፍላጎት አማካይ ውጤት (49.76) የ24.4 አማካይ ውጤት ብልጫ አስመዝግበዋል፡፡ በትይዩ የድህረ-ትምህርት አጠቃላይ የስነዘዴው ፍላጎት

አማካይ ውጤት መደበኛ ልይይት (0.1137) ከቅድመ-ትምህርቱ አጠቃላይ የስነዘዴው ፍላጎት አማካይ ውጤት መደበኛ ልይይት (0.138) የ-0.0243 መደበኛ ልይይት በመቀነስ አሳይቷል፡፡ ይህም በድህረ-ትምህርቱ የጽሁፍ መጠይቅ ለአጠቃላይ ፍላጎት ተላውጠ የሰጡት ምላሽ ከአማካይ ውጤቱ ያለው ርቀት ከቅድመ-ትምህርቱ በተሻለ በጣም ጠባብ ወይም የማይዋዥቅ መሆኑን ይጠቁማል፡፡

በሌላ በኩል የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ድህረ-ትምህርት የማንበብ ፍላጎት ተላውጠ አማካይ ውጤት (46.64) ከቅድመ-ትምህርቱ የማንበብ ፍላጎት አማካይ ውጤት (30.04) የ16.6 አማካይ ውጤት ብልጫ አስመዝግበዋል፡፡ በአንጻሩ የድህረ-ትምህርቱ የማንበብ ፍላጎት አማካይ ውጤት መደበኛ ልይይት (0.0699) ከቅድመ-ትምህርቱ አጠቃላይ የማንበብ ፍላጎት አማካይ ውጤት መደበኛ ልይይት (0.1137) በ-0.0438 መደበኛ ልይይት ቅነሳ ልዩነት  አሳይቷል፡፡ ይህም በድህረ-ትምህርቱ የጽሁፍ መጠይቅ ለማንበብ ፍላጎት ተላውጠ የሰጡት ምላሽ ከአማካይ ውጤቱ ያለው ርቀት ከቅድመ-ትምህርቱ ያነሰና በጣም ጠባብ ወይም ወጥ በሆነ መንገድ የቀረበ መሆኑን ይጠቁማል፡፡

በመጨረሻ የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ድህረ-ትምህርት የማንበብ ችሎታ ተላውጠ አማካይ ውጤት (30.48) ከቅድመ-ትምህርቱ የማንበብ ችሎታ አማካይ ውጤት (20.40) የ10.08 አማካይ ውጤት ብልጫ አስመዝግበዋል፡፡ በአንጻሩ የድህረ-ትምህርቱ የማንበብ ችሎታ አማካይ ውጤት መደበኛ ልይይት (0.1146) ከቅድመ-ትምህርቱ የማንበብ ችሎታ አማካይ ውጤት መደበኛ ልይይት (0.1811) በ-0.668 መደበኛ ልይይት ቅነሳ ልዩነት  አሳይቷል፡፡ ይህም በድህረ-ትምህርቱ የጽሁፍ መጠይቅ ለማንበብ ችሎታ ተላውጠ የሰጡት ምላሽ ከአማካይ ውጤቱ ያለው ርቀት ከቅድመ-ትምህርቱ ያነሰና በጣም ጠባብ ወይም ወጥ በሆነ መንገድ የቀረበ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ከላይ የቀረበው ትንተና ያመለከተው ተጠኚዎቹ ለፍላጎት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ ተላውጠዎች በድህረ-ትምህርት ያሳዩት ፍላጎት ወጥነት ባለው መልኩ ከቅድመ-ትምህርቱ የተሻለ መሆኑን አመላካች ነው፡፡ የሙከራ ቡድኑ ተጠኚዎች በድህረ-ትምህርት አጠቃላይ የስነዘዴው ፍላጎት ከቅድመ-ትምህርቱ የ24.4 አማካይ ውጤት ብልጫ፣ በድህረ-ትምህርት የማንበብ ፍላጎት ተላውጠ ከቅድመ-ትምህርቱ የ16.6 አማካይ ውጤት ብልጫ እንዲሁም በድህረ-ትምህርት የማንበብ ችሎታ ከቅድመ-ትምህርቱ የ10.08 አማካይ ውጤት ብልጫ

እንዳስመዘገቡ ትንተናው አመላክቷል፡፡ ሆኖም በየተላውጦዎቹ የተመዘገቡት የአማካይ ውጤት ብልጫዎች የጉልህነት ደረጃ ምን እንደሚመስል ለማወቅ ለየተላውጦዎቹ የዳግም ልኬት ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ውጤቱ በሰንጠረዥ 12 ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 12፡- የሙከራ ቡድኑ ተጠኚዎች የቅድመ እና ድህረ-ትምህርት ለፍላጎት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴው ተላውጦዎች የሰጧቸው የጽሁፍ መጠይቅ ምላሾች የዳግም ልኬት ናሙናዎች ቲ-ቴስት ንጽጽር**

| የፍላጎት ተላውጦዎች | የጽሁፍ መጠይቅ | የናሙና መጠን | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የነጻነት ደረጃ (df) | የ«ቲ» ዋጋ | የጉልህነት ደረጃ (sig.2 tailed) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| አጠቃላይ የስነዘዴ ፍላጎት | ቅድመ-ትምህርት | 25 | 49.76 | .138 | 24 | -27.81 | .000* |
| | ድህረ-ትምህርት | 25 | 74.16 | .1123 | | | |
| የማንበብ ፍላጎት | ቅድመ-ትምህርት | 25 | 30.04 | .1137 | 24 | -27.76 | .000 |
| | ድህረ-ትምህርት | 25 | 46.64 | .0699 | | | |
| የማንበብ ችሎታ | ቅድመ-ትምህርት | 25 | 20.40 | .1811 | 24 | -12.64 | .000 |
| | ድህረ-ትምህርት | 25 | 30.48 | .1146 | | | |

p<0.05

በሰንጠረዥ 12 ከቀረበው መረጃ መመልከት እንደሚቻለው በቀረቡት የፍላጎት ተላውጦዎች ሁሉ ወጥ በሆነ መልኩ ጉልህ የፍላጎት እንደታየ ማጤን ይቻላል፡፡ በቅደም ተከተል ለአጠቃላይ የስነዘዴው ፍላጎት ተላውጦ (t= -27.81, df= 24, p= .000)፣ ለማንበብ ፍላጎት ተላውጦ (t= -27.76, df= 24, p= .000)፣ እንዲሁም ለማንበብ ችሎታ ተላውጦ (t= -12.64 df= 24, p= .000) መሆኑ የዳግም ልኬት ናሙናዎች ቲ-ቴስቱ ውጤት

አመላክቷል፡፡ በሦስቱም የፍላጎት ተላውጦዎች p= .000 ከ $p<0.05$ አንሶ መገኘቱን ልብ ይሏል፡፡

ከዚህ የዳግም ልኬት ናሙናዎች ቲ-ቴስት ውጤት መደምደም የሚቻለውም የኦሮምኛ ቋንቋ አፌ-ፈት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፍላጎት ለማሻሻል በሚረዱ ብልሃቶች ትግበራ ያላቸው ምላሽ ጠንካራና አዎንታዊ ሲሆን የፍላጎት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ ልምምድ የሙከራ ቡድኑን የማስተማሪያ ዘዴው ፍላጎት፣ የማንበብ ፍላጎትና የማንበብ ችሎታ በማሻሻል ረገድ ጉልህ አስተዋጽኦ ያለው መሆኑን ነው፡፡
በመጨረሻም በፍላጎት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴና በአንብቦ መረዳት ውጤት መካከል ያለውን ተዛምዶ ለመተንተንም ፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ (Pearson Correlation coefficient) ተሰልቷል፡፡

### ሰንጠረዥ 13፡- የፒርሰን የተዛምዶ ልኬት

**Paired Samples Correlations**

| | N | Correlation | Sig. |
|---|---|---|---|
| የፈተና ውጤትና የመጠይቅ ምላሽ ተዛምዶ | 25 | .204 | .050 |

በሙከራ ቡድኑ ተጠኚዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የአንብቦ መረዳት ፍላጎት መካከል ያለውን ተዛምዶ ለመለካት የረዳው የሙከራ ቡድኑን ተጠኚዎች የድህረ-ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት በመውሰድ ከድህረ-ትምህርት የፍላጎት መለኪያ የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ ጋር ያለውን ግንኙነት ለማወቅ የፒርሰን ተዛምዶ ቀመር ተግባራዊ በማድረግ ነው፡፡ በስታቲስቲካዊ መረጃው መሰረት የፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ (Pearson Correlation coefficient) ተሰልቶ ($P = 0.204$, $\alpha = 0.05$) ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም ማለት ድህረ-ትምህርት የሙከራ ቡድኑ አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት ($r = 0 .204$, $P = .050$፣ በባለ ሁለት ጫፍ ጉልህነት ደረጃ አዎንታዊ የፍላጎትና አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት ግንኙነት መኖሩን አመልክቷል፡፡ ይህም በሙከራ ቡድኑ ድህረ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት እና በተማሪ ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ መካከል ጉልህ አዎንታዊ ተዛምዶ መታየቱን ያሳያል፡፡

### 4.2 የትንተናው ውጤት ትርጎማ

በጥናቱ መረጃ ትንተና ክፍል የምርምሩን መሰረታዊ ጥያቄዎች መነሻ በማድረግ በቀረቡት መረጃዎች ላይ ሰፋ ባለ መልኩ ትንተና ቀርቧል፡፡ በዚህ መሰረት የጥናቱ የመጀመሪያው ጥያቄ ምላሽ ያገኘው ከሙከራ እና ቁጥጥር ቡድኖቹ በቅድመ-ትምህርት እና ድህረ-ትምህርት በተወሰዱ አንብቦ የመረዳት ፈተና መረጃዎች ሲሆን የቅድመ-ትምህርቱ አንብቦ የመረዳት ፈተና መረጃ ሁለቱን የጥናቱ ተተኳሪ ቡድኖች አባላት በአንጻራዊ ተመጣጣኝ አንብቦ የመረዳት ችሎታ መገኘት አረጋግጦ በዋናው የምርምሩ አውድ ለማሳተፍ ረድቷል፡፡ የድህረ-ትምህርቱ አንብቦ የመረዳት ፈተና በበኩሉ ሁለቱ ተተኳሪ ቡድኖች በየተመደበላቸው መማሪያ አውድ በየተመደበላቸው የማስተማሪያ ዘዴዎች (የሙከራ ቡድኑ በፍላጎት ተኮር፣ የመቆጣጠሪያ ቡድኑ በተለምዷዊ ማስተማሪያ ዘዴ) በቂ የአንብቦ መረዳት ልምምድ አድርገው ከቆዩ በኋላ ለአዲሱ የማስተማሪያ ዘዴ ተጋልጦ ያገኘው የሙከራ ቡድን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ጉልህ መሻሻል ማሳየት አለማሳየቱን ለማረጋገጥ የቀረበ ነበር፡፡ በዚህ መሰረት የሁለቱ ቡድኖች የቅድመ እና ድህረ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና መረጃዎች በገላጭ ስታቲስቲክና ድምዳሜ ስታቲስቲክስ እና በነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተሰልተው የተገኘው ውጤት ተተንትኖ ለትርጎማ ቀርቧል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ለሁለተኛው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት ከሙከራ ቡድኑ ተጠኚዎች ብቻ በቅድመ እና ድህረ-ትምህርት በፍላጎት መለኪያ የጽሁፍ መጠይቅ ሁለት ጊዜ የተሰበሰበው መረጃ በገላጭና ድምዳሜያዊ ስታቲስቲክስ እና በዳግም-ልኬት ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተተንትነዋል፡፡

ከተተነተኑት መጠናዊ መረጃዎች የተገኘው ውጤት እርስ በርስ ተደጋጋፊ በሆነ መልኩ ፍላጎት ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የማንበብ ፍላጎትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማጎልበት ከፍ ያለ አስተዋጽኦ ያላቸው መሆናቸውን ያመለክታል፡፡

በዚሁ መሰረት የመጀመሪያው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ የኦሮምኛ ቋንቋ አፈ-ፈት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል ያላቸው ፍላጎት በውጤታቸው ላይ ተጽዕኖው ምን ይመስላል? የሚል ሲሆን ሁለቱ በቅድመ-ትምህርት ተመጣጣኝ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ የነበራቸው ተጠኚዎች (ሰንጠረዥ 1) በተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎች ማለትም የሙከራ ቡድኑ በፍላጎት ተኮር፣ የመቆጣጠሪያ ቡድኑ በተለምዷዊ ማስተማሪያ

ዘዴ በቂ የአንብቦ መረዳት ልምምድ አድርገው ከቆዩ በኋላ፣ ለአዲሱ የማስተማሪያ ዘዴ ተጋላጭነት ያገኘው የሙከራው ቡድን በልማዳዊው ዘዴ አንብቦ መረዳትን ሲማር ከቆየው የቁጥጥር ቡድን አብላጫ የአማካይ ውጤት ማስመዝገቡን (ሰንጠረዥ 3) የመረጃ ትንተናው አመላክቷል፡፡ የጥናቱ ውጤት እንዳረጋገጠው በሁለቱ ቡድኖች የድህረ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና አማካይ ውጤቶች ንጽጽር መሰረት የሙከራው ቡድን ተጠኚዎች ከራሳቸው የቅድመ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤትም ሆነ ከቁጥጥር ቡድኑ ተጠኚዎች የድህረ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት የልዩነት የጉልህነት ደረጃው ከፍተኛ ነው (ሰንጠረዥ 5)፡፡

በዚህ መሰረት የሙከራ ቡድኑ ተጠኚዎች የማንበብ ክሂል መሻሻል፣ አንብቦ የመረዳት ችሎታና ፍላጎት እድገት የታየው በርግጥም በክፍል ውስጥ ፍላጎት ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ ልዩ ልዩ ግብአቶች፡- ተማሪዎቹ የቋንቋ መማር አስተሳሰብ እንዲያዳብሩ ማድረግ፣ ተማሪዎች በእውቀትና ክህሎት ሊደርሱበት የሚገባ ፍላጎትን በውስጣቸው ማስረጽ፣ ተማሪዎች የሚደረስባቸው የቋንቋ መማር ግቦችን እንዲያስቀምጡ መገፋፋት፣ ተማሪዎች በራስ የመተማመን ስሜት እንዲገነቡ ማበረታታት፣ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ለማንሰራራት የሚረዱ አዳዲስ የማስተማሪያ ብልሃቶችን መተግበር (የቃላት ጫዋታ፣ የፕሮጀክት ክንዋኔ፣ ሚና ጫዋታ፣ ችግር ፈቺ የማስተማሪያ ብልሃት፣ በመደጋገፍ መማር፣ ብጤን ማስተማር እና ማነቃቃት)፣ የተለያዩ ቋንቋ ነክ ተግባራትን መገልገል (በእለት ተእለት ግንኙነት የሚጠቀሙባቸውን አውዳዊ ተግባራትና ክንውኖችን ለተማሪዎቹ ማቅረብ፣ አገላለጾችንና ድርጊቶችን በድርጊት ጭምር እንዲለማመዱ ማድረግ) ላይ ያተኮሩ ተግባራት … በአንብቦ መረዳት አውድ በሚገባ በመጠቀማቸው የድህረ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤታቸውን ጉልህ በሚባል መልኩ ለማሻሻል ያስቻላቸው መሆኑን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

ይህ ጥናት የኔሰው (1990)፣ ‹‹በሁለተኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ክሂላቸውን ለማዳበር ተራክቧዊ የንባብ ክሂልን ማስተማሪያ ሞዴል በክፍል ውስጥ ተጠቅሞ ማስተማር ያለው አስተዋጽኦ›› በሚል ርእስ ያቀረቡት ጥናት ውጤት ጋር በከፊል መመሳሰል ይታይበታል፡፡ የየኔሰው ጥናት  ዋነኛ ዓላማ አድርጎ የተነሳው ተራክቧዊ የንባብ ክሂልን ማስተማሪያ ሞዴል በሁለተኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ክሂላቸውን ለማዳበር ያለውን አስተዋጽኦ

በመፈተሽ ላይ ነው፡፡ በቅድመ ፈተና ያገኙት መረጃን መሰረት በማድረግ በሁለቱ ቡድኖች መካከል የባህሪ ተመሳሳይነት የሚታይ መሆኑን አረጋግጠ ከቅድመ ፈተና በኋላ ጥብቅ ቡድኑን በልማዳዊ ዘዴ ማስተማሪያ ክፍል፣ ተጠኚ ቡድኑን በተራክቧዊ ዘዴ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል ለአምስት ሳምንታት ካስተማረ በኋላ በድህረትምህርት ለሁለቱም ቡድኖች አንድ አይነት ፈተና ከሰጡ በኋላ በተገኘው ውጤት በተራክቧዊ ዘዴ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል የተማሩት ተማሪዎች ውጤታቸው የተሻሻለ መሆኑን አመላክተዋል፡፡ ይሁንና የየኔሰው ጥናት ምንም እንኳን በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ላይ ቢያተኩርም ተራክቧዊ የማስተማሪያ ዘዴ አዋጭነት ላይ ያተከረ በመሆኑ የደረሰበት የጥናት ውጤት ከዚህ ጥናት ውጤት ጋር አይመሳሰልም፡፡

በተጨማሪም በስታቲስቲካዊ መረጃው መሰረት፣ የፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ (Pearson Correlation coefficient) ተሰልቶ (P = 0.204, α = 0.05) ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁ መሰረት ድህረ-ትምህርት የሙከራ ቡድኑ አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት (r = 0 .204, P = .050፣ በባለ ሁለት ጫፍ ጉልህነት ደረጃ አዎንታዊ የፍላጎትና አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት ግንኙነት መኖሩን አመልክቷል፡፡ ይህም በተጠኚዎቹ የአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤትና በፍላጎት የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ አማካይ ውጤት መካከል በስታቲስተካዊ መገመቻ ጉልህ እንዲሁም ቀጥተኛ አዎንታዊ ተዛምዶ መኖሩን ያሳያል፡፡ በዚሁ መሰረት የኦሮምኛ ቋንቋ አፈ-ፈት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል ያላቸው ፍላጎት በውጤታቸው ላይ ያለውን ተጽዕኖ ለሚጠይቀው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ ጠንካራ አዎንታዊ ተዛምዶ መኖሩ አንዱ የጥናቱ ግኝት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

Hidi and Renninger, 2006) እንደገለጹት፣ የመማር ፍላጎት ልዩ የሆነ መነቃቃት ላይ የሚመሰረት ተላውጦ ሲሆን ተማሪዎች የሚወዱት ወይም የሚመርጡት የመማሪያ ይዘትና ግብአትን ከተወሰነ የትምህርት ግብ፣ ተግባርና ልምምድ ጋር አሰናኝቶ ለተማሪዎቹ ስነልቦናዊ ዝግጅት በሚመጥን ቅንጅት ማቅረብን የሚጠይቅ አሰራር ነው (Hidi and Renninger, 2006)፡፡ የዚህ ጥናት ውጤትም ያመለከተው ፍላጎት ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ በተገቢ መንገድ ከተተገበረ የተማሪዎችን የመማር መነቃቃት በማጎልበት ውጤታማ ለማድረግ ባለው ጠቀሜታ ነው፡፡

ሁለተኛው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ የኦሮምኛ ቋንቋ አፌ-ፊት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፍላጎት ለማሻሻል በሚረዱ ብልሃቶች ትግበራ ያላቸው ምላሽ ምን ይመስላል? የሚል ሲሆን የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በፍላጎት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ ላይ ያላቸው ፍላጎት ቅድመ እና ድህረ-ትምህርት የጽሑፍ መጠይቅ አጠቃላይና አማካይ ውጤት የገላጭ ስታትስቲክስ ንጽጽር (ሰንጠረዥ 8 እና 10) ውጤት ተመርኩዞ ለመግለጽ እንደሚቻለው፣ ፍላጎት ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ በሙከራው ቡድን የፍላጎት ተላውጦዎች ሁሉ ወጥ በሆነ መንገድ አዎንታዊ ምላሽ የተገኘ መሆኑን የትንተናው ውጤት አመላክቷል፡፡ የሙከራው ቡድን ተጠኚዎች በድህረ-ትምህርት ለስነዘዴው ያላቸው ፍላጎት፣ የማንበብ ፍላጎት እና የማንበብ ችሎታ በቅድመ-ትምህርት ካሳዩት የፍላጎት መለኪያ አማካይ ውጤት ጉልህ ለውጥ ማሳየታቸውን ፍተሻው አረጋግጧል፡፡

የዚህ ጥናት ውጤት ክፍሌ (2002 ዓ.ም) እና አለምነሽ (2001 ዓ.ም) አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በመማር ተነሳሽነትና በውጤት መካከል ያለው ተዛምዶ ጥናት ውጤቶች ጋር በከፊል ይመሳሰላል፡፡ ይህ ጥናት በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት፣ በመማር ፍላጎትና በውጤት ተዛምዶ ላይ ስላተኮረና የጽሑፍ መጠይቅን እንደአንድ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ስለተጠቀመ ከሁለቱ ጥናቶች ጋር ይመሳሰላል፡፡ ይሁን እንጂ ጥናቱ የተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ለማግኘት ለዚሁ ተብሎ የተዘጋጀ ፈተናን በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት በመጠቀሙ፣ በጥናቱ ተሳታፊዎች አፍ መፍቻ ቋንቋ፣ የክፍል ደረጃና መገኛ አካባቢ፣ ጥናቱ በተካሄደበት ጊዜ፣ በጽሑፍ መጠይቁ ጥያቄዎች ዓይነት፣ ይዘትና ወቅታዊነት፣ በጥናቱ ተላውጦዎች፣ እንዲሁም በአቀራረቡም ከሁለቱ ጥናቶች ይለያል፡፡ ሁለቱም ተነሳሽነትን በጽሑፍ መጠይቅ የለኩ ሲሆን፣ የተሳታፊዎችን የአማርኛ ቋንቋ ችሎታ ለመለካት ግን ፈተና በራሳቸው አላዘጋጁም፤ የመደበኛውን ትምህርት የዓመት አጋማሽ ፈተና ውጤት ከሮስተር በመመዝገብ ነው መረጃ የወሰዱት፤ ይህም የመረጃውን ትክክለኛነትና አስተማማኝነት ጥያቄ ውስጥ ያስገበዋል፡፡ ከዚህም ሌላ በዓለምነሽ ጥናት ውስጣዊና ውጫዊ የተነሳሽነት ዓይነቶች ብቻ በመጠይቁ የተካተቱ ሲሆን፣ በክፍሌ እነዚህን ጨምሮ ውህዳዊና ጥቅማዊ የተነሳሽነት ዓይነቶች ተካተዋል፡፡ በተጨማሪም በዓለምነሽ ጥናት ፆታ ጣልቃገብ ተላውጦ ሲሆን በክፍሌ ግን አይደለም፡፡ የክፍል ደረጃ በሁለቱም ጥናቶች በጣልቃገብ ተላውጦነት አልተካተተም፡፡ እንዲሁም በዓለምነሽ ጥናት የጽሑፍ መጠይቁ ጥያቄዎች አብዛኞቹ ተነሳሽነትን ሳይሆን የመማር

ብልሀትን የሚመለከቱ በመሆናቸው የይዘት ትክክለኛነት ይጎድላቸዋል፡፡ በክፍሌ ጥናት ግን ሁሉም ጥያቄዎች ተነሳሽነት ላይ ያተኩሩ ቢሆኑም ብዙዎቹ ከተዘጋጁና በጥናት ከተፈተሹ ረዥም ዘመን ያስቆጠሩና ማሻሻያም ያልተደረገባቸው በመሆናቸው ወቅታዊነት ይጎድላቸዋል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# የጥናቱ ማጠቃለያና የመፍትሄ ሐሳቦች ጥቆማ

## 5.1 የጥናቱ ማጠቃለያ

ይህ ጥናት ያተኮረው በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዲምቱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ለመማር ያላቸው ፍላጎትና የውጤት ተዛምዶ ላይ ነው፡፡ ጥናቱን በተገቢው መስመር ለማራመድ ሁለት የምርምር መሰረታዊ ጥያቄዎች ቀርበው በተለያዩ መረጃዎች ትንተና በመደገፍ በቂ ምላሽ አግኝተዋል፡፡ ጥናቱ ያነሳቸው መሰረታዊ ጥያቄዎች የሚከተሉት ነበሩ፡፡

- የኦሮምኛ ቋንቋ አፈ-ፈት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል ያላቸው ፍላጎት በውጤታቸው ላይ ተጽዕኖው ምን ይመስላል?
- የኦሮምኛ ቋንቋ አፈ-ፈት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፍላጎት ለማሻሻል በሚረዱ ብልሃቶች ትግበራ ያላቸው ምላሽ ምን ይመስላል?

በምዕራፍ አራት ከተተነተኑት መጠናዊ መረጃዎችና በትንተናው ከተደረሰባቸው ውጤቶች በመነሳት ይህ ጥናት ከሚከተለው ማጠቃለያ ላይ ለመድረስ ችሏል፡፡ ፍላጎት ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ ልዩ ልዩ ብልሃቶች በአግባቡ በሚተገበሩበት አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ በፍላጎት-ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ ልዩ ልዩ ተግባራትና አነቃቂ ክንዋኔዎች በመታገዙ የተነሳ የተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ፍላጎት ጉልህ መሻሻል ማሳየቱ ተረጋግጧል፡፡ ፍላጎት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ አንብቦ የመረዳት ችሎታ እንዲያዳብሩና

አንብቦ የመረዳት ውጤታቸው ጉልህ እድገት እንዲያሳይ ጠቀሜታ እንዳለው የዚህ ተግባራዊ ጥናት ግኝት አመላክቷል፡፡ በዚሁ መሰረት የኦሮምኛ ቋንቋ አፌ-ፌት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል ያላቸው ፍላጎት ከአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤታቸው ጠንካራ አዎንታዊ ተዛምዶ ያለው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

በሌላም በኩል የሙከራው ቡድን ተጠኚዎች በድህረ-ትምህርት ለፍላጎት ተኮር ስነዘዴ ያላቸው ፍላጎት፣ የማንበብ ፍላጎት እና የማንበብ ችሎታ በቅድመ-ትምህርት ካስመዘገቡት የፍላጎት መለኪያ የጽሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት ጉልህ መሻሻል ማሳየታቸውን ፍተሻው አረጋግጧል፡፡ ይህም ፍላጎት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት መነሳሳትን ለማሻሻል ጉልህ አዎንታዊ ተጽእኖ ያለው መሆኑን አመላክቷል፡፡

የፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ (Pearson Correlation coefficient) ተሰልቶ (P = 0.204, α = 0.05) ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም በተጠኚዎቹ የአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤትና በፍላጎት የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ አማካይ ውጤት መካከል በስታቲስተካዊ መገመቻ ጉልህ እንዲሁም ቀጥተኛ አዎንታዊ ተዛምዶ መኖሩን ያሳያል፡፡ በዚሁ መሰረት የኦሮምኛ ቋንቋ አፌ-ፌት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል ያላቸው ፍላጎት በውጤታቸው ላይ ያለውን ተጽዕኖ ለሚጠይቀው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ ጠንካራ አዎንታዊ ተዛምዶ መኖሩ አንዱ የጥናቱ ግኝት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

## 5.2 የመፍትሄ ሃሳቦች ጥቆማ

የተገኙ ውጤቶችን መነሻ በማድረግና በክለሳ ድርሳናት ፍተሻ በመደገፍ አጥኚዋ የሚከተሉትን የመፍትሄ ሐሳቦች ለመጠቆም ትሻለች፡፡

1. በሰፊው እንደሚታወቀው መማሪያ ክፍል የቋንቋ ልምምዶችን ለማካሄድና ለመማር ዋንኛው ስፍራ ነው፡፡ በተለይ የመማሪያ ክፍል ውስጥ የቋንቋ ልምምዶች ከገሃዱ አለም ተግባቦታዊ ፍላጎቶቻቸው ጋር በተገናዘበ መንገድ የሚቀርቡ ከሆነ የተማሪዎቹ ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ፍላጎትና ውጤታማ የመሆን ተነሳሽነት እንደሚሻሻል ይህ ተግባራዊ ጥናት ያረጋገጠው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም የቋንቋ መምህራን ከልማዳዊው ማስተማሪያ ዘዴ ተላቀው ልዩ ልዩ አውዳዊ ተግባራትና ክንውኖችን ለተማሪዎቹ ፍላጎት፣ የትምህርት ደረጃና እድሜ በሚመጥን መልኩ ማቅረብ፣ አገላለጾችንና ድርጊቶችን በድርጊት ጭምር

እንዲለማመዱ ማድረግና ተማሪዎችን ማነቃቃት ቢችሉ ሁለተኛ ቋንቋን በፍላጎትና ተነሳሽነት ለመማር እንደሚችሉ ለመጠቆም እወዳለሁ፡፡

2. በICDR (2009) እንደቀረበው፣ በችግር ላይ ተመስርቶ ክፍተትን ለመሙላት የሚቀርብ ብሎም ውጤቶችንና የመፍትሄ አማራጮችን ለመጠቆም የሚረዳ ክንውን ጠቃሚ የተማሪዎች የመማር ችግሮችን ማቃለያ ፍላጎት ተኮር ዘዴ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ውጤቱ ወይም መፍትሄው የችግሩን ክፍተት መሙላትን ታሳቢ አድርጎ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ በዚህ የተነሳ ይህ ሂደት ‹‹ዘዴ--ውጤት ትንተና›› (means-ends analysis) ተብሎ ይጠራል፡፡ በዚህም የተነሳ ችግር ፈቺ ፍላጎት ተኮር ብልሃት ተማሪዎቹ በሚገኙበት የክፍል ደረጃ ባላቸው የእውቀት ክፍተት ላይ ተመስርተው የሚፈለገውን አዲስ እውቀትና ክህሎት ለመጨበጥ እንዲችሉ ያግዛቸዋል፡፡ በመሆኑም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተማሪዎቹ በቋንቋ መማሪያ አውዱ ላሉባቸው ጉልህ የክህሎት ችግሮች ቅድሚያ በመስጠት ክፍተቶቻቸውን ለመሙላት ቢጥሩ ተማሪዎቹ ጉልህ ችግሮቻቸው በመቃለላቸው መጠን ሌሎች ችግሮችን እያቃለሉ ለመማር ልምድ ያገኛሉ፡፡ ሁለተኛ ቋንቋውን የመማር ፍላጎት፣ ተነሳሽነት፣ በራስ መተማመን ያዳብራሉ፡፡

3. በቋንቋ መማሪያ አውዱ የሚደረስባቸው እውነተኛ /ተጨባጭ/ የቋንቋ መማር ግቦችን ማስቀመጥና እነዚህን ትምህርታዊ ግቦች በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ለመጨበጥ የሚደረግ ትምህርታዊ እንቅስቃሴ በተማሪዎች አስተሳሰብ ውስጥ የመማር ፍላጎትን ለማስረጽ ቁልፍ ጠቀሜታ አለው፡፡ በመሆኑም የቋንቋ መምህራን በየደረጃው ተማሪዎቹ የአጭርና የመካከለኛ ጊዜ የቋንቋ ትምህርቶችን በአሳታፊ መንገድ ተወያይተው እንዲያስቀምጡና እነዚህን ግቦች መጨበጥ አለመጨበጣቸውን በግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ ሰርክ እየገመገሙ እንዲማሩ ቢያደርጉ በሁለተኛ ቋንቋ መማር የተሻለ ውጤታማ ሊሆኑ እንደሚችሉ ለመጠቆም እወዳለሁ፡፡

4. በመደጋገፍ መማር ተማሪዎች ትንንሽ ቡድኖችን መስርተው እርስ በርስ በመማማር የራሳቸውን መረዳት ከፍ ለማድረግም ሆነ ሌሎች እንዲረዱ ለማገዝ አብረው የሚሰሩበት አውድ ነው፡፡ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ድግግፋዊ መማር በአዎንታዊ አቻዊ ግንኙነትና እርስ በእርስ መደጋገፍ ከፍ ወዳለ የመማማር ውጤታማነት ለመድረስ የሚያግዝ ብልሃት ነው፡፡ በመሆኑም የቋንቋ መምህራን በመደጋገፍ የመማር ስልቶችን ቢያጠናክሩ

ተማሪዎቻቸው የተሻለ ተግባቦታዊ ፍላጎት እና ችሎታ ሊያዳብሩ እንደሚችሉ ለመጠቆም እወዳለሁ፡፡

# ዋቢዎች


አለምነሽ የኔነህ፡፡ (2001 ዓ.ም)፡፡ አዊኛ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን እንደሁለተኛ ቋንቋ ሲማሩ ያላቸው ተነሳሽነትና የትምህርት ውጤት ተዛምዶ፡፡ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ፣ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ባህር ዳር፡፡

የኔሰው ደሴ፡፡ (1990)፡፡ በሁለተኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ክሂላቸውን ለማዳበር ተራክቧዊ የንባብ ክሂልን ማስተማሪያ ሞዴል በክፍል ውስጥ ተጠቅሞ ማስተማር ያለው አስተዋጽኦ፡፡ በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን በማስተማር ዘዴ ለማስተርስ ኦፍ አርትስ ዲግሪ የቀረበ ጥናት፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድህረ-ምረቃ ትምህርት ቤት፡፡

ዘሪቱ አስፋው እና ማረው ዓለሙ፡፡ (2009)፡፡ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የመማር ተነሳሽነትና የውጤት ተዛምዶ፤ በጋሞኛ ቋንቋ አፍፈት ተማሪዎች፡፡

Barron, K. E., & Harackiewicz, ]. M. (2000*). Achievement goals and optimal motivation: A multiple goals approach*. In C. Sansone & ]. M. Harackiewicz (Eds.), Intrinsic and extrinsic motivation-. The search for optimal motivation and performance (pp. 231-256). New York: Academic Press.

Bainbridge, C. (2014). *High Achiever: Gifted Children Categories*. http://giftedkids.about.com/od/glos sary/g/High-Achiever.htm

Beck, I. L., & McKeown, M. G. (2001). Inviting students into the pursuit of meaning. In K. A. Renninger, & S. E. Wade (Guest Eds.), Student interest and engagement. *Educational Psychology Review*, 13 (3), pp. 225-242.

Brown, H.D. (2000). Principles of Language Learning and Teaching. (4th ed.). USA: Longman Inc.

Eidswick, J. (2010). Interest and prior knowledge in second language reading comprehension. *JALT Journal*, 32 (2), 149—168.

Ellis, R. (1997). *Sceond Language Acquisition.* Oxford: Oxford University Press.

Fine, D.(2003). A sense of learning style. *Principal Leadership: High School Edition, 4*(2), 55-6.

Gardner, C. (1985). Social psychology and second Language, The role of Attitude and motivation: London Arnold.

Gardner,R.C.(2001).*Integrative Motivation and Second Language Acquisition.* In Z. Dorneyei and R. Schmidt (Eds). *Motivation and Second Language Learning.* Hondulu: University of awai.

Gu, Yueguo. (2010). *English language Teaching Methodology.* Beijing: Foreign Language Teaching and Research Press.

Guo, Z. F., and Zhang, D. Q. (2012). The main reason of learning weariness in primary school students: the overburden of study load. *Res. Basic Edu.* 18, 3—5.

Gutherie, I. T., & Cox, K. E. (2011). Classroom conditions for motivation and engagement in reading. In K. A. Renninger, & S. E. Wade (Guest Eds.), Student interest and engagement. *Educational Psychology Review*, 13 (3), pp. 283-3.

Hamilin, E. (1996). Oxford advanced Learners' Dicticreny (5th ed). New York University press.

Harmer, J. (1991). *The Practice of English Language Teaching.* London: Longman.

Hidi, S. (2010). *An interest researcher's perspective: The effects of extrinsic and intrinsic factors on motivation*. In C. Sansone, & J. M. Harackiewicz (Eds.), \ntrinsic and extrinsic motivation-. The search for optimal motivation and performance (pp. 309-339). New York: Academic Press.

Hidi, S. (2013). Interest, reading, and learning: Theoretical and practical considerations. In K. A. Renninger, & S. E. Wade (Guest Eds.), Student interest and engagement. *Educational Psychology Review*, 13 (3), pp. 191-210.

Hidi, S., & Harackiewicz, J. (2008). Motivating the academically unmotivated: A critical issue for the 21st century. Review of Educational Research, 70, 151—179.

Hidi, S., & Renninger, K. (2006). The four-phase model of interest development. Educational Psychologist, 41(2), 111—127.

Hofer, M. (2010), Adolescents' Development of Individual Interests: A Product of Multiple GoalRegulation? EDUCATIONAL PSYCHOLOGIST, 45(3), 149—166, 2010.

Hoffmann, L. (2002). Promoting girls' interest and achievement in physics classes for beginners. Learning and Institution, 12 (4), 447-465.

Honigsfeld, A., & Schiering, M. (2004). Diverse approaches to the diversity of learning styles in teacher education. *Educational Psychology*, *24*(4), 487-8

Huang, Yuefa. (2011). *English Teaching Methodology.* Shanghai: Foreign Language Teaching and Research Press.

ICDR. (2009). Teacher Roles in the Learner-Centered Classroom. *ELT Journal*. Vol. 47,No. 1.

Jacobs, I. E., & Eccles, J. S. (2010). *Parents, task values, and real-life achievement-related choices.* In C. Sansone, & ]. M. Harackiewicz (Eds.),

Intrinsic and extrinsic motivation-. The search for optimal motivation and performance (pp. 405-439). New York: Academic Press.

Justina, Reamen. (2015). Motivational Factors that Enhance Students Learning/Achievement, *Journal of Teaching and Education*, 04(02):323- 332 (2015),

Kolb, A., & Kolb, D. (2009). The learning way: Meta-cognitive aspects of experiential learning. *Simulation & Gaming, 40*(3), 297-327. Retrieved from Academic Search Complete database.

Krapp, A. (2002). An educational-psychological theory of interest and its relation to self-determination theory. In: E. Deci & R. Ryan (Eds), The handbook of self-determination research (pp. 405-427). Rochester: University of Rochester Press.

Linnenbrink, E.A., & Pintrich, P.R. (2008). *Multiple pathways to learning and achievement: The role of goal orientation in fostering adaptive motivation, affect, and cognition.* In C. Sansone, & I. M. Harackiewicz (Eds.), Intrinsic and extrinsic motivation-. The search for optimal motivation and performance (pp. 196-230). New York: Academic Press.

McCarthy, John. (2014). Learner Interest Matters: Strategies for Empowering Student Choice, https://www.edutopia.org.

Mitchell, M. (2003). Situational interest: Its multifaceted structure in the secondary school mathematics classroom, *journal of Educational Psychology*, 85(3), 424-436.

McClanaghan, M. E. (2008). A strategy for helping students learn how to learn. *Education, 120*(3), 479-486. Retrieved from EBSCO host database.

MOE (2004). *Education and Training policy, Addis Ababa*; MOE/NOE (National Organization for Examinations) Dec 2004, Ethiopian Second National Learning assessments of grade 4 students and grade 8 students. ESDP I to IV, 2000-2011, MOE, Addis Ababa.

Murphy, P K., & Alexander, P A. (2000). A motivated exploration of motivation terminology. *Contemporary Educational Psychology*, 25, 3

National Research Council. (2003). Samples of Questionnaires Used to Evaluate Undergraduate Student Learning. *Evaluating and Improving Undergraduate Teaching in Science, Technology, Engineering, and Mathematics*. Washington, DC: The National Academies Press.

Omrod, J. E. (2008). *Educational psychology: developing learners*. Sixth Edition. Upper Saddle River, New Jersey: Pearson Education.

Pashler, H., McDaniel, M., Rohrer, D., & Bjork, R. (2008). Learning styles: Concepts and evidence.*Psychological Science in the Public Interest*, 9(3).

Reid, J.M.(1995). *Learning Styles in the ESL/EFL Classroom*. Boston: Heinle & Heinle Publishers.

Renninger, K A. Hidi, S. and Krapp A. (2012). *The role of interest in learning and development*; Hillsdale, NJ: Eribaum.

Schiefele, U. (2008). *The role of interest in motivation and learning*. In J. M. Collis & S. Messick (Eds.), Intelligence and personality: Bridging the gap in theory and measurement (pp. 163-194). Mahwah, NJ: Erlbaum.

Schmidt, Richard, Boraje, Deena and Kassbgy, Omneya. (1996). *Foreign Language Motivation*: Internal Structure and External Connections. In Rebecca Oxford (Ed.), Honolulu: University of Hawai.

Stern, H. H. (1994). *Fundamental Concepta of Language Teaching.* Hong Kong: Oxford University Press.

Subramaniam P. R. (2009). *Motivational Effects of Interest on Student Engagement and Learning in Physical Education*: New York, A Review.

Tomlinson, C. A. (2005). Quality curriculum and instruction for highly able students. *Theory into Practice*, *44*(2), 160-166.

Tomlinson, C. A. (2007). Learning to love assessment. *Educational Leadership*, *65*(4), 8-13. Retrieved from Academic Search Complete database.

Walkington, C. & Sherman, M. (2013). *Using adaptive learning technologies to personalize instruction: The impact of interest-based scenarios on performance in algebra*. Proceedings of the 10th International Conference of the Learning Sciences, 80—87.

Wang Y. (2003). Assessment of Learner Satisfaction with Asynchronous Electronic Learning Systems. Information & Management. 41, 75-86.

Willemse M, Lunenberg M, & Korthagen F. (2005). Values in education: a challenge for teacher educators.

Winger, T. (2005). Grading to communicate. *Educational Leadership*, *63*(3), 61-65. Retrieved from Academic Search Complete database.

Wilson, S. (1971). Interest and Discipline in Education. London: Routledge and Keganpaul.

Wright, T. (2016). *Roles of Teachers and Learners.* Oxford: Oxford University Press, 2016.

# አባሪ ሀ

## ጅማ ዩኒቨርሲቲ ሶሻል ሳይንስና ሒዩማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

## ለተማሪዎች የቀረበ መጠይቅ

ውድ ተማሪዎች!

ይህ መጠይቅ የተዘጋጀው በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን በጢሮ አፈታ ወረዳ በዲምቱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ለመማር ያላቸው ፍላጎትና የውጤት ተዛምዶ ለመፈተሽ ነው፡፡ መጠይቁ ባለ አምስት የመልስ አማራጮች አሉት፡፡ ሙሉ በሙሉ እስማማለሁ፣ እስማማለሁ፣ አቋም የለኝም፣ አልስማማም እና ፈጽሞ አልስማማም ከሚሉ የመልስ አማራጮች መካከል ለአንተ/ቺ/ ትክክል የሆነውን በመምረጥ በየጥያቄዎቹ አንጻር በየሳጥኑ

ውስጥ የ‹‹X›› ምልክት በማድረግ መጠይቁን ሞልታችሁ ጨርሱ፡፡ በቅድሚያ ይህን መጠይቅ ለመሙላት ትብብራችሁን ስላሳያችሁኝ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

**መግለጫ፡-**

ሙሉ በሙሉ እስማማለሁ (5)

እስማማለሁ (4)

አቋም የለኝም (3)

አልስማማም (2)

ፈጽሞ አልስማማም (1)

የፅሁፍ መጠይቁ የተሞላበት ወቅት፡-

ሀ) ቅድመ-ትምህርት -------            ለ) ድህረ-ትምህርት------

| ተ.ቁ | ጥያቄ | የምላሽ አሰጣጥ አማራጮች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | አቋም የለኝም | አልስማማም | ፈጽሞ አልስማማም |
| | **አጠቃላይ ፍላጎት** | | | | | |
| 1 | አማርኛ ቋንቋ መማር ለእኔ አስደሳች ክንዋኔ ነው፡፡ | | | | | |
| 2 | አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ መማር የተግባቦት እና የስራ እድል እንደሚያሰፋልኝ አውቃለሁ፡፡ | | | | | |
| 3 | በትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ ችሎታዬን ለማሳደግ ምቹ እድል እንዳለኝ አምናለሁ፡፡ | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 4 | አማርኛ ቋንቋን መማር እንደጨዋታ ያስደስተኛል፡፡ | | | | | |
| 5 | አማርኛ ቋንቋን መማር ለኔ አዲስ ነገር እንደማወቅ የምደሰትበት ክንዋኔ ነው፡፡ | | | | | |
| 6 | አማርኛ ቋንቋን መማር ከሰዎች ጋር የመተዋወቅ እድሌን ያሰፋልኛል፡፡ | | | | | |
| 7 | አማርኛ ቋንቋን መማር በአካባቢዬ ያለውን አለም ለማወቅ ያስችለኛል፡፡ | | | | | |
| 8 | አማርኛ ቋንቋን መማር በቋንቋው የሚቀርቡ መረጃዎችን ለመገንዘብ ይረዳኛል፡፡ | | | | | |
| 9 | አማርኛ ቋንቋን በመማር የሁለተኛ ቋንቋ ችሎታን እንደማዳብር እረዳለሁ፡፡ | | | | | |
| 10 | አማርኛ ቋንቋን መማር በቋንቋው ሀሳቤን ለመግለጽ እንድችል ይረዳኛል፡፡ | | | | | |
| 11 | አማርኛ ቋንቋን መማር ነገሮችንና ክስተቶችን የመረዳት እድሌን ያሰፋልኛል፡፡ | | | | | |
| 12 | አማርኛ ቋንቋን መማር የቋንቋ ክህሎቶቼን ያሳድግልኛል፡፡ | | | | | |
| 13 | በአማርኛ ቋንቋ መማር አዳዲስ ነገሮችን እንዳውቅ ረድቶኛል፡፡ | | | | | |
| 14 | በአማርኛ ቋንቋ ከሚቀርቡልን ይዘቶች ያልገቡኝን ጉዳዮች በመጠየቅ ለመረዳት ፍላጎት አለኝ፡፡ | | | | | |
| 15 | በአማርኛ ቋንቋ ክፍለጊዜ ከክፍል ጓደኞቼ ጋር በመተባበር እሰራለሁ፡፡ | | | | | |
| 16 | በመማሪያ ክፍል ውስጥ በአማርኛ ቋንቋ ክፍለጊዜ የሚሰጡኝን ተግባራት በፍላጎትና ተነሳሽነት አከናውናለሁ፡፡ | | | | | |
| 17 | እንደ እኔ እምነት አማርኛ ቋንቋን በሚገባ ለማወቅ ጠንክሬ መማር እንዳለብኝ አስባለሁ፡፡ | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 18 | አማርኛ ቋንቋን መማር ከሌሎች ሰዎች ጋር ተፎካካሪ የመሆን ብቃት | | | | | |
| 19 | አማርኛ ቋንቋን ልክ እንደ መጀመሪያ ቋንቋዬ ለማቀላጠፍ ፍላጎት አለኝ፡፡ | | | | | |
| 20 | ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያለኝ አጠቃላይ አመለካከት አዎንታዊ ነው፡፡ | | | | | |
| | **የማንበብ ፍላጎት** | | | | | |
| 21 | በአማርኛ ቋንቋ ስለ ማንበብ ሳስብ ሁሌ ከፍ ያለ የጥንካሬ ስሜት ይሰማኛል፡፡ | | | | | |
| 22 | ቤት በምሆንበት ወቅት ሁሌ በአማርኛ ቋንቋ ብዙ አነባለሁ፡፡ | | | | | |
| 23 | ብዙ የማነባቸው የአማርኛ ቋንቋ መጻህፍት እንዲኖሩኝ ፍላጎት አለኝ፡፡ | | | | | |
| 24 | ካነበብኳቸው ረጅም ጊዜ ቢሆናቸውም እንኳን በቀላሉ የማስታውሳቸው ጉዳዮች አሉ፡፡ | | | | | |
| 25 | እኔና ጓደኞቼ ባነበብናቸው መጻህፍት ዙሪያ ውይይት እናካሂዳለን፡፡ | | | | | |
| 26 | ሰዎች ከሚነግሩኝ ይልቅ ራሴ ያነበብኳቸውን ጉዳዮች በበለጠ አስታውሳለሁ፡፡ | | | | | |
| 27 | አብዛኛውን ትርፍ ጊዜዬን በአማርኛ ቋንቋ በማንበብ ማሳለፍ እወዳለሁ፡፡ | | | | | |
| 28 | በአማርኛ ቋንቋ የተጻፉ መጻህፍት በስጦታ መቀበል ያስደስተኛል፡፡ | | | | | |
| 29 | በአማርኛ ቋንቋ ንባብ እወዳለሁ፤ ምክንያቱም የተግባቦት ችሎታዬን አዳብሮልኛል፡፡ | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 30 | ለእኔ ንባብ ማለት የእውቀት ምንጭ ነው፡፡ | | | | | |
| 31 | ለእኔ ንባብ ማለት የመዝናኛ ምንጭ ነው፡፡ | | | | | |
| 32 | ለእኔ ንባብ ማለት የመረጃ ምንጭ ነው፡፡ | | | | | |
| | **የማንበብ ችሎታ** | | | | | |
| | በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ችሎታዬ በጥሩ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ | | | | | |
| 33 | አንድን ለንባብ የቀረበ ጽሁፍ በፍጥነት፣ በትክክልና በተገቢው አገላለጽ የማንበብ ብቃት አለኝ ብዬ | | | | | |
| 34 | ሳነብ የቀደመ እውቀቴን ተጠቅሜ ምንባቡን ለመረዳት ጥረት አደርጋለሁ፡፡ | | | | | |
| 35 | ሳነብ ስለጽሁፉ መልእክት በሃሳቤ ምስል በመፍጠር ለመረዳት | | | | | |
| 36 | በክፍል ውስጥ በንባብ ትምህርት ወቅት በንቃት እሳተፋለሁ፡፡ | | | | | |
| 37 | በማንበብ ሂደት ዘዴ በተሞላበት ሁኔታ አጠቃላዩን የምንባቡን መልእክት ለመገመት እሞክራለሁ፡፡ | | | | | |
| 38 | በማንበብ ክሂል ያለኝ ዳራ እውቀት አበረታችና ለወደፊቱ የማንበብ ህይወቴ ጥሩ መሰረት እንደሆነ | | | | | |
| 39 | ስላነበብኩት ጉዳይ የተረዳሁትን በራስ በመተማመን መንፈስ እገልጻለሁ፡፡ | | | | | |
| 40 | አንብቦ በመረዳት ፈተና የማገኘው ውጤት አበረታች ነው፡፡ | | | | | |

*(ምንጭ፡- ከNational Research Council (2003) እና Schiefele (2008) ለዚህ ጥናት እንዲስማማ በመጠኑ ተሻሽሎ የተወሰደ፡፡)*

# አባሪ ለ

## አንብቦ የመረዳት ፈተና

*(አንብቦ የመረዳት ፈተናው በቅድመ እና ድህረ-ትምህርት አንድ አይነት ፈተናን ደግሞ በመፈተን የተካሄደ ነው፡፡)*

## (ምንባብ አንድ)

**የተፈታኙ መለያ ኮድ፡- -------------**

**የተፈታኙ ምድብ፡- ሀ) ቁጥጥር ---------- ለ) ሙከራ ------------**

መመሪያ:- ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ በጥሞና በማንበብ ከሥር ለቀረቡላችሁ ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል በምንባቡ መሰረት ትክክል የሆነውን መልስ በመምረጥ መልሱ፡፡

ቅርስ ተፈጥሮ የለገሰንን እና የሰው ልጅ በኖረበት ዘመን ያከማቻቸውን የፈጠራ ውጤቶች ሁሉ የሚያካትት በመሆኑ ቁጥሩ እና አይነቱ እጅግ ብዙ ነው፡፡ ቅርስን በአራት አይነት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ እነሱም (1) ባህላዊ እና ተፈጥሯዊ ቅርስ፣ (2) የአለም ቅርስ እና ብሔራዊ ቅርስ፣ (3) ተንቀሳቃሽ እና የማይንቀሳቀስ ቅርስ እና (4) ተጨባጭ እና ተጨባጭ ያልሆነ ቅርስ ናቸው፡፡

ቅርስ ሲባል አብዛኞቻችን የምናስበው ከባህል ጋር በተገናዘበ መልኩ ብቻ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ቅርስ የተመረጡ የተፈጥሮ ስጦታዎችንና የሰው ልጅን የፈጠራ ውጤቶችን ወይም የሁለቱንም ጥምረት የሚያካትት ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ባህላዊና ተፈጥሯዊ ቅርስ በመባል በሁለት ይከፈላል፡፡ የባህል ቅርስ የተመረጡ የሰው ልጅ የፈጠራ ውጤቶችን ማለትም ሀውልቶችን፣ ህንፃዎችን፣ ዋሻዎችን፣ በድንጋይ እና በብራና… ወዘተ. በመሳሰለት ላይ የተጻፉ ወይም የተቀረጹ ጽሁፎችን፣ ቅርጻ ቅርጾችን፣ አልባሳትን፣ እምነቶችን፣ ወጎችን፣ ስርአቶችን… ወዘተ ሁሉ ያካትታል፡፡ የተፈጥሮ ቅርስ ደግሞ በላቀ ጠቀሜታቸው የተመረጡ ማራኪ እና ውብ የሆኑ ደኖችን፣ ሐይቆችን፣ ዋሻዎችን፣ ብሔራዊ ፓርኮችን፣ የእንስሳት መጠለያዎችን፣ በአጠቃላይ ህይወት ያላቸውን እና የሌላቸውን ፍጡሮች እና እነርሱም የሚገኙባቸውን ቦታዎች ሁሉ ያካትታል፡፡

ቅርስ ካለው ጠቀሜታ አንጻር የአለም ቅርስ እና ብሔራዊ ቅርስ በሚሉ ሁለት ክፍሎች ይከፈላል፡፡ አንድ ቅርስ (የባህል፣ የተፈጥሮ እና ሁለቱንም በጣምራ ያካተተ ቅርስ) የተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ የሳይንስ እና የባህል ድርጅት ባወጣው መመዘኛ መሰረት በውስጡ የላቀ አለም አቀፍ እሴት ካለው፣ የአለም ህዝቦች ሊያደንቁት፣ ሊማሩበት እና ሊጠቀሙበት የሚችሉበት ከሆነ በአለም ቅርስነት ተመዝግቦ የአለም ቅርስ በመባል ይታወቃል፡፡ ብሔራዊ ቅርስን በተመለከተ ደግሞ እያንዳንዱ መንግስት ባወጣው መመዘኛ መሰረት ማንኛውም ብሔራዊ እሴት ያለው ቅርስ (የባህል፣ የተፈጥሮ እና ሁለቱንም በጣምራ ያካተተ ቅርስ) ህዝቦች ሊያደንቁት፣ ሊማሩበት እና ሊጠቀሙበት የሚችሉበት ከሆነ በብሔራዊ ቅርስነት ተመዝግቦ ብሔራዊ ቅርስ በመባል ይታወቃል፡፡ በዩኔስኮ የውሳኔ ሰነዶ መሰረት የአለም የባህል ቅርስ የሚባሉት ሐውልቶች፣ ሕንጻዎች፣ ከታሪክ፣ ከስነ ጥበብ

እና ከሳይንስ አንጻር የላቀ አለም አቀፍ እሴት ያላቸው ቦታዎች፣ የተፈጥሮ እና የሰው ስራዎችን በአንድ ላይ ያጣመሩ የቁፋሮ ቦታዎችንም ያካትታል፡፡

በሌላ በኩል ከአይነቱ፣ ከተፈጥሮው እና ከመጠኑ አንጻር ቅርስ ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀስ ተብል በሁለት ይከፈላል፡፡ ተንቀሳቃሽ የሚባለው በቀላሉ ከቦታ ወደቦታ ሊንቀሳቀስ ወይም ሊወሰድ የሚችል የቅርስ አይነት ነው፡፡ ለምሳሌ በቅርስነት የተመዘገቡ በብራና ላይ የተጻፉ ጽሁፎች፣ አልባሳት በተለያዩ ቁሳቁሶች (ከእንጨት፣ ከብረት፣ ከሸክላ፣ ከድንጋይ ከወርቅ… ወዘተ) የተሰሩ እቃዎች እና ቅርፃቅርፆች መጠናቸው አነስተኛ የሆነ በቁፋሮ የተገኙ ጥንታዊ የመገልገያ እቃዎች… ወዘተ በቀላሉ ከቦታ ወደ ቦታ ሊንቀሳቀሱ ወይም ሊወሰዱ ስለሚችሉ ተንቀሳቃሽ ቅርስ በመባል ይታወቃሉ፡፡ የማይንቀሳይስ የሚባለው በቀላሉ ካለበት ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ሊንቀሳቀስ ወይም ሊወሰድ የማይችል የቅርስ አይነት ነው፡፡ ለምሳሌ የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስትያናት፣ ታሪካዊ የሐረር ከተማ ጀጎል ግንብ፣ የአል-ነጃሺ መስጊድ፣ የሰሜን ብሔራዊ ፓርክ… ወዘተ ይጠቀሳሉ፡፡ በአለም ቅርስነትም የተመዘገቡ ናቸው፡፡ አፈጣጠራቸው ከግዝፈታቸው እና ከሚገኙባቸው ቦታዎች አኳያ በቀላሉ ለማንቀሳቀስ አይቻልም፡፡

በመጨረሻም ልናየው፣ ልንዳስሰው፣ ልናሸተው… ወዘተ በአጠቃላይ በሁሉም ስሜት ህዋሳቶቻችን ልንገነዘበው የምንችለው ተንቀሳቃሽም ሆነ የማይነቀሳቀስ ቅርስ ተጨባጭ ቅርስ በመባል ይታወቃል፡፡ ለምሳሌ ሀውልቶች፣ ህንጻዎች፣ ዋሻዎች፣ መጻህፍት፣ የተለያዩ ቅርሳ ቅርሶች፣ አልባሳት… ወዘተ ተጨባጭ ቅርስ በመባል ይታወቃሉ፡፡ ልናየው፣ ልንዳስሰው፣ ልናሸተው… ወዘተ የማንችለው ነገር ግን የውስጥ ስሜታችንን የሚያረካ ቅርስ ተጨባጭ ያልሆነ ቅርስ በመባል ይታወቃል፡፡ ወጎች፣ ተረቶች፣ ስርአቶች፣ ማራኪ እይታዎች፣ ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ ስርአቶች ወዘተ ቁሶች አይደሉም፡፡ በውስጣቸው ግን መንፈሳችንን የሚያነሳሱ፣ የአእምሮ እርካታንም የሚሰጡን በርካታ እሴቶች አሉዋቸው፡፡ የሰው ልጅ በተፈጥሮው ማወቅን፣ መመራመርን፣ መፍጠርን፣ መደሰትን… ወዘተ፣ ሁሉ ይፈልጋል፡፡ ፍላጎቶች ሁሉ ግን በቁሳዊ ፍላጎቶች ብቻ ሊረኩ ከቶውንም አይቻላቸውም፡፡ ተጨባጭ ከሆኑት ወይም ከቁሳዊ ፍላጎቶቹ በተጨማሪ ተጨባጭ ወይም ቁሳዊ ያልሆኑ ፍላጎቶችም አሉት፡፡ በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱት ቁሳዊ ያልሆኑና መንፈሳችንን በማነሳሳት የአእምሮ እርካታን የሚሰጡን ነገሮች በቅርስነት ሲመዘገቡ ተጨባጭ ያልሆነ ቅርስ በመባል ይታወቃሉ፡፡ በአጠቃላይ የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ቅርሶች የሰውን ልጅ

አኗኗር፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ አስተሳሰብ፣ የህይወት ፍልስፍና፣ ወግ እና ስርአትን የሚያንፀባርቁ የዘመን አሻራዎች ናቸው፡፡

*ምንጭ፡- ባህልና ልማት በኢትዮጵያ፣ ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ (2004) ተሻሽሎ የተወሰደ*

1) በምንባቡ መሰረት ቅርስ ማለትን የማይገልጸው የቱ ነው?

   ሀ/ በእድሜ አንጋፋ ከሆነ ማንኛውም ቁስ ቅርስ ሊባል ይችላል፡፡

   ለ/ የተፈጥሮ ስጦታ እና ጠቃሚ ባህላዊ እሴቶች ቅርስ ይባላሉ፡፡

   ሐ/ ቅርስ ከእዴሜው፣ ከውበቱ፣ ከጠቀሜታው፣ ከብርቅየነቱ አንጻር ሊታይ ይችላል፡፡

   መ/ የሰው ልጅ የፈጠራ ውጤት ቅርስ ሊባል ይችላል፡፡

2) ‹‹ብርቅ›› የሚለው ቃል ትርጉም............................ማለት ነው፡፡

   ሀ/ አዲስ　　ለ/ ነባር　　ሐ/ አስገራሚ　　መ/ የሚያብለጨልጭ

3) ከሚከተሉት <u>ተጨባጭ ያልሆነ ቅርስ</u> የሚለውን ሐሳብ በትክል የሚገልጸው የቱ ነው?

   ሀ/ በሁሉም ስሜት ህዋሳቶቻችን ልንገነዘበው የምንችለው ቅርስ ነው፡፡

   ለ/ በአይን የማይታይ አእምሯዊ የሆነ ሐሳብ ነው፡፡

   ሐ/ ሀውልቶች፣ ህንጻዎች፣ ዋሻዎች፣ መጻህፍትና አልባሳትን የሚያካትት ነው፡፡

   መ/ ህይወት ያላቸውን እና የሌላቸውን ፍጡራን ይመለከታል፡፡

4) በምንባቡ መሰረት በቁፋሮ የሚገኙ ጥንታዊ የመገልገያ እቃዎች ...............ናቸው፡፡

   ሀ/ ተጨባጭ ያልሆኑ ቅርሶች　　ለ/ ተጨባጭ ቅርሶች

   ሐ/ ተፈጥሯዊ እና ተጨባጭ ቅርሶች　　መ/ የማይንቀሳቀሱ ቅርሶች

5) በምንባቡ መሰረት የአለም ቅርስ የሚባለት ምን መስፈርት ያሟሉ ናቸው?

   ሀ/ አብረቅራቂ እና ትልቅ ከሆኑ　　ለ/ በቁፋሮ ከተገኙ

   ሐ/ በቆዳ እና በድንጋይ ላይ ከተጻፉ　　መ/ በውስጣቸው ከፍተኛ እሴት ካላቸው

6) በምንባቡ መሰረት ብራና ...................... ነው፡፡

   ሀ/ ከፍተኛ ገንዘብ　　ለ/ ከቆዳ የተሰራ መጻፊያ

   ሐ/ ጠንካራ ብረት　　መ/ ደማቅ ብርሃን

7) ፀሐፊው ማስተላለፍ የፈለገው መልእክት ምንድን ነው?

   ሀ/ ቅርሶች የሐገርና የአለም ሐብት መሆናቸውን

   ለ/ የሐገራችን ቅርስ እየተመዘበረ መሆኑ

   ሐ/ ቅርሶች አይነታቸው ብዙ በመሆኑ መለየት አስቸጋሪ መሆኑን

መ/ ቅርሶች ዋጋቸው በጣም ውድ መሆኑን

8) ከሚከተሉት መካከል ቅርስ ያልሆነውን ለይ/ዪ፡፡

ሀ/ ቅርጻ ቅርጾች፣ አልባሳት፣ እምነቶች፣ ወጎችና ባህላዊ ስርአቶች

ለ/ ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ ስርአቶች

ሐ/ የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስትያናትና የአል-ነጃሺ መስጊድ

መ/ መልሱ አልተሰጠም፡፡

9) በምንባቡ መሰረት *እሴት* የሚለው ቃል ፍቺ .....................ነው፡፡

ሀ/ ዋጋ ለ/ ቀረጥ ሐ/ ውበት መ/ መጠን

10) በምንባቡ አውድ ‹‹*ማድነቅ*›› የሚለውን ቃል ሊተካ የሚችለው የቱ ነው?

ሀ/ ማቆየት ለ/ መንከባከብ ሐ/ ማክበር መ/ ማጋነን

11) ተጨባጭ ያልሆነ ቅርስ ውስጥ የሚካተተው የቱ ነው?

ሀ/ ብሔራዊ ፓርኮች ለ/ ሐውልቶች እና ቅርፃቅርፅች

ሐ/ የተለያዩ እምነታዊ ስርአቶች መ. አልባሳትና ጌጦች

12) ጠቀሜታ ላይ የተመሰረተ የቅርስ አከፋፈል ...................... ይባላል፡፡

ሀ/ ባህላዊ እና ተፈጥሯዊ ቅርስ

ለ/ የአለም ቅርስ እና ብሔራዊ ቅርስ

ሐ/ ተንቀሳቃሽ እና የማይንቀሳቀስ ቅርስ

መ/ ተጨባጭ እና ተጨባጭ ያሌሆነ ቅርስ

13) በምንባቡ መሰረት «*አሻራ*» የሚለው ቃል ፍቺ .......................ነው፡፡

ሀ/ ምልክት ለ/ እንከን ሐ/ ጠባሳ መ/ እንቅፋት

14. የሰው ልጅ ቅርስ አልባ ቢሆን ምን ጉዳት አለው?

ሀ/ የየትኛው ሀገር ዜጋ መሆኑን መለየት አይቻልም ነበር፡፡

ለ/ ታሪኩን ከትውልድ ወደ ትውልድ ማስተላለፍ አይቻልም ነበር፡፡

ሐ/ በአንድ ዘመን የነበረን አስተሳሰብ፣ ወግና ስርአት መገንዘብ ይቸግር ነበር፡፡

መ/ እርስ በእርስ አለመግባባትና የተፈጥሮ አደጋዎች ይበዙ ነበር፡፡

15) *ቅርስ ተፈጥሮ የለገሰንን እና የሰው ልጅ በኖረበት ዘመን ያከማቻቸውን <u>የፈጠራ ውጤቶች</u> ሁሉ የሚያካትት በመሆኑ ቁጥሩ እና አይነቱ እጅግ ብዙ ነው፡፡* በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ከአማራጮቹ የማይገሌፀው የቱን ነው?

ሀ/ መስጊዶችን እና ቤተክርስትያኖችን ለ/ ወንዞችን እና ፎፎቴዎችን

ሐ/ ሀውሌቶችን እና ቅርፃ ቅርፆችን መ/ ቤተመንግስቶችን

## መልስ መስጫ

**የተማሪው ኮድ፡-** --------------------

1. _______ 2. _______ 3. _______ 4. _______ 5. _________

6. _______ 7. _______ 8. _______ 9. _______ 10. _________

11. _______12. _______13. _______ 14. ______15. _________

## (ምንባብ ሁለት)

**የተፈታኙ መለያ ኮድ፡- -------------**

**የተፈታኙ ምድብ፡- ሀ) ቁጥጥር ---------- ለ) ሙከራ ------------**

*መመሪያ*፡- ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ በጥሞና በማንበብ ከሥር ለቀረቡላችሁ ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል በምንባቡ መሰረት ትክክል የሆነውን መልስ በመምረጥ መልሱ፡፡

### ጆሮና መስማት

የመስማት ችሎታ እንደ ትልቅ ሐብት ሊቆጠር የሚገባ ውድ ስጦታ ነው፡፡ ብዙዎቻችን ግን ይህንን ልብ አንልም፡፡ ትልቅ ሐብትነቱን የምንረዳው በህመም ወይም በሌላ ድንገተኛ ክስተት መስማት ሳንችል ስንቀር (ስንታወክ) አለያም እድሜያችን እየገፋ እና የመስማት ችሎታችንም እየተዳከመ ሲሄድ ነው፡፡

ድንገተኛ ለሆነ ከፍተኛ ድምጽ መጋለጥ በውስጠኛው የጆሮ ክፍል በሚገኙ ብዙ አቅም የሌላቸው ሕዋሳት ላይ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ እንደ ፍንዳታ ያሉ ከፍተኛ ድምጽ ሲሰማ በተቻለ ፍጥነት አፋችንን ብንከፍት ይህን ጉዳት ማስቀረት እንችላለን፡፡ ምክንያቱም የፍንዳታው ድምጽ በጆሮ ብቻ የሚገባ ከሆነ የድምጽ ግፊት በዚያው በጆሮ ውስጥ ያሉትን ስስ ስሮች ሊበጣጥሳቸው ይችላል፡፡ አፋችንን ከከፈትን ግን

ድምጹ በሁለቱም በኩል በአፍንጫም በጆሮም የመግባት እድል ያገኝና በመስሚያ አካላት ላይ ሚዛናዊ የድምጽ ግፊት ያርፋል፡፡ ይህም ጉዳት አያስከትልም፡፡

በሌላ በኩል አብዛኛውን ጊዜ አንድ ሰው የመስማት ችሎታውን የሚያጣው ጫጫታ በሚበዛባቸው የስራ ቦታዎችና ከፍተኛ ድምፅ ባለባቸው ስፍራዎች ብዙ ጊዜ ሲገኝ እንደሆነ በጥናት ተደርሶበታል፡፡ ከፍተኛ የሚባለው ድምጽ ምን አይነት ነው? የሚለው ጥያቄ በውስጣችን ሊፈጠር ይችላል፡፡ ድምጽ በሶስት መንገዶች ማለትም በጊዜ፣ በድግግሞሽ እና በኃይል ይመደባል፡፡ ጊዜ የሚያመለክተው ድምጹ የሚሰማበትን የጊዜ ርዝመት ነው፡፡ የአንድ ድምጽ ድግግሞሽ መጠን ወይም ቃና በሰከንድ ይህን ያህል ድግግሞሽ ወይም ‹‹ኸርዝ›› ነው ተብል ይገለጻል፡፡ ልንሰማው የምንችለው ልከኛ ድምጽ በሰከንድ ከ 20 እስከ 20 ሺ.ህ የሚበልጥ ርግብግቦሽ ሊኖረው ይገባል፡፡

የአንድ ድምጽ ኃይል ወይም ጥንካሬ የሚለካው ደግሞ “ዴሲቤል” በሚል አሃድ ነው፡፡ ተራ የሆነ ጭውውት በአማካይ 60 ዴሲቤል የሚያህል ጥንካሬ ይኖረዋል፡፡ ከ85 ነጥብ ዴሲቤል ለሚበልጥ የድምጽ መጠን ለረዥም ጊዜ የተጋለጠ ሰው ውሎ አድሮ የመስማት ችሎታውን የማጣት አጋጣሚው ከፍተኛ እንደሚሆን የጆሮ ሐኪሞች ይናገራሉ፡፡ ድምጽ በጣም ጮክ ባለ መጠን በጆሮ ላይ የሚያደርሰው ጉዳት የከፋ ይሆናል፡፡ “በኒውስዊክ” መጽሄት ላይ የቀረበ አንድ ሪፖርት “ጆሮ አንድ በኤሌክትሪክ የሚሰራ መሰርሰሪያ የሚያሰማውን ድምጽ (100 ዳሲቤል) ለሁለት ሰዓት ያህል መቋቋም ይችላል፡፡ በቪዲዮ ማጫወቻ ቦታዎች የሚሰማውን ሁከት ግን (110 ዳሲቤል) ከ30 ደቂቃ በላይ መቋቋም አይችልም፡፡ የድምጽ መጠን በ10 ዴሲቤል ሲጨምር ጆሮን የመጉዳት ኃይሉ በ10 እጥፍ ይጨምራል” ሲል ገልጿል፡፡

አንድ ድምጽ 120 ዴሲቤል ገደማ ሲደርስ ጆሮ እንደሚያሳምም ሙከራዎች አረጋግጠዋል፡፡ አንዳንድ የቤት ውስጥ የሙዚቃ መሳሪዎች ከ140 ዴሲቤል የሚበልጥ ድምጽ ማውጣት ይችላሉ፡፡ የተለያዩ ድምጾች የተለያዩ የዴሲቤል መጠን ይኖራቸዋል፡፡ ለምሳሌ መተንፈስ 10፣ ማንሾካሾክ 20፣ ጭውውት 60፣ የስራ መግቢና መውጫ ሰዓት ግርግር 70፣ የመኪናዎች እንቅስቃሴ 80፣ በኤሌክትሪክ የሚሰራ መጋዝ 110፣ አውሮፕላን ሲያርፍ 120፣ የጠመንጃ ተኩስ 140 ዴሲቤል ይኖራቸዋል፡፡

ለመሆኑ ድምጽ የምንሰማው እንዴት ነው? ከውጪ አይናችን ኋላ የሚገኘው የጆሮ ክፍል የሚያገለግለው የድምጽ ሞገዶችን ሰብስቦ ወደ ውስጠኛው የጆሮ ክፍል ለማስገባት ነው፡፡ ከዚያም የድምጽ ሞገድ ወደ ጆሮ ታምቡር ይደርሳል፡፡ የድምጽ ሞገድ የጆሮው ታምቡር እንዲርገበገብ ያደርግና የጆሮ ታምቡሩ በተራው በመካከለኛው ጆሮ ውስጥ የሚገኙት ሶስት አጥንቶች እንዲርገበገቡ ያደርጋል፡፡ ቀጥሎ እርግብግቢቱ ፈሳሽ ወደ ተሞላውና በአጥንት ወደ ተከበበው የውስጠኛ ጆሮ ይገባል፡፡ ከዚያም የድምጹ እርግብግቢት የቀንድ አውጣ ቅርጽ ባለውና ኮክሊያ በተሰኘው የውስጠኛው ጆሮ ክፍል በሚገኘው ፈሳሽ በኩል ያልፋል፡፡ በኮክሊያ ውስጥ ፀጉር መሰል ሕዋሳት ይገኛሉ፡፡ በኮክሊያ ውስጥ የሚገኘው ፈሳሽ ፀጉር መሰል ሕዋሳት የላይኛው ክፍላቸውን በማንቀሳቀስ የነርቭ መልእክት እንዲተላለፍ ያደርጋል፡፡ እነዚህ መልዕክቶች ወደ አንጎል ይተላለፍና ድምፅ ሆነው ይሰማሉ፡፡

ለመስሚያ የሚያገለግለው የአንጎል ክፍል ደግሞ አንጎል ለየትኛው ድምጽ ትኩረት መስጠትና የትኛውን ደግሞ ችላ ብሎ ማለፍ እንደሚኖርበት እንዲለይ ያስችለቸዋል፡፡ ለምሳሌ አንዲት እናት ስራ እየሰራች ህፃን ልጅዋ ሲጫወት የሚያሰማውን ድምጽ ሆን ብላ አታዳምጠውም፡፡ ደንግጦ በሚጮህበት ጊዜ ግን ወዲያው ብድግ ትላለች፡፡ የዚህ ምክንያቱ አንጎል ድምጽን የመለየት ስራ ስለሚያካሂድ ነው፡፡ በሁለት ጆሯችን የምናዳምጥ መሆናችን ከተለያዩ አቅጣጫዎች የሚመጡ ድምፆችን ለመስማት ያስችለዋል፡፡ ይሁን እንጂ ንግግር የታከለበት ድምጽ ከሆነ አንጎል ሊረዳ የሚችለው በአንድ ጊዜ አንድ መልእክት ብቻ ነው፡፡ ሌሎችን ድምጾች ይሰማቸዋል እንጂ አይረዳቸውም፡፡ ለማንኛውም በጣም ጮክ ያለ ድምጽ መስማት የጆሮ የመስማት አቅም እየቀነሰ እንደሚመጣ መረዳቱ ጠቃሚ ነው፡፡ ከ90 ዴሲቤል በላይ መጠን ላለመጋለጥ መጣርም ይገባል፡፡

*ምንጭ፡-አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ ሐምሌ 24/1994 ዓ.ም*

1) የመስማት ችሎታ እንደ ትልቅ ሀብት ሊቆጠር የሚገባ ውድ ስጦታ ነው፡፡ ብዙዎችን ግን ይህንን ልብ አንልም፡፡ በሚለውው አረፍተነገር ውስጥ የተሰመረበት ሐረግ ትርጉም ............................ነው፡፡

   ሀ/ አናገኘውም ለ/ አናስበውም ሐ/ አንመኘውም መ/ አንጠብቀውም

2) በምንባቡ መሰረት ድንገተኛ ለሆነ ከፍተኛ ድምጽ ስንጋለጥ ማድረግ ያለብን ምንድነው?

ሀ/ ጆሯችንን መድፈን ለ/ ድምጽ በሌለበት አካባቢ መኖር

ሐ/ አፋችንን መክፈት መ/ መሸሽ

3) በምንባቡ ውስጥ እንደቀረበው የድምፅ መለኪያ ............................ነው፡፡

ሀ/ ሕዋስ ለ/ ኸርዝ ሐ/ ዴሲቤል መ/ ኮክሊያ

4) በምባቡ መሰረት ድምጽ እንዲሰማ ከሚያስፈልጉን ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው?

ሀ/ ዴሲቤል ለ/ የድምጽ ሞገድ

ሐ/ የጆሮ የውጨኛው ክፍል መ/ የጆሮ ታምቡር እርግብግቢት

5) የምንባቡ መልእክት የሆነው ከሚከተሉት የትኛው ነው?

ሀ/ ድምፅ በተለያየ መንገድ ይመደባል ለ/ መጠነኛ ድምጽ ለጤናማ ጆሮ

ሐ/ ድምጽ እንዴት ይሰማል መ/ እናቶች ለህጻናት ትኩረት ይስጡ

6) በጣም ጮክ ያለ ድምጽ መስማት የጆሮን የመስማት አቅም እየቀነሰው እንደሚመጣ መረዳቱ ጠቃሚ ነው፡፡ በሚለው አረፍተነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል ትርጉም ...........ነው፡፡

ሀ/ ፀጥ ለ/ ከፍ ሐ/ ፈጠን መ/ ዝግ

7) በቀረበው ምንባብ የስድስተኛው አንቀጽ ትኩረት ምንድን ነው?

ሀ/ ድምጽ እንዴት እንደሚፈጠር ለ/ ድምጽን እንዴት እንደምንሰማ

ሐ/ ድምጽ ለጆሮ እንዴት ጠንካራ እንደሆነ መ/ የጆሮ አፈጣጠር ምን እንደሚመስል

8) ይህ ምንባብ ርዕሱ ይቀየር ቢባል ሊስማማው የሚችለው የቱ ነው?

ሀ/ የጆሮን ጤንነት መጠበቅ ለ/ ከፍተኛ ድምጽ

ሐ/ መስማት ጠቃሚ ነው መ/ መስማትን መለማመድ

9) ... ልጅዋ ሲጫወት የሚያሰማውን ድምጽ ሆን ብላ ... ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሀ/ በቸልታ ለ/ አስባ ሐ/ በተንኮል መ/ ደንግጣ

10) በምንባቡ መሰረት ከሚከተለት አንዱ ስህተት ነው፡፡

ሀ/ ድንገተኛ ድምጽ በጆሮ ብቻ የሚገባ ከሆነ የድምጹ ግፊት በጆሮ ውስጥ ያሉትን ስራ ስሮች ይበጣጥሳል፡፡

ለ/ ልንሰማው የምንችለው ወይም የሚገባው ልከኛ ድምጽ ከ20 እስከ 20 ሺህ የሚበልጥ ርግብግቦሽ ሊኖረው ይገባል፡፡

ሐ/ ለከፍተኛ የድምጽ ዴሲቤል የተጋለጠ ሰው የመስማት ችሎታው እየጠነከረ ይመጣል፡፡

መ/ የድምጽ መጠን በ10 ዳሲቤል ሲጨምር ጆሮን የመጉዳት ኃይለ 10 እጥፍ ይጨምራል፡፡

11) በአንቀፅ አራት እና አምስት ከተዘረዘሩት የድምፅ መከሰቻዎች ለጆሮ ተስማሚ ሊሆን የሚችለው የድምፅ መጠን የቱ ነው?

ሀ/ 60 ዴሲቤል ለ/85 ዴሲቤል ሐ/ 100 ዴሲቤል መ/ 120 ዴሲቤል

12) በምንባቡ መሰረት ኸርዝ ምንድን ነው?

ሀ/ መስማትን የሚያውክ ጫጫታ ለ/ የጆሮ ህመም

ሐ/ የድምፅ መለኪያ መ/ የድምፅ ድግግሞሽ

13) በምንባቡ እንደተገለፀው ህዋስ ..................ነው፡፡

ሀ/ ስሜት ለ/ ሰውነት የተገነባበት ደቂቀ አካል

ሐ/ በሽታ አምጪ ተህዋስ መ/ የጆሮ የውጨኛው ክፍሌ

14) ሰዎች የመስማትን ጥቅም የበለጠ ከሚረዱበት መንገድ ውስጥ <u>የማይካተተው</u> የቱ ነው?

ሀ/ መስማት ሲሰለቻቸው

ለ/ በህመም ምክንያት መስማት ሲቸገሩ

ሐ/ በእድሜ መግፋት ምክንያት መስማት ሳይችሉ ሲቀሩ

መ/ ድንገተኛ በሆነ ክስተት ሲታወኩ

15) በምንባቡ መሰረት ‹‹ማንሾካሾክ›› የሚለው ቃል ፍቺ ...........................ነው፡፡

ሀ/ ማንኳኳት ለ/ መጋጨት ሐ/ ቀስ ብሎ ማውራት መ/ መጣራት

## መልስ መስጫ

**የተማሪው ኮድ፡- --------------------**

1. _______ 2. _______ 3. _______ 4. _______ 5. _________

6. _______ 7. _______ 8. _______ 9. _______ 10. _________

11. _______12. _______13. _______ 14. ______15. _________

# አባሪ ሐ

# የተጠኚዎች ቅድመ-ትምህርት አንብቦ መረዳት ፈተና የውጤት ማጠቃለያ ሰንጠረዥ

| የተጠኚዎች ኮድ | የቁጥጥር ቡድን | የተጠኚዎች ኮድ | የሙከራ ቡድን |
|---|---|---|---|
| | የቅድመ-ትምህርት ፈተና ውጤት ከ30 | | የቅድመ-ትምህርት ፈተና ውጤት ከ30 |
| 01 | 16 | 26 | 15 |
| 02 | 14 | 27 | 17 |
| 03 | 18 | 28 | 17 |
| 04 | 19 | 29 | 13 |
| 05 | 14 | 30 | 18 |
| 06 | 10 | 31 | 11 |
| 07 | 18 | 32 | 14 |
| 08 | 15 | 33 | 18 |
| 09 | 14 | 34 | 15 |
| 10 | 20 | 35 | 17 |
| 11 | 12 | 36 | 15 |
| 12 | 20 | 37 | 18 |
| 13 | 16 | 38 | 19 |
| 14 | 18 | 39 | 21 |
| 15 | 15 | 40 | 11 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 16 | 17 | 41 | 19 |
| 17 | 12 | 42 | 16 |
| 18 | 20 | 43 | 18 |
| 19 | 18 | 44 | 14 |
| 20 | 12 | 45 | 17 |
| 21 | 19 | 46 | 20 |
| 22 | 17 | 47 | 15 |
| 23 | 15 | 48 | 18 |
| 24 | 18 | 49 | 20 |
| 25 | 20 | 50 | 16 |

## አባሪ መ

## የተጠኚዎች ድህረ-ትምህርት አንብቦ መረዳት ፈተና የውጤት ማጠቃለያ ሰንጠረዥ

| የተጠኚዎች ኮድ | የቁጥጥር ቡድን | የተጠኚዎች ኮድ | የሙከራ ቡድን |
|---|---|---|---|
| | የድህረ-ትምህርት ፈተና ውጤት ከ30 | | የድህረ-ትምህርት ፈተና ውጤት ከ30 |
| 01 | 17 | 26 | 17 |
| 02 | 16 | 27 | 21 |
| 03 | 19 | 28 | 20 |
| 04 | 21 | 29 | 19 |
| 05 | 16 | 30 | 20 |
| 06 | 12 | 31 | 18 |
| 07 | 18 | 32 | 19 |
| 08 | 16 | 33 | 20 |
| 09 | 15 | 34 | 20 |
| 10 | 22 | 35 | 23 |
| 11 | 14 | 36 | 19 |
| 12 | 21 | 37 | 22 |
| 13 | 16 | 38 | 23 |
| 14 | 18 | 39 | 24 |
| 15 | 16 | 40 | 19 |
| 16 | 17 | 41 | 21 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 17 | 14 | 42 | 19 |
| 18 | 22 | 43 | 20 |
| 19 | 18 | 44 | 19 |
| 20 | 13 | 45 | 22 |
| 21 | 20 | 46 | 24 |
| 22 | 17 | 47 | 19 |
| 23 | 16 | 48 | 22 |
| 24 | 18 | 49 | 24 |
| 25 | 22 | 50 | 19 |

# አባሪ ሠ

## ልዩ ልዩ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች

### 1.ቅድመ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች የውጤት ስርጭት

| የቁጥጥር ቡድን ማርክ ስርጭት | | Frequency | Percent | Valid Percent | Cumulative Percent |
|---|---|---|---|---|---|
| Valid | 10 | 1 | .2 | 4.0 | 4.0 |
| | 12 | 3 | .7 | 12.0 | 16.0 |
| | 14 | 3 | .7 | 12.0 | 28.0 |
| | 15 | 3 | .7 | 12.0 | 40.0 |
| | 16 | 2 | .5 | 8.0 | 48.0 |
| | 17 | 2 | .5 | 8.0 | 56.0 |
| | 18 | 5 | 1.2 | 20.0 | 76.0 |
| | 19 | 2 | .5 | 8.0 | 84.0 |
| | 20 | 4 | 1.0 | 16.0 | 100.0 |
| | Total | 25 | 6.2 | 100.0 | |
| Missing | System | 378 | 93.8 | | |
| Total | | 403 | 100.0 | | |

## 2.ቅድመ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች የውጤት ስርጭት

| የሙከራ ቡድን ማርክ ስርጭት | | Frequency | Percent | Valid Percent | Cumulative Percent |
|---|---|---|---|---|---|
| Valid | 10 | 1 | .2 | 4.0 | 4.0 |
| | 12 | 3 | .7 | 12.0 | 16.0 |
| | 14 | 3 | .7 | 12.0 | 28.0 |
| | 15 | 3 | .7 | 12.0 | 40.0 |
| | 16 | 2 | .5 | 8.0 | 48.0 |
| | 17 | 2 | .5 | 8.0 | 56.0 |
| | 18 | 5 | 1.2 | 20.0 | 76.0 |
| | 19 | 2 | .5 | 8.0 | 84.0 |
| | 20 | 4 | 1.0 | 16.0 | 100.0 |
| | Total | 25 | 6.2 | 100.0 | |
| Missing | System | 378 | 93.8 | | |
| Total | | 403 | 100.0 | | |

3.ድህረ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች የውጤት ስርጭት

| የቁጥጥር ቡድን ማርከ ስርጭት | | Frequency | Percent | Valid Percent | Cumulative Percent |
|---|---|---|---|---|---|
| Valid | 12 | 1 | .3 | 4.0 | 4.0 |
| | 13 | 1 | .3 | 4.0 | 8.0 |
| | 14 | 2 | .5 | 8.0 | 16.0 |
| | 15 | 1 | .3 | 4.0 | 20.0 |
| | 16 | 6 | 1.6 | 24.0 | 44.0 |
| | 17 | 3 | .8 | 12.0 | 56.0 |
| | 18 | 4 | 1.1 | 16.0 | 72.0 |
| | 19 | 1 | .3 | 4.0 | 76.0 |
| | 20 | 1 | .3 | 4.0 | 80.0 |
| | 21 | 2 | .5 | 8.0 | 88.0 |
| | 22 | 3 | .8 | 12.0 | 100.0 |
| | Total | 25 | 6.6 | 100.0 | |
| Missing | System | 352 | 93.4 | | |
| Total | | 377 | 100.0 | | |

### 4. ድህረ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች የውጤት ስርጭት

| የሙከራ ቡድን ማርክ ስርጭት | | Frequency | Percent | Valid Percent | Cumulative Percent |
|---|---|---|---|---|---|
| Valid | 17 | 1 | .3 | 4.0 | 4.0 |
| | 18 | 1 | .3 | 4.0 | 8.0 |
| | 19 | 8 | 2.1 | 32.0 | 40.0 |
| | 20 | 5 | 1.3 | 20.0 | 60.0 |
| | 21 | 2 | .5 | 8.0 | 68.0 |
| | 22 | 3 | .8 | 12.0 | 80.0 |
| | 23 | 2 | .5 | 8.0 | 88.0 |
| | 24 | 3 | .8 | 12.0 | 100.0 |
| | Total | 25 | 6.6 | 100.0 | |
| Missing | System | 352 | 93.4 | | |
| Total | | 377 | 100.0 | | |

## 5. ቅድመ-ትምህርት አጠቃላይ ፍላጎት የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ

**Descriptive Statistics**

| | N | Mean | | Std. Deviation |
|---|---|---|---|---|
| | Statistic | Statistic | Std. Error | Statistic |
| A0001 | 25 | 2.56 | .117 | .583 |
| A0002 | 25 | 2.44 | .130 | .651 |
| A0003 | 25 | 2.28 | .136 | .678 |
| A0004 | 25 | 2.52 | .117 | .586 |
| A0005 | 25 | 2.44 | .142 | .712 |
| A0006 | 25 | 2.32 | .095 | .476 |
| A0007 | 25 | 2.60 | .100 | .500 |
| A0008 | 25 | 2.44 | .142 | .712 |
| A0009 | 25 | 2.56 | .130 | .651 |
| A0010 | 25 | 2.32 | .125 | .627 |
| A0011 | 25 | 2.76 | .105 | .523 |
| A0012 | 25 | 2.36 | .114 | .569 |
| A0013 | 25 | 2.80 | .100 | .500 |
| A0014 | 25 | 2.48 | .117 | .586 |
| A0015 | 25 | 2.40 | .100 | .500 |
| A0016 | 25 | 2.52 | .102 | .510 |
| A0017 | 25 | 2.48 | .117 | .586 |
| A0018 | 25 | 2.40 | .115 | .577 |
| A0019 | 25 | 2.64 | .128 | .638 |
| A0020 | 25 | 2.44 | .117 | .583 |
| Valid N (listwise) | 25 | | | |

## 6. ቅድመ-ትምህርት የማንበብ ፍላጎት የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ

| | N | Mean | | Std. Deviation |
|---|---|---|---|---|
| | Statistic | Statistic | Std. Error | Statistic |
| B0001 | 25 | 2.56 | .117 | .583 |
| B0002 | 25 | 2.60 | .129 | .645 |
| B0003 | 25 | 2.56 | .130 | .651 |
| B0004 | 25 | 2.60 | .129 | .645 |
| B0005 | 25 | 2.44 | .101 | .507 |
| B0006 | 25 | 2.64 | .098 | .490 |
| B0007 | 25 | 2.32 | .125 | .627 |
| B0008 | 25 | 2.48 | .117 | .586 |
| B0009 | 25 | 2.64 | .114 | .569 |
| B0010 | 25 | 2.32 | .138 | .690 |
| B0011 | 25 | 2.44 | .174 | .870 |
| B0012 | 25 | 2.44 | .142 | .712 |
| Valid N (listwise) | 25 | | | |

## 7 ቅድመ-ትምህርት የማንበብ ችሎታ የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ

| | N | Mean | | Std. Deviation |
|---|---|---|---|---|
| | Statistic | Statistic | Std. Error | Statistic |
| C0001 | 25 | 2.76 | .087 | .436 |
| C0002 | 25 | 2.80 | .082 | .408 |
| C0003 | 25 | 2.60 | .163 | .816 |
| C0004 | 25 | 2.32 | .095 | .476 |
| C0005 | 25 | 2.60 | .100 | .500 |
| C0006 | 25 | 2.44 | .142 | .712 |
| C0007 | 25 | 2.56 | .130 | .651 |
| C0008 | 25 | 2.32 | .125 | .627 |
| Valid N (listwise) | 25 | | | |

8 ድህረ-ትምህርት አጠቃላይ ፍላጎት የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ

| | N | Mean | | Std. Deviation |
|---|---|---|---|---|
| | Statistic | Statistic | Std. Error | Statistic |
| A0001 | 25 | 3.48 | .131 | .653 |
| A0002 | 25 | 3.60 | .115 | .577 |
| A0003 | 25 | 3.68 | .150 | .748 |
| A0004 | 25 | 3.64 | .128 | .638 |
| A0005 | 25 | 3.76 | .133 | .663 |
| A0006 | 25 | 3.92 | .128 | .640 |
| A0007 | 25 | 3.72 | .136 | .678 |
| A0008 | 25 | 3.68 | .125 | .627 |
| A0009 | 25 | 3.52 | .131 | .653 |
| A0010 | 25 | 3.88 | .120 | .600 |
| A0011 | 25 | 3.80 | .129 | .645 |
| A0012 | 25 | 3.72 | .136 | .678 |
| A0013 | 25 | 3.76 | .156 | .779 |
| A0014 | 25 | 3.84 | .125 | .624 |
| A0015 | 25 | 3.68 | .138 | .690 |
| A0016 | 25 | 3.76 | .156 | .779 |
| A0017 | 25 | 3.76 | .145 | .723 |
| A0018 | 25 | 3.72 | .136 | .678 |
| A0019 | 25 | 3.56 | .130 | .651 |
| A0020 | 25 | 3.68 | .111 | .557 |
| Valid N (listwise) | 25 | | | |

## 9 ድህረ-ትምህርት የማንበብ ፍላጎት የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ

**Descriptive Statistics**

| | N | Mean | | Std. Deviation |
|---|---|---|---|---|
| | Statistic | Statistic | Std. Error | Statistic |
| B0001 | 25 | 3.84 | .111 | .554 |
| B0002 | 25 | 3.88 | .120 | .600 |
| B0003 | 25 | 3.76 | .087 | .436 |
| B0004 | 25 | 3.80 | .115 | .577 |
| B0005 | 25 | 3.96 | .091 | .455 |
| B0006 | 25 | 3.84 | .095 | .473 |
| B0007 | 25 | 3.96 | .091 | .455 |
| B0008 | 25 | 3.92 | .114 | .572 |
| B0009 | 25 | 3.84 | .125 | .624 |
| B0010 | 25 | 3.92 | .128 | .640 |
| B0011 | 25 | 3.96 | .122 | .611 |
| B0012 | 25 | 3.96 | .108 | .539 |
| Valid N (listwise) | 25 | | | |

## ድህረ-ትምህርት የማንበብ ችሎታ

**Descriptive Statistics**

| | N | Mean | | Std. Deviation |
|---|---|---|---|---|
| | Statistic | Statistic | Std. Error | Statistic |
| C0001 | 25 | 3.72 | .147 | .737 |
| C0002 | 25 | 3.76 | .145 | .723 |
| C0003 | 25 | 3.72 | .136 | .678 |
| C0004 | 25 | 3.92 | .114 | .572 |
| C0005 | 25 | 3.72 | .123 | .614 |
| C0006 | 25 | 3.96 | .122 | .611 |
| C0007 | 25 | 3.72 | .108 | .542 |
| C0008 | 25 | 3.96 | .122 | .611 |
| Valid N (listwise) | 25 | | | |

## የፍላጎትና የውጤት ግንኙነት

**Correlations**

| | | A0001 | B0002 |
|---|---|---|---|
| A0001 | Pearson Correlation | 1 | .294 |
| | Sig. (2-tailed) | | .153 |
| | Sum of Squares and Cross-products | 94.240 | 1.672 |
| | Covariance | 3.927 | .070 |
| | N | 25 | 25 |
| B0002 | Pearson Correlation | .294 | 1 |
| | Sig. (2-tailed) | .153 | |
| | Sum of Squares and Cross-products | 1.672 | .633 |
| | Covariance | .070 | .016 |
| | N | 25 | 40 |